ብለው በመታዘዛቸው እንቅስቃሴው እንደተገታ ፕሮፌሰር ጌታቸው በመጽሐፋቸው ዘርዝረዋል። በዓለማችን ላይ በነፃ ፈቃድ፣ ምርጫና ስብከተ ወንጌል የታወቀው ክርስትና በኢትዮጵያ ቅዱሳን ያነሱትን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ በገመድ፣ በጠመንጃና በእሳት በማስፈራራት የሰዎችን የማሰብና የመምረጥ ነፃነት በኃይል ሲያኮላሽ እንመለከታለን። ከአራተኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ "ክርስትና" በኢትዮጵያ የተስፋፋው በወንጌል ስብከት ብቻ ሳይሆን በነገሥታት ጉልበት እንደሆነ ታሪክ ምስክር ሲሆን ከላይ የተመለከትነው የዐፄ ያግብ ጽዮን የማስፋራራትና የኃይል እርምጃና ዛቻ አንዱ ማስረጃ ነው።

*"የኢትዮጵያ ነገሥታት የቤተ ክርስቲያንን አስተዳደር ከመንግሥታቸው አመራር ለይተው አይመለከቱም ነበር"*[217] በተለይ ዐፄዎቹ ከቤተ ክህነት ጋር በመጣመር ለአገር አንድነት ያላቸው ብርቱ ትጋት ቢደነቅም ክርስትና ሕይወት ለዋጭ መሆኑ ተዘንግቶ የፖለቲካና የግዛት ማስፋፊያ መሣሪያ ማድረጋቸው በመንፈስና በሥጋ ላለንበት ፈርጀ ብዙ ቀውስ ምክንያት ሆነዋል። በአገራችን ክርስቶስ ያልገነነበት አፋዊ ክርስትና መንሰራፋት ብቻ ሳይሆን የለውጥ ጠላቶች አድርጎናል። ዓለም ሁሉ በሁለንተናዊ ለውጥ ባሕር ሲዋኝ እኛ በነገር ሁሉ ከሁሉ ኋላ ቀርተን ዛሬም እንደቀዳሚዎች መፎከራችን ያሳዝናል። ከዚህም የተነሣ አብዛኛው ሕዝባችን በቃሉና በመንፈሱ ልቡ ሳይለወጥ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ጋር የተፋታና ለክርስቶስ ባዕድ በሆነ አገራዊ የ"ክርስትና" ዱር ተውጧል። ክርስትናችን የቃሉና የመንፈሱ ድሃ፣ የሰይፍ፣ የስደት፣ ሰዎችን የማስቃየት፣ የመግደል፣ ፀረ ምናምን እያለን የመፈረጅ፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ የሰው ልጆች ቁም ስቅል የሚያዩበት የሥጋትና የስቃይ ካምፕ መስሎ እንደዘለቀ ብዙ ምሁራንና የታሪክ ሊቃውንት ዘግበዋል።

ክርስትናን በጠራ የወንጌል ስብከት ሳይሆን በሥጋ ኃይል ማስፋፋት እንደ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ሽፋን የተሰጠው ስለሆነ ምድራችንን ከእርግማን በታች ያቆየን ሰንኮፍ ሆኖብናል። በአጠቃላይ በዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን የምንመለከተው በኢትዮጵያ ክርስትና ሥጋዊ የኃይል አጠቃቀም አይሎ መቀጠሉን ነው። በአጭር ቃል በዘመኑ የነበሩ ጥቂት ቅዱሳን እግዚአብሔር በቃሉ የገለጠላቸውን እውነት በመያዝ ነባሩንና የተንሻፈፈን አስተምህሮ ለማቅናት በተነሡ ጊዜ ሞት ሲታወጅባቸው ዝም ለማለት እንደተገደዱ ታሪክ ምስክር ነው። ይህ በኢትዮጵያ ከሚሲዮናውያንና ከወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ልደት እጅግ የቀደመ የተሐድሶ/ለውጥ ጥያቄ እንደሆነ ልብ ይበሉ። የተሐድሶ ጥያቄ በኃይል አዋጅ ለጊዜው ቢታፈንም ሙሉ በሙሉ አልከሰመም፡ ነበር። ከዚህ የተሐድሶ ጥያቄ በኋላ የተከተለው፡-

[217] *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ (2000 ዓ.ም) ገጽ 330*





## ደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን

*የሀገራችን ያልሆነ ትምህርት ታስተምራለህ! ሲሉ በጥል ተነሡብኝ።
የዚህች አገር ትምህርት ምንድነው? እንዴትስ የሌላ ነው? በክርስቶስና
በአንዲት ቤተ ክርስቲያን ከሆነው ሁሉ በቀር ሌላ አላውቅም።
አባ እስጢፋኖስ*

ደቂቀ እስጢፋኖስ የተባሉት በአሥራ አምስተኛው ምእተ ዓመት በኢትዮጵያ በነበረችው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ላስነሱት ለአባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው የተሰጠ ስም እንደሆነ ይነገራል። ደቂቅ ማለት "ልጆች" ማለት ሆኖ እንደ "ደቀ መዝሙር" የተከታዮች መጠሪያ ነው። አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቻቸው *(1406 - 1421)* ይዘውት የተነሡትን የተሐድሶ ጥያቄ ፕሮፌሰር ኃይሌ በመጽሐፋቸው፡-

*ለአብ፣ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ በቀር (ለወላዲተ አምላክ) ሥዕል፣ ለመስቀልና ለንጉሥ አንሰግድም (እራስን የሚያስጎነብስ እጅ አንነሳም) ከቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት ውጪ የሆኑትን አንቀበልም የሚባል እንደነበር ይገልጻሉ።*

እንዲሰገድለት በብርቱ ለሚፈልግ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስግደት ጥያቄ አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ እንቢ ይሉ ነበር፡-

*እስጢፋኖስና ደቂቀ እስጢፋኖስ ወደ ንጉሡ በቀረቡ ጊዜ ኹሉ እጅ መንሣታቸው አልቀረም፤ ንጉሡ ግን በዚህ አልረካምና ለምን አትሰግድልኝም? ሲል አፍ አውጥቶ ጠየቀው። እግዚአብሔር ብቻ እንጂ ለፍጡራን ይሰግድ ዘንድ እንዳልታዘዘ ነገረው።*[218] *ንጉሡም ራስኽን ዝቅ በማድረግ የማትሰግደው ለምድነው? ሲል እስጢፋኖስን ጠየቀው፤ እርሱም ሲመልስ አንተ እንደምትለው እንድንሰግድ በመጽሐፍ አልታዘዘም። ለእግዚአብሔር እንድንሰግድ ታዘናል እንጂ። ስግደት ከእኛ አትፈልግ፤ ጸሎትና ቡራኬ ይበቃኻልና አለው።*[219]

## አባ እስጢፋኖስ
### በዐፄ ይስሐቅ ችሎት(1406-1421) ተቀባይነት ስለማግኘታቸው

አባ እስጢፋኖስ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የንግሥና መንበራቸውን ከመቆናጠጣቸው በፊት በዐፄ ይስሐቅ ዘመን *(1406-1421)* ስለ ትምህርታቸው ተከሰው ንጉሥ ፊት ቀርበው ነበር። አባ እስጢፋኖስ በንጉሥ፣ በጳጳስ፣ በመነኮሳትና በደብተራዎች ፊት ቆመው ትምህርታቸው

[218] ዘአኀተም መምህር ወማኅበር ዘጉንዳጉንዶ ደብረ ገሪዛን ማርያም ገዳም *(1996 ዓ.ም)፤ ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ ገጽ ፲፮*
[219] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 139*

ከእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ባመለከቱ ጊዜ መሳሳታቸውን ሊያመለክት ማንም አልቻለም።

*ከዚያ በኋላ ንጉሡ እንዲህ የሚል ዐዋጅ ይነገር ዘንድ አዘዘ። ይህ መነኩሴ ትምህርቱ ቀና አይደለም፤ ከሕግ ውጪ ያስተምራል በማለት ከስሰው ወደዚህ አምጥተው ነበር። አሁን እኔና ካህናተ ደብተራ ኹሉ ነገሩ የታመነና ትምህርቱም ቅዱሳን ሐዋርያት እንደሚያስተምሩት ትምህርት ወንጌል እውነተኛ እንደሆነ ተረድተናል። ስለዚህ እኛ ትምህርቱን ተቀብለነዋልና እናንተም ውደዱት። ከዚህም ኋላ ከሌሎች አውራጃዎች ትምህርቱን መከተል የሚወድ ማንም ሰው አይከልክል።*[220]

## በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት - ስለመወገዛቸው

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ወደ ዙፋን ከመጣ በኋላ ነገሩ ተገለበጠ።

*አባ እስጢፋኖስ በክሐዲነት ተከሰው ከሱ በፊት በነገሡው በዐፄ ይስሐቅ ችሎት ሲቀርቡ ከገለጡት እምነታቸው የተለየ አልነበረም። ሆኖም በዐፄ ይስሐቅ ችሎት የተመሰገኑ መነኩሴ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ተወገዙ።*[221]

አባ እስጢፋኖስ በዐፄ ይስሐቅ ችሎት ፊት ተከሰው ቀርበው ካህናትና ደብተራዎች ሁሉ ባሉበት ጉባኤ አቅርበው ትምህርታቸው ከሐዋርያት ትምህርት የሚስማማ መሆኑ ተመስክሮላቸው በነፃነት እንዲያስተምሩ ተፈቅዶላቸው ነበር። አባ እስጢፋኖስ የመጀመሪያ ትምህርታቸውን ሳይለውጡ፣ ከካህናትና ከደብተራዎች መካከል መሳሳታቸውን በግልጽ በቃሉ ያሳየ አንድም ሰው ሳይኖር በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ችሎት ለምን ተወገዙ? አባ እስጢፋኖስ በሐዋርያት ትምህርት ላይ ከቆሙ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ምን ላይ ቆሞ ነው እነርሱን ያወገዘው? መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የላቸውም።

ንጉሥ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ደቂቀ እስጢፋኖስን እጅግ ከመጥላቱና ከመቃወሙ የተነሣ አባ እስጢፋኖስን "እስጢፋ" ተከታዮቻቸውንም "ደቂቀ እስጢፋ" (የእስጢፋኖስ ልጆች) ይላቸው ነበር። ይህም የሽሙጥ ስም እንደሆነና ደቂቀ እስጢፋኖስ ሽሙጡ እንደገባቸው ከሆነ "እስጢፋ" ማለት በግብጽ ቋንቋ የሰይጣን ስም ስለሆነ እኛን የሰይጣን ልጆች ለማለት ነው፤ ይላሉ።

## የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስደት አዋጅ

### የአዋጁ ሙሉ ቃል በግዕዝ

*አብለክሙ ኦ ሕዝበ ክርስቲያን ምእመናኒሃ ለማርያም ድንግል በክልኤ። ኵሉ ብእሲ ዘተወክፈ ኪያሆሙ፤ ወዘተሳተፈ ምስሌሆሙ፤ ወዘአንበሮሙ ውስተ ቤቱ ወኀበ ቤተክርስቲያን ወውስተ ምድረ ርስቱ እመሂ ሥዩም ይሰዐር። ወይትበርበር ቤቱ ወኵሉ ንዋዩ፡ ወምድረ ርስቱ ይኩን ለባዕድ። ሊቃነ ካህናትኒ ወንቡራነ እድ ውኵሎሙ ሥዩማነ ቤተ ክርስቲያን ወመነኮሳትሂ ወኵሎሙ ሕዝብ ለእመ ተረከቡ እንዘ የኀብኡ ኪያሆሙ፡ ፈድፋደ ኵነኔ ላዕሌሆሙ። ሢመቶሙ ወምድረ ርስቶሙ ይኩን ለካልእ እስመ ኮኑ ሱቱፋነ ምስሌሆሙ። ወእሙንቱሰ ደቂቀ እስጢፋ በአማን አይሁድ እሙንቱ፤ እለ አብዩ ሰጊደ ለማርያም ድንግል በክልኤ፣ ወለ መስቀል ወልዳ። ሎሙሰ ኵነኔሆሙ ሞት። ወዘረከቦሙሂ ይኩንኖሙ በጽኑዕ ኵነኔ። ወቀቲልሰ ኢይቅትሎሙ፤ አላ ያብጽሖሙ ውስተ ኩርጓኔነ ከመ ንስማዕ ቃሎሙ፤ ወከመ ይኩን ፍትሕ ላዕሌሆሙ። ወዘሂ ተረከበ ብእሲ እንዘ ይብሎ ሰላም ለእስጢፋዊ መክፈልቱ ምስለ እለ ተወከፍዎሙ ለደቂቀ እስጢፋ።*

### የአዋጁ ሙሉ ቃል በአማርኛ

*በነፍስ በሥጋ ድንግል የምትኾን የማርያም ምዕመናን የኾናችሁ ሕዝበ ክርስቲያን ሆይ! እንዲህ እላችኋለሁ:- ማናቸውም ሰው ኹሉ ደቂቀ እስጢፋን የተቀበለ ከእነርሱ ጋር የተባበረ በቤቱ ውስጥም ያኖራቸው፣ ወይም በቤተ ክርስቲያኑና በርስቱም ምድር ያኖራቸው ቢገኝ፣ ሹመት ያለው ከኾነም ከሹመቱ ይሻር፣ ቤቱም ይዘረፍ፣ ገንዘቡ ኹሉና ያለው የምድር ርስት ለባዕድ ይኹን።*

*ሊቃነ ካህናት፣ ንቡራነ እድ የቤተ ክርስቲያን ሹማምንትና መነኮሳትም ኹሉ ሕዝቡም ኹሉ እነርሱን ሲደብቁአቸው ከተገኙ በእነርሱ ላይ ከፍ ያለ ቅጣት ይፈጸምባቸዋል። ሹመታቸውና የምድር ርስታቸው ለሌላ ይኹን። ከእነርሱ ጋር ተባብረዋልና ነው። እነዚህ ደቂቀ እስጢፋ ግን ለድንግል ማርያምና ለአንድ ልጇዋ መስቀል መስገድ እምቢ ያሉ ናቸውና፤ በእውነት አይሁድ ናቸው። የእነርሱ ቅጣት ሞት መሆን አለበት። ያገኛቸው ኹሉ በጽኑ መከራ ይቅጣቸው። ቃላቸውን ሰምተን በአደባባያችን ሸንጎ እንድንፈርድባቸው ወደ አደባባያችን ያምጣቸው እንጂ መግደልን ግን እርሱ ራሱ አይግደላቸው። እንደዚሁም ደቂቀ እስጢፋ የኾነውን ሰው አግኝቶ ሰላምታ የሰጠው ሰው ሁሉ ዕድል ፈንታው ደቀ እስጢፋን ለተቀበሉ እንደሚደረግባቸው ይኾናል።*[222]

በማለት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አዋጅ አስነገረ። ለመሆኑ ለማርያምና ለአንድ ልጇዋ መስቀል መስገድ እንቢ ያለ አይሁድ እንደሆነና ሞት እንደሚገባው መጽሐፍ ቅዱስ ይናገራል ወይ? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከዐፄ ያግብ ጽዮን የሚለይበት በሥልጣኑ ተጠቅሞ የማርያምና የመስቀል አምልኮ የኑፋቄ ትምህርት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ በአዋጅ መጫኑና በቃሉ ላይ ቆመው ኑፋቄውን የተቃወሙ አበው ላይ የከፋ ስደትና ጥፋት ማወጁ ነው። አባ እስጢፋኖስ ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ከመነሣቱ በፊት በኢትዮጵያ ምድር የጠራውንና የነጠረውን የወንጌልን እውነት በመረዳት ለተሐድሶ የተነሡ ታላቅ ፋና ወጊ አባት የነበሩ ሲሆን ብዙ ደቀ መዛሙርት (ደቂቀ እስጢፋኖስ የተባሉ) አፍርተው ነበር።

[220] ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ፣ (1996 ዓ.ም)፣ ገጽ 109 - 110
[221] ደቂቀ እስጢፋኖስ ገጽ፣ 25
[222] የኢትዮጵያ ዓመታዊ ታሪክ መጽሔት 4ኛ መጽሔት 1954 ዓ.ም ገጽ 79-87

*የሚዘራውን አትክልት ለጥቻችኋለሁ፤ ያለው ለብዙዎች አይደለምን? በሉት፡ አላቸው፡፡*[228]

*እያንዳንዱንም ለንጉሥ እንዲሰግዱ ያስገድዳቸው ጀመር፤ እነርሱም እንደ አባታቸው እንቢ ባሉት ጊዜ እንደ ትናንቱ ደማቸው እስኪፈስስ ድረስ ደበደባቸውና ኹሉንም በጅንግላ አሰራቸው፡፡ ከዚህ በኋላ የቅዱስ እስጢፋኖስን ማደሪያ አቃጠለው፤ ያላቸውንም ኹሉ ወሰደባቸው ልብሳቸውን ገፈፋአቸው፡፡'*[229] *ከንጉሡ እንደታዘዙት የሽኮናቸውን ቋንጃ መቁረጥ ጀመሩ፡፡ ከነሱ ውስጥ አምኀ ማርያም የሚሏት እጇቿ የታመሙ ጉልበቶቿ የተጣበቁ አንዲት መነኩሲት ነበረች፡፡ የንጉሡን የቁጣ ደረጃ ለማሳየት ያለምሕረት በእርሷ ጀምረው ሁሉንም ፈጸሙ፡፡*[230] ይላል፡፡

ይህ ምን ዓይነት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት ነው? የእግዚአብሔር ቃል፡- *"በላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውንም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ፡፡ አትስገድላቸው አታምልካቸውምም፤" (ዘፀ.20:4-5)፡፡* ኢየሱስ ሊሰገድለት የሚገባ እግዚአብሔር ብቻ እንደሆነ ሲናገር፡- *"ለጌታ ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ" (ማቴ.3:10) ብሏል፡፡* እንዲሁም ሐዋርያው ዮሐንስ ለመልአኩ ልሰግድ በእግሩ ፊት ስደፋ መልአኩ ስግደት ለእግዚአብሔር እንጂ ለእርሱ እንደማይገባ በማስጠንቀቅ የተናገረውን እንመልከት፡- *"እንዳታደርገው ተጠንቀቅ ከአንተ ጋር የኢየሱስ ምስክር ካላቸው ከወንድሞችህ ጋር አብሬ ባሪያ ነኝ ለእግዚአብሔር ስገድ የኢየሱስ መንፈስ የትንቢት መንፈስ ነውና አለኝ" (ራእ.19:9-10)፡፡* ታዲያ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የእግዚአብሔርን ስግደት ለእኔ ካልሰጣችሁ ብሎ ቅዱሳንን የፈጀው ከየት ተምሮ ይሆን? ሰውን ማክበር የተገባ ሲሆን የግድ ሰዎች እንዲያከብሩን መጠየቅና ማስገደድ በልባችን ያለውን ድብቅ ማንነት ያመለክታል፡፡ ለመሆኑ ዘርዓ ያዕቆብ ምድሪቷን በንጹሐን የእምነት አባቶች ደም ሲያጥብ፣ አንዳንድ ካህናትና ደብተራዎችን የህቡዕ አጀንዳው ጋሻ ጃግሬ አድርጎ ሲያሰልፋቸው፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ኑፋቄን ያለ አንዳች ከልካይ ወደ ቤተ መቅደስ ሲያስገባ በየትኛው መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ተመርቶ ይሆን? ከእያንዳንዱ ድርጊት ጀርባ የእግዚአብሔር ወይም የሰይጣን አጀንዳ መኖሩ የታወቀ ሲሆን ከዘርዓ ያዕቆብ ጭፍጨፋ ጀርባ ያለው የማን አጀንዳ ነበር? መልሱን ለአንባቢያን፡፡

ይትባረክ ግደይ፡- *"ዘረኛ ማነው? ኢትዮጵያውያን ፍረዱ!"* በሚል መጽሐፋቸው ዘርዓ ያዕቆብ ለምን ይህን ዘግናኝ ጭፍጨፋ እንዳካሄደ ሲናገር፡- *"ዘርዓ ያዕቆብን ያሣሣቱት ግብጻውያን ጳጳሳት በሃይማይኖት ሰበብ እንደሆነ አያጠራጥርም፡፡ ...በዚያን ወቅት ደግሞ በሃይማኖት የመጣን ነገር ወይም ጠላትን መግደል እንደ ጽድቅ ይቆጠር ስለነበር'*[231] ብለዋል፡፡ ይትባረክ ግደይ እንዳሉት በዚያ ዘመን ለሃይማኖት ብሎ ሰውን መግደል እንደጽድቅ የሚቆጠር ከሆነ የኢትዮጵያ ክርስትና በዚያ ዘመን ዛሬ በእጃችን ካለው መጽሐፍ ቅዱስ የተለየ መመሪያ ያለው አያስመስልም ወይ? ይህም ክርስትናችን በዘመን ሁሉ ግድያን በሚያወግዘው ግልጽ የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ላይ እንዳልተመሠረተና ችግር እንዳለበት ፍንጭ ይሰጣል፡፡ በእውነተኛ ቤተ ክርስቲያንና በአዲስ ኪዳን በየትኛውም ዘመን ሌላውን መግደል እንደ ጽድቅ የተቆጠረበት ዘመን የለምና፡፡

---

[228] *ደቂቀ እስጢፋኖስ 1996 ዓ.ም ገጽ 168*

[229] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 152*

[230] *ጌታቸው ኃይሌ (ፕሮፌሰር) (1996 ዓ.ም) ፣ ደቂቅ እስጢፋኖስ፣ ገጽ 160*





## የአባ እስጢፋኖስ ሰማዕት መሆን

*"ሰማዕት"* የሚል ትርጉም የያዘው የእንግሊዝኛ ቃል፣ *(Martyr)* (ማርቲየር) ከላቲን የመጣ ሲሆን፣ ቀጥተኛ ትርጉሙ *"ምስክር"* መሆን ማለት ነው፡፡ የቀድሞ ክርስቲያኖች ኢየሱስ ጌታ መሆኑን ክደው ከመኖር ይልቅ *"ለሚያምኑትና ለተቀበሉት ሃይማኖት ምስክር"* ሆነው መሞት የመረጡትን አማኞች ለመግለጽ ለመጀመሪያ ጊዜ የተጠቀሙበት ቃል ነው፡፡[232] ፕሮፌሰር ኃይሌ የተሐድሶው ፋና ወጊ የነበሩ አቡነ እስጢፋኖስ ላይ የደረሰውን የመጨረሻ መከራና ሰማዕትነት በመጽሐፋቸው እንዲህ ዘግበዋል፡፡

*ቅዱሱንም (አባ እስጢፋኖስ) ፊቱን ወደ ላይ አቅንተው ሁለንተናው ደም በደም እስኪሆን ደበደቡት፡፡ የንጉሡ የግራ ወታደሮች ሲያዩ ከራሱ እስከ እግሩ በመደብደብ በቅዱሱ ላይ ተረባረቡበት፡፡ ንብ ማርን (እንደሚከብ) ከበቡት፡፡ ሰውነቱ አልበቃ ሲላቸው የመልኩ ውበት እስኪ ለውጥ ድረስ ግማሾቹና ግማሾቹ ተራ በተራ ተፈራረቁበት፡፡ በእሳት የጠበሱት እንጨት መሰለ፡፡ ከድብደባው እብጠት የተነሣ የጉንጩ ስፋትና የከንፈሮቹ ሥርዓት (በእብጠት) ከአፍንጫው ጫፍ ጋር እኩል ሆነ፡፡ ዓይኑ ማየት አልቻለም፡፡ ብቻ ደሙ ከድንኳኑ በር እንደ ውሃ ይወርድ ነበር፡፡*[233] *ቅዱሱንም (አባ እጢፋኖስ) ከወደቀበት ቦታ አመጡት፡፡ (ሲያመጡት) አጐንብሶ ነበረ የሚሄደው፣ ምክንያቱም በጢሙ ላይ የወረደው የአፍንጫውና የአፉ ደም ሲረጋ እንደ ገመድ ሆኖ ሳይበጠስ ከቀሚሱ ጋር ተያይዞ ነበር፡፡ ሲመቱት ቆቡን ጥለዋት ስለነበረ ራሱ ራቁቱን ነበር፤ ግን በልብሱ መገናኛ ቁልፍ ተይዞ ተንጠልጥላ ነበረ፡፡ ልጆቹ አስተካከሉት፤ ቆቡን ራሱ ላይ አደረጉለት፤ የደሙንም ገምድ ከጢሙ አስወገዱለት፡፡ ዐይኑ ግን ጠፍቶም እንደሁ ወይም እንዳለ ለመረዳት አልቻሉም፡፡*

## ቅዱሱም ልጆቹን እንዲህ አላቸው፡-

*አሁን ታዲያ በዚህ ታዝናላችሁን? ይኸ ድብደባ ብቻ ሳይሆን ስለ ክርስቶስ አጥንቴን ሁሉ እንኳን ቢበታትኑም እንደዚሁ እደሰታለሁ፡፡*[234]

---

[231] ይትባረክ ግደይ *(2000 ዓ.ም)* ፤*ዘረኛ ማነው? ኢትዮጵያውያን ፍረዱ፤* ገጽ 149

[232] *መለሰ ወጉ (ዶ/ር) (2004 ዓ.ም)፣ መስቀል-አልባ ክርስትና፣ ሕትመት ፋር-ኢስት ትሬዲ.ግ.* ኃላ.የተ.የግ.ማህ፣ ገጽ 133

[233] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 103

[234] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 104*

ያስገባ አደገኛ ፍልስፍና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ሰው ሰውን እንዲገድል አይፈቅድም። ከአሥርቱ ትዕዛዛት አንዱ *"አትግደል"(ዘፀ.20:13)* ይላል። ኢየሱስ በአዲስ ኪዳን፡- *"ለቀደሙት አትግደል እንደተባለ ሰምታችኋል፤ የገደለም ሁሉ ፍርድ ይገባዋል። እኔ ግን እላችኋለሁ በወንድሙ ላይ የሚቆጣ ሁሉ ፍርድ ይገባዋል" (ማቴ.5:21)* በማለት ለነፍስ ገዳይ ሳይሆን ወንድሙን ለሚቆጣ ሁሉ ፍርድ እንደሚገባው ገልጾአል። እንዲሁም ነፍስ ገዳዮች የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደማይወርሱ ቃሉ ይናገራል*(ራእ.22:15)*። *"ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ። እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅርን አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል" (1ዮሐ.4:16-17)*። በክርስቶስ ሞት በእውነት የዳነ ሰው ማንኛውንም ሰብዓዊ የሆነ ፍጡር ለመግደል አይነሣም። ታዲያ መንፈሳዊነታቸው በአንዳንዶች የሚመሰከርላቸው ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ከላይ በተመለከትነው አሰቃቂ ሁኔታ በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ውሸትን ያወገዙ የኦርቶዶክስ አባቶችን ለእግዚአብሔር እውነትና ለቤተ ክርስቲያን በመቅናት እንደገደሏቸው በኩራት ቢወሳላቸውም በእግዚአብሔር ቃል ግን ድርጊታቸው የተወገዘ ነው።

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ እንደዚህ የከፋና *መራራ* የመከራ መዓት ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ ሌላ ነገር በእጃቸው በሌላቸው የእምነት አበው ላይ ሲያደርስ ማን መርቷቸው ነው? ይህን ኢሰብዓዊና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እኩይ ድርጊት ሲያደርስ ቤተ ክርስቲያን ዝምታን ለምን መረጠች? ያለፈ ይቅር ካልን አሁን ባለንበት ዘመን ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ስለዚያ ክፉ ዘመን የሚጽፉ ብዙዎች የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን እንከን አልባ መሪና ታላቅ መንፈሳዊ ሰው ብቻ አድርገው በማቅረብ በእውነት ላይ መዋሸትን ለምን መረጡ? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ለአገር ያደረገው መልካም ነገሮቹ ሲጠቀሱ በኢትዮጵያ የኑፋቄን ትምህርት እንዳስፋፋና የእምነት አባቶችን በጭካኔ እንደ ጨፈጨፈም መገለጽ አለበት። ገዳይና ተገዳዮች በዚህ ዘመን ባይኖሩም ለተሳሳተ ድርጊት የመንፈሳዊነት ሽፋን ዛሬም እየተሰጠ ስላለ በቃሉ ገለባውን ከፍሬው ለይተን የራሳችንን እምነትና አቋም በቃሉ እንድንፈትሽና ካለፈ ታሪክ ዞር ብለን በማየት መማር እንድምንችል ይህ ታሪክ በሰፊው ተጽፎአል።

የዚህ መጽሐፍ ዓላማ በአፈ-ታሪክ ላይ የተመሠረተ ክርስትናችን ወደ ቃሉ እንድመለስ፣ ያለፈውን እሉታዊ ታሪክ በትክክል በመረዳት አዎንታዊ ታሪክ ለመሥራት እንድንነሳ፣ የጠራ ወንጌል ትውልዱ ዳግም እንዲያነሣ፣ የሰማይን ምሕረትና ፍቅር በምድራችን ተያይዘን ለማወጅና ምድራችንን ከእርግማን በንስሐ ለማጽዳት ነው። ስለዚህ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ አድናቂዎች ነን የሚሉ ሰዎች ለትምህርታችን ይሆን ዘንድ የእርሱን ኢ-ሰብዓዊ ድርጊት ሳይጠቅሱልን ማለፍ አልነበረባቸውም። ግማሽ እውነት ከውሸት ብላጫ የለውምና። ይህ በቀደምት አባቶቻችን ለኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የተከፈለ የደም ዋጋ ነው። ይህ ኢሰብዓዊ፣ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና በሰው






አዕምሮ ለማሰብ እጅግ የሚከብድ ጭካኔ በእግዚአብሔር ስም፣ *"አገረ እግዚአብሔር" "መሐሏ ገነት" "የክርስቲያን ደሴት"*...ወዘተ በማለት ስናቆላምጣት በፍጹም በማንሰለቸው አገራችን የተፈጸመ ህቡዕ ዘመን ዘለቅ አንገት የሚያስደፋ ታሪክ ነው። ለዚህ ንስሐ መግባት የለብንም ወይ? *"አለባበሰው ቢያርሱ ለአረም ይመለሱ"* በቆየ ብሂላችን እንደምንለው ይህን ለዓለም እርጌ ለእኛ ለባለታሪኮቹ አዲስ የሆነ የጭፍጨፋ ታሪክ ሌላ ስም ሳንሰጠው በእግዚአብሔር ፊት በመናዘዝ ለምድራችን ፈውስ በእውነት ንስሐ ልንገባ ይገባል። *"ምክንያት ሰነፎች ቤት ሲሠሩ የሚጠቀሙበት ሚስማር ነው"* እንደሚባለው ከንስሐ ውጭ ምክንያተ ብዙነት ይህን ዘመን ዘለቅ ቁስል አይፈውስም፤ ምድራችንም እንድትባረክ አያደርግም። ከላይ የተመለከትነው አሰቃቂና ዘግናኝ የመዓት ውርጅብኝ የጠራ እምነት በያዙት በአባ እስጢፋኖስ፣ በደቂቀ እስጢፋኖስና በሌሎች ሰማዕታት ላይ ቀርቶ እንደተባሉትም "መናፍቅ" ቢሆኑ እንኳ አይገባቸውም። አሳዳጆች መንፈሳውያን ቢሆኑ *"በእምነት የደከመውንም ተቀበሉት በአሳቡም ላይ አትፍረዱ" (ሮሜ.14:1)* ቃሉ እንደሚለው ባደረጉ ነበር።

## ከሰማዕታት ደም የተወለዱ ሰማዕታት

አባ እስጢፋኖስና የእርሱ ተማሪዎች የነበሩ ደቂቀ እስጢፋኖስ ከላይ እንደተመለከትነው ለሰው እንሰግድም፤ ለማርያምና ለመስቀል የአምላክ ስግደት ይገባቸዋል የተባለውን ኑፋቄ በቃሉ ላይ ቆመው በመቃወማቸው ሰማዕት ሆነው እንዳሸነፉ ታሪክ ይመሰክራል። ብዙዎች ይህን ታላቅ የእምነት ተጋድሎ በዓይናቸው ስላዩት ለሰማዕትነት ራሳቸውን በእምነት ሰጥተዋል፡-

## "ገድለ" እማሆ መክብዪ

*ደብረ ሰላም በሚባል ቦታ የምትኖር መክብዪ የሚሏት አንዲት መበለት ነበረች። እንግዳ ተቀባይ፤ በምግባሯም ጥሩ ነበረች። ወንድና ሴት ልጆች አሏት። ይኸንን ዓለም ለመተው ስትወስን ንብረቷን ከሦስት ከፈለችና ዘመዶቿን ከንብረቷ፡ " ሁለቱ እጅ ለልጆቹ ይሁን አንዱ እጅ የኔ ነው ዕዳ ቢመጣብኝ በልጆቼና በዘመዶቼ ላይ ሐዘን እንዳይመጣ ከሱ እሰጣለሁ" አለቻቸው። እሷ ግድ እንደሚመጣባት እያወቀች ቅዱሳኑን ከቤቷ ታስገባቸው አብራቸውም ለመሆን ትፈልግ ነበር። (ንብረቷን) እንደዚህ (የከፋፈለችው) ስለዚህ ነው። በዚህ ሥራ ዘመዶቿ ብዕዕት አደረጓት አደነቋትም። "ጥሩ ነው እንዳልሽው ይሁን" አሏት። ከዚህ በኋላ ቅዱሳኑን "መነኩሲት እንድሆን እፈልጋለሁ" አለቻቸው። "ታገሺ የምንኩስና ሥራ አስጨናቂና ጽኑ ነው ብዙ ሥቃይና ሲደት አለበት፡ እስከ መሞትም ያደርሳል" አሏት። "እግዚአብሔር ዐቅሙን ይሰጠኛል" አለቻቸው። ሁለቱም ሦስቱም ነገሯት፡ እሷም ያንኑ መለሰች። ወደነሱ ለሚመጣ ሁሉ ሥርዓታቸው እንደዚህ ነው። ከዚያ መንኩሳ በንጽሕ ሥርዓት ኖረች። ከዚያ በኋላ እንደነገሯት ደረሰባት። ቅዱሳን እና እሷንም ከቤቷ ያዟቸው። እሷም እንዳለችው አደረገች (ቀጣቷን) ለተላኩት ከገንዘቧ ሰጠች፤ ልጆቿን አላሳዘነችም። ወስደው ለብቻዋ አቆሟት።*

በአገራችን ባሉት አንዳንድ ድርሳናትና ገድላት ከተጻፈው ጋር ብዙ ይጋጫል:: ሐዋርያው ዓለም ሳይፈጠር በክርስቶስ እንደተመረጥንና እግዚአብሔር ይህን ያደረገበት ትልቁ ዓላማ የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ እንደሆነ ገልጾአል:-

> *ዓለም ሳይፈጠር በፊቱ ቅዱሳንና ነውር የሌለን በፍቅር እንሆን ዘንድ በክርስቶስ መረጠን:: በበጎ ፈቃዱ እንደ ወደደ በኢየሱስ ክርስቶስ ሥራ ለእርሱ ልጆች ልንሆን አስቀድሞ ወሰነን:: በውድ ልጁም እንዲያው የሰጠን የጸጋው ክብር ይመሰገን ዘንድ ይህን አደረገ:: (ኤፌ 1: 3-6)*

ሐዋርያው ጴጥሮስ በነገር ሁሉ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር ይከብር ዘንድ ይላል:- *ክብርና ሥልጣን እስከ ዘላለም ድረስ ለእርሱ በሚሆነው በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል እግዚአብሔር በነገር ሁሉ ይከብር ዘንድ አሜን:: (1ጴጥ.4:11) ሁሉን ለእግዚአብሔር ክብር አድርጉት (1ቆሮ.10:31)::* ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር እንጂ ለማርያም መስጠት እንደሚገባ መጽሐፍ ቅዱስ በፍጹም አይናገርም:: የጌታችን እናት ማርያም የአገራችን ድርሳናት የቀደመውን ቃሉን ቸል በማለት የሚሰጧትን ከንቱ ውዳሴ እንደማትቀበል የታወቀ ነው:: ከሁሉ በላይ በእግዚአብሔር የከበረችና የተባረከች የጌታ እናት የመጽሐፍ ቅዱስን ቃል በሚጋፋው በእኛ ተረት ቦታ ለማግኘት የምትታገል ሴት አይደለችም::

## በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈጠሩ የኑፋቄ ትምህርቶች?

*መምህር ጽጌ ስጦታ* የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የቅዱስ ጳውሎስ የከፍተኛ መንፈሳዊ ትምህርት ቤት ምሩቅ፣ በጎፋ መካነ ሕያዋን ቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል የስብከተ ወንጌል ኃላፊ፣ የወንጌል ሰባኪ፣ አስተማሪ ሆነው ያገለገሉና በቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ አስፈላጊነት ላይ ዳጎስ ያሉ ጥራዞች ያሏቸውን መጻሕፍት የጻፉ አገልጋይ እንደሆኑ ግለ ታሪካቸው ያወሳል:: ወጋገን (ገጽ 215 -216/ 2004 ዓ.ም ) በሚለው መጽሐፋቸው የዘርዓ ያዕቆብ ጉባዔ የወሰነው ውሳኔና የፈጸመው ስህተት በሚል አሳብ ሥር የሚከተሉትን ዘርዝረዋል::

*1. መስቀል ያማልዳል::*

*2. ለመስቀልና ለማርያም የፈጣሪ ስግደት ይገባቸዋል::*

*3. በክብራቸው ከፈጣሪ ጋር ተስተካክለዋል::*

*4. ዓለም የተፈጠረው እመቤታችንን ለማመስገን ነው::*

*5. አዳምና ሔዋንም እመቤታችንን ለማመስገን ተፈጠሩ::*

*6. ለሥዕል ስግደት፣ ውዳሴና ምስጋና ይገባል::*





*7. ለእመቤታችን ሥዕል የማይሰግድ ከቆመበት ሥፍራ ይጥፋ፤ ስም አጠራሩም አይታወቅ መላዕክትም አሜን ይበሉ::*

*8. 16ቱን ትዕዛዛት በመፈጸም የእግዚአብሔር ባሪያዎች ለመሆን አንሻ ይልቅስ የማሪያም ባሪያዎች ለመሆን እንሽቀዳደም::*

*9. የእመቤታችንን የ33ቱን በዓላት እንደ እሑድ ሰንበት አድርጎ የማያከብር ወልድ በጌትነቱ እስኪመጣ ድረስ የተረገመ ይሁን::*

*10. ለሕንጻ ቤተ ክርስቲያን ስግደት ይገባል::*

*11. መስቀል በአንገት ማሠር ይገባል::*

*12. በመስቀል ምልክት ማማተብ ሰይጣንን ያርቃል መንፈስ ቅዱስንም ያቀርባል::*

*13. ድርሳናትና ገድላትን ማንበብና መጸለይ ይገባል::*

*14. ከተነበበ በኋላ መሳሳምና መተሻሸት ያስፈልጋል::*

*15. በቅጽረ ቤተ-ክርስቲያን የሚገኝ ማንኛውም አፈር አመድ /እምነት/ ቅጠላቅል ውኃ ሁሉ ከማንኛውም ደዌ ይፈውሳል::*

*16. የእመቤታችንን ተአምር የሰማ ሥጋ ወደሙን እንደተቀበለ ይቆጠርለታል:: የሚሉትና የመሳሰሉት ሕገ ልቡናዎች የተሠሩበት ጉባዔ ነበር::*

ዘርዓ ያዕቆብ ካስተማረው ኢ.መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርቶች መካከል የ*"መስቀል"* ምልክት የእግዚአብሔር ስልጣንና ኃይል እንዳለው ብቻ ሳይሆን ስግደት እንደሚገባውና እንደሚያማልድ በገሃድ ማስተማሩና ዛሬም በብዙዎቹ መታመኑ ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ ለማን መስገድ እንዳለበት በግልጽ ተናገሯል:- *"ብላይ በሰማይ ካለው በታችም በምድር ካለው ከምድርም በታች በውኃ ካለው ነገር የማናቸውም ምሳሌ የተቀረጸውንም ምስል ለአንተ አታድርግ:: አትስገድላቸው አታምልካቸውምም" (ዘፀ.20:4-5):: "እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስና በእውነት ሊሰግዱለት ያስፈልጋቸዋል"(ዮሐ.4:24)::* የሚለውን ግልጽ አስተምህሮ ዘርዓ ያዕቆብ መተላለፍን ለምን ወደደ?

ለእንጨት መለኮታዊ ኃይል ማላበስና ልዩ ሃይማኖታዊ ጉልበት መጨመር የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ አይደለም:: መስቀል በራሱ የኃይል ምንጭ ሳይሆን የኃይል ሁሉ መሠረት የሆነ ጌታ የተሰቀለበት ነው:: መስቀል ኢየሱስ ክርስቶስ ስለተሰቀለበት ብቻ የኢየሱስ መለኮታዊነት ወይንም ልዩ ኃይል ተካፋይ አልሆነም:: የመስቀል እንጨት ቢሆንም የዓለም መድኃኒት በእርሱ ላይ በመሰቀሉ ልዩ ያደርገዋል:: ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ *"በዚህ የመስቀል ዘንግ ሐዋርያቱ ተዓምር ሠሩ፣ አጋንንት አባረሩ፣ ጣዖታትን ሰባበሩ"* በማለት በሐዋርያት ትምህርትና አገልግሎት ያልተጻፈውን አስነብቦናል:: በሐዋርያት አገልግሎት ተዓምር የተሠራው፣ አጋንንትን ከሰው ያስወጡት በመስቀል ዘንግ ሳይሆን በመስቀል ላይ በተሰቀለው በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ነው:: ሐዋርያው ጴጥሮስ ወደ መቅደስ ከሚገቡት ምጽዋት

ለሕትመት እንዲበቃ ፈቀደች? ዘርዓ ያዕቆብን እንደ ጻድቅ አባት በእርሱ የጭካኔ ፍርድ የተጨፈጨፉትን ደግሞ እንደ የቀደሙ የቤተ ክርስቲያኒቷ ሰማዕታት ተቀብሎ አንድ ላይ መዘከር ይቻላል ወይ? ቤተ ክርስቲያን የሁለቱን አስተምህሮ በቃሉ በመፈተሽ ያገኘችው ውጤት አለ ወይ? ሁለቱን አንድ ላይ ትክክል ነው ብሎ መያዝ እርስ በርስ የሚጋጭ ሐሳብ አይሆንም ወይ? የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን እንደተባለው ከዛሬ ስድስት መቶ ዓመታት ገደማ በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጠንሳሽነት በአባ እስጢፋኖስና በተከታዮቹ ላይ ለተፈፀመው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ጭፍጨፋ እጇን ካስገባችበት ግልጽ ይቅርታ መጠየቅ የለባትም ወይ? ዓለም ካወቀው ከ400 ዓመታት በላይ ለተቆጠረው እኛም በቅርቡ ለማወቅ ለበቃነው አስደንጋጭና ሰቀጣጭ ታሪክ ሁላችንም በእግዚአብሔር ፊት በወንጌል እውነት ላይ በቆሙት አባቶች ላይ በዚህ ምድር ስለተደረገው ግፍ ንስሐ ልንገባ ይገባል:: ኢትዮጵያ እንደ ዕድሜዋ አቅም እንዳይኖራት ውስጧን በልቶ የጨረሰ አንዱ እርግማን በእግዚአብሔር ለዕድገታችንና ለበረከታችን የተሰጡንን፣ ታላቅ የተሐድሶ ራእይ ይዘው የተነሡ አባቶችን *"ለእግዚአብሔርና ለቤተ ክርስቲያን እንቆናለን"* በማለት በጅምላ መጨረሳችን ነው:: ምሕረት ለምድራችን! ኢትዮጵያ ታላላቅ ልጆቿን በልታ ተጽዕኖ ፈጣሪ ልጅ አልባ ሆናለች::

## ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብና ማርያም

ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የማርያምን ስም ከኢየሱስ ስም በላይ ለምን አገነነ? በቅዳሴ ጊዜ ካህናት ቆመው ተአምረ ማሪያምን እንደ ወንጌል እንዲያነቡት ለየገዳሙ ልኮ፣ *ልጁን ወለተ ማርያም፣ ገብረ ማርያም ብሎ የሠየመ መንግሥተ ሰማያትን ይወርሳል፡፡(ተአምረ ማርያም፣ 12:41)* በማለት የማርያምን ልጅ ሞትና ትንሣኤ ዋጋ ቢስ አድርጓል::

ከላይ ያለው በዘርዓ ያዕቆብ የተገለጠው ክሂደት በመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ላይ የተደረገ አደገኛ የኑፋቄ ትምህርት እንደሆነ ለማመልከት የጠለቀ የነገረ መለኮት ዕውቀት አይጠይቅም:: ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማርያም በፍጹም የማይለውንና ለቃሉ ባዕድ የሆነውን አሳብ በድፍረት ማስተማር ምን አነሳሳው? ከአዳኙ በላይ ለእናቱ ልዩ ትኩረት ለምን ሰጠ? እርሱ ማርያም እያለ በሚጠራትና በጌታችን እናት መካከል ልዩነት ይኖር ይሆን? ዘርዓ ያዕቆብ ለማርያም ልዩ ትኩረት የሰጠበት አንዱ ምክንያት ሊሆን የሚችለው በፕሮፌሰር ጌታቸው መጽሐፍ የተገለጠው አሳብ ይሆን?

> *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የስለት ልጅ ነበረ:: እናቱ የፊተኛው ልጇ ስለሞተባት ያሁኑ ፅንሴ ተወልዶ በጤና ካደገ ለቅድስት ድንግል እመቤታችን እሰጠዋለሁ ብላ ተስላ እንደነበር ተጽፏል:: በእመቤታችን ዕርዳታ በሰላምና በጤና ስለተወለደ ለሷ ከፍ ያለ ክብር መስጠት ግዴታ የተሰማው ይመስላል::[277] ብለዋል::*

[277] ደቂቀ እስጢፋኖስ፣ ገጽ





መምህር ጌታቸው በመጽሐፉ ብዙ የአገራችን የኑፋቄ መጻሕፍት ጸሐፊዎች ማርያም ብለው የሰየሟት ከመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ጋር የስም መመሳሰል እንጂ አንድ እንዳይደለች ሲገልጽ፣

> *ጸሐፊዎች ማርያም እያሉ የሚጠሯት መጽሐፍ ቅዱስ ስለትህትናዋ ስለቅድስናዋ፣ ስለታማኝነቷ፣ እግዚአብሔርን ስለመፍራቷ የጻፈላትን የጌታችንን እናት ማርያም ነች ለማለት አያስደፍርም::[278] ዘርዓ ያዕቆብ ወደ ሩቅ ምሥራቅ ሄዶ እንደነበር የታወቀ ነው:: አንዳንድ ምሁራን በምድራችን ዛሬ እንደ አሸን የፈሉ የአምልኮ ስዕላትና ቅርጻቅርጾች ንጉሡ ከዚያ እንዳመጣ ይገልጻሉ:: በሩቅ ምሥራቅ ያሉ ኢአማኒያን የሚያመልኳትና የሚያጥኑላትን "የሰማይ ንግሥት" የምትባለው ሴት ምሥል ዛሬ በአገራችን በጌታችን እናት ስም አስመስለው ድንግል ማርያም እያሉ የሚሰግዱላትን የሚያጠኑላትን ምስል በመልክና በቅርጽ ተመሳስለው መገኘትን ነው:: የሚገርመው የእኛዎችም ሰዎች ይችን ስዕል "ንግሥት ሰማይ ወምድር" በማለት መጥራታቸው ነው::[279] ብሏል::*

አባ እስጢፋኖስና ተከታዮቹ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮን በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው የተጋፈጡ ሲሆን በደስታ ለወንጌል እውነት ሰማዕት ሆነዋል:: ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ክፉ ክሂደቱን በምድራችን ሲዘራ፣ የኑፋቄ ትምህርት ያለ አንዳች ከልካይ ሲያስፋፋ፣ የቀደሙ የኦርቶዶክስ የእምነት አባቶችን ደም በከንቱ ያለ ርህራሔ ሲያፈስ፣ አፍቅሮተ ንዋይ ልባቸውን የጋረደና አድርባይ ሥልጣን ፈላጊ ደብተራዎች አጀብ እንደነበረው መዛግብቶች ያወሳሉ:: በተቃራኒው:-

> *ዘርዓ ያዕቆብ በገንዘብና በሹመት አባብሎም ኸነ በሥቃይ አስፈራርቶ ከደቂቀ እስጢፋኖስ አንዱን እንኳ ሐሳቡን ለማስለወጥ ባለመቻሉ ተደንቋል፤[280]* ይላል::

የኢትዮጵያ አንዱ ያለመባረክ ምክንያት በእግዚአብሔር ስም እንዲህ ያለ ዘግናኝ ጥፋት በዚህ ምድር መደረጉ ብቻ ሳይሆን በዚህ ጉዳይ ላይ በእውነት ንስሐ ያለመግባታችንና አንዳንዶቻችን ለዚህ ለፈጠጠው ኢሰብዓዊና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊት ዛሬም ጥብቅና ለመቆም መዳዳታችን ነው:: እግዚአብሔር ምሕረትን እንዲያወርድልን ንስሐ እንግባ:: የሚገርመው ነገር የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን ዘግናኝ የጭፍጨፋ ድርጊት ዛሬም በደፈናው የሚደግፉና ሥራው ፍጹም እንደነበር የሚሟገቱ ሰዎች መኖራቸው ነው:: መምህረ ኪዳነ ማርያም ጌታሁን በመጽሐፉ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን *"ጻድቅና ታላቅ ንጉሥ"*[281] *"ደግ ንጉሥ"*[282] ብሎ ስለጽድቁ ከመሰከረለት በኋላ አንዳች ነውርና የሚያስነቅፍ ነገር በእጁ እንዳልተገኘ ሲመሰክር:-

[278] መምህር ጌታቸው(ስመ ጥምቀቱ ገብረ ኢየሱስ) *(1995 ዓ.ም)፣ገድል ወይስ ገደል? ገጽ 32*
[279] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 47*
[280] *ገድለ አቡነ እስጢፋኖስ ዘጉንዳጉንዶ፣ 1996 ዓ.ም ገጽ 25*
[281] ኪዳነ ማርያም ጌታሁን *(1993 ዓ.ም)፣ ፣ አመቻ ፊልጶስ ምልምል ቅጥረኞች ፀረ ማርያሞች አታወናብዱን*፣ ክፍል አንድ፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 9
[282] ጌታቸው ዓለሙ (ሻምበል)*(2001 ዓ.ም)* ገጽ 193

*ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በዘመነ መንግሥታቸው አስገደዱ፣ አሳደዱ፣ አስገደሉ የሚል ታሪክ አልተጻፈባቸውም፣ እንኳን ዓለም የሚያውቀው ይቅርና አካባቢ የሚያውቀው ነውር ነቀፋ የላቸውም*[283] ብሏል።

መምህሩ ከአገር ቤት አልፎ ላለፉት 400 ዓመታት ለምዕራቡ ዓለም በቋንቋው ተተርጉሞለት ያነበቡትንና በቅርቡም ፕሮፌሰር ጌታቸው ከግዕዝ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ የታተመውን "ደቂቀ እስጢፋኖስ" የሚለውን መጽሐፍ አንብቦ ይሆን? ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ስለሠራው መልካም ሥራ ሙገሳ የተገባ ሲሆን የእግዚአብሔርን ቃል በመያዝ የእርሱን የኑፋቄ ትምህርት የሞገቱትን አበ እምነቶችን እጅግ ዘግናኝና ኢሰብዓዊ በሆነ ሁኔታ አሰቃይቶ እንደገደላቸው መዘለል የለበትም። ይህን በብዙ መረጃ የተረጋገጠውን እውነት ዓይኔን ግንባር ያድርገው ብለን ከካድን ለዚህች አገር ዘመን ዘለቅ ችግር ባለመፍትሔዎች አንሆንም። ለመሆኑ የተሐድሶ ባለ ራእዮችን በመግደል የተሐድሶን ሃሳብ መግደል ይቻል ይሆን? የደቂቀ እስጢፋኖስ ጥያቄ ከአራት መቶ ዓመት በኋላ በ21ኛክፍለ ዘመን በምድራችን ላለችው ቤተ ክርስቲያን ዛሬም አውራ ጥያቄ አይደለም ወይ?

## ሌሎች ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ምን አሉ?

በኢትዮጵያ የነገሥታት ታሪክ ውስጥ ዘርዓ ያዕቆብ የገዛበት ዘመን (1426-1460 ዓ.ም) አሳፋሪና ዘግናኝ ከሚባሉት ዘመናት አንዱ እንደነበረ አንዳንድ ምሁራን ይገልጻሉ። *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የነገሡባቸው ሠላሳ አራት ዓመታት ለኢትዮጵያ ሕዝብ የልቅሶና የዋይታ ጊዜያት ነበሩ ማለት ይቻላል።*[284]

ፕሮፌሰር ታደሰ ታምራት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፡-

> *አምባገነን ነበረ...ወጥ የሆነን ሃይማኖት ለመፍጠር ካለው መነሣሣት የተነሣ ጠጣር የሆኑ ሕጎችን በሕዝቡ ላይ ተጠቅሟል፤፤*[285] *የሃይማኖት ብሔርተኝነትና ፈላጭ ቆራጭ የፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም በአንድ ላይ በመቀየጥ በሥሩ ያሉትን በማስፈራራት የገዛ*[286]

በማለት ዘርዓ ያዕቆብ የሃይማኖት አሀዳዊነት በአገሪቷ ለማስፈን ጠጣር ሕግ በሕዝቡ ላይ የተጠቀመ ፈላጭ ቆራጭ መሪ እንደነበር አስቀምጠዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በወንጌል ስብከት እንጂ ማንም በልዩ ሕግና በጉልበት የሰዎችን አቋም እንዲያስለውጥ አያዝም። የክርስትና መሠረት የሆነው ክርስቶስ፣ ከእርሱ የተማሩ ሐዋርያትና የቤተ ክርስቲያን አባቶች ወንጌልን በኃይል አላስፋፉም፣ የሰዎችን ውሳኔ በኃይል አላስቀየሩም።

[283] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 12*
[284] *የአቡነ እስጢፋኖስ፣ የደም ድምፅ!!! ገጽ 29*
[285] Tddesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 1270-1527*(Oxford, 1972), p.240
[286] *Ibid,pp 238-42, 284-85*





እንደዚሁም በፍጹም አላስተማሩም። ክርስትናን በሚመለከት ዋና አስተማሪ፣ መካሪ፣ መንገድ አመልካች፣ ሰባኪ የሆነች ቤተ ክርስቲያን በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጉዳይ ለምን ዝምታን መረጠች? መጥምቁ ዮሐንስ ንጉሥ ሄሮድስ የወንድሙን ሚስት ሲቀማ "አይገባህም" የሚል የግሳጼ ድምፁ ከምድረ በዳ በቤተ መንግሥት እንደተሰማ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ የፈለገውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ሲያስተምርና ቃሉን ይዘው የቆሙትን የእምነት አባቶችን ለክርስትና በመቅናት ሲገድል ይህ አግባብ አይደለም፤ ብላ ለምን አልሞገተችውም? ዲያቆን ጽጌ ስጦታ "ይነጋል" በሚል መጽሐፉ ስለ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ሲገልጽ፡-

> *ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ፀረ ወንጌል አቋም በመውሰድ ቤተ ክርስቲያን በጭንቅ አምጣ የወለደቻቸውን እንቁ ልጆቿን አይቀጡ ቅጣት ቀጣቸው። ቤተ ክርስቲያንንም ልጅ አልባ በማድረግ በምትኩ እርሱን ጨምሮ የአጋንንትን ትምህርት እየደመጡ፣ ከመናፍስት ጋር የሚያቆራኘውን ክፉ ትምህርት ያለ ከልካይ አስገባ።* [287]

እንደ ዲያቆን ጽጌ ከሆነ፡-

> *ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ ከሐዋርያት ያልተገኘ ትምህርት በአቀንቃኝ ደብተራዎች ታግዞ ወደ ቤተ ክርስቲያን ያለ ከልካይ በገፍ አስገብቶታል። ይህም በሆነበት ወራት ዳግማዊ እስጢፋኖስ በትግራይ ክፍለ ሀገር ነጥር ያለውን ያልተበረዘውን የሐዋርያትን ትምህርት በማስተማር ጥቂት ከማይባሉ ደቀ መዛሙርት ጋር ወደ መሐል አማራ ገሰገሰ። ከሐዲው ዘርዓ ያዕቆብ ያስተላለፈውንም እንግዳ ትምህርት አወገዙ። ብዙ ምዕመናን ተከተሉ።*[288] ብሏል።

አንዳንድ የአገራችን ጸሐፊዎች ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ በፖለቲካው ስለተጫወተው አዎንታዊ ሚና፣ ለሥነ ጽሑፍ ዕድገት ያበረከተው አስተዋጽኦና ቤተ ክርስቲያን ማስፋፋቱ ገንቢ እንደነበር በሰፊው ጽፈውለታል። ይህን ማድረጋቸው መልካም ነው። ለዚህም ሊመሰገኑና አክብሮት ሁሉ ሊቸራቸው የተገባ ነው። ነገር ግን በሃይማኖት ስም ምድሪቷን በሰው ደም እንዳጨቀየና የኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትምህርት ዘር በምድሪቷ እንደዘራ ለትምህርታችን መግለጽ ነበረባቸው።

ስለቤተሰባዊ ሕይወቱና አንዳንድ ድርጊቱ ማጤን ስለ ክርስቶስ፣ ስለ ክርስትና ትምህርትና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የነበረውን መረዳት እንድናውቅ አንዳንድ ፍንጭ ይሰጠናል። የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ታሪክና በክርስትና ስም በምድራችን የፈጸመውን ዘግናኝ ድርጊት እኛን ብቻ ሳይሆን ዓለምን ካነጋገረ ውሎ ሰንብቷል። *"ጆሮ ለራሱ ባዳ ነው"* እንደሚባለው በዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ዘመን የተፈፀመው የሰማዕታት ታሪክ *"ደቂቀ እስጢፋኖስ"* በመባል የሚታወቅ ሲሆን ይህ ታሪክ ከግማሽ ሚሊኒየም በላይ ያስቆጠረ የቆየ ታሪክ

[287] *ጽጌ ስጦታ (ዲያቆን) (1997 ዓ.ም)፣ይነጋል፣ ገጽ 63*
[288] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 59*

በተከታዩ ዓመት ማለትም በኖቨምበር 1882 ዓ.ም ታዬ ቅኔ ለመቀኘት ፊታቸውን ወደ በጌምድር መለሱ:: ምርምራቸውንም ዕውቅና ባላቸው በተለያዩ አድባራትና ገዳማት ካጠናቀቁ በኋላ "አለቃ" የተሰኘውን ከፍተኛ ማዕረግ አገኙ::[87]

*አለቃ ታዬ ከፊል ትምህርታቸውን ከውጪ አገር መምህራን ዘንድ በመቅሰማቸው፤ አንዳንድ የቤተ ክህነት ሰዎች ተቃውሞ ያነሱባቸውና ያስነሱባቸው ነበር::[88] ፀሐፊ ትዕዛዝ ገብረሥላሴ እና አቡነ ማቴዎስ ከፍተኛ በደል እንደፈፀሙባቸው የሰሙ ዐፄ ሚኒልክ ባለሟላቸውን (ፀሐፊ ትዕዛዝ) ገብረሥላሴ በእጅጉ ገስጸዋቸዋል:: ለአቡኑም ቢሆን አለቃ ታዬን በማይረባ በማንገላታታቸው ቅሬታቸውን በይፋ ገለጹላቸው::[89]*

ያም ቢሆን ንጉሡ አለቃ ታዬን ከወህኒ፣ ከመከራና ከገዳዮች እጅ ማስጣል አልቻሉም:: ይህም በአገራችን የአሳብ ነፃነት በፍጹም እንዳልነበረና እግዚአብሔር ለሰው ልጅ የሰጠውን የአሳብ ልዕልና ቤተ ክርስቲያን በመደፍጠጥ ቀዳሚ እንደነበረች የአለቃ ታዬ መከራና ሞት ተጨባጭ ማስረጃ ነው:: ለአለቃ ታዬ ንጉሥ ሲራራላቸው አንዳንድ የቤተክህነት ሰዎችና አቡኑ ለምን ጨከኑባቸው? አለቃ ታዬ ይደርስባቸው የነበረውን ተቃውሞና በደል ለንጉሡ በማመልከታቸው ዐፄ ሚኒልክ እንዲህ የሚል ደብዳቤ ጽፈውላቸው ነበር:-

*ሞአ አንበሳ ዘእምነገደ ይሁዳ ዳግማዊ ሚኒልክ ሥዩመ እግዚአብሔር ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ፣ አለቃ ታዬ ገብረማርያም የሚባል ሰው ምጽዋ የነበረ ሃይማኖቱን እኛ መርምረነዋልና ማንም አንዳች አይበለው በሃይማኖቱ ነገር:: [90]*

ስለ አለቃ ታዬ ካህናት፣ አቡን፣ የንጉሥ ጸሐፊ የነበሩ ወንጌልን በመናገራቸው ቢቃወሟቸውም አንዱም የሚያስተምረው ትምህርት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደሆነ ከመጽሐፍ ቅዱስ በማጣቀስ የረታቸው አንድም ሰው በሕይወት ዘመናቸው እንዳልተገኘ ታሪካቸው ይናገራል:: የእግዚአብሔርን ቃል እውነት በመኖር የወንጌልንም ቃል በገሃድ ቢናገሩም ከመከራና ከእስራት ማምለጥ አልቻሉም:: የካቲት 25 ቀን 1961 ዓ.ም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ *"ምን ሠርተው ታወቁ"* በተሰኘው አምዱ የመረጣቸው ከቀዳሚ የአገራችን ምሁራን መካከል አንዱ አለቃ ታዬ ነበሩ:: ስለ እርሳቸው ሲናገር:-

*እንደ ዛሬው ኤ.ቢ.ሲ.ዲ. የቆጠረው በመቶ ሺህ ሳይቆጠር፣ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰርና ዶክተር ሳይገኝ፣ አለቃ ታዬ የዐሥራ ዘጠነኛው ዘመን ኢትዮጵያዊ ምሁር ነበሩ:: ሙያቸውና ችሎታቸው በአንድ መሥመር ብቻ የተወሰነ አልነበረም:: በአንደበታቸው የሚመስጡና ልብን የሚማርኩ የክርስቲያን*

---

[87] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 61*
[88] *ፍጹም ወ/ማርያም (2005 ዓ.ም)፣ ያልተዘመረላቸው፣ ህትመት ፋርኢስት ትሬዲንግ፣ ኃላ.* የተ. የግ. ማህበር፣ ገጽ 46
[89] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 67*
[90] *ህዳር 6 ቀን 1891 ዓ.ም በወረኢሉ ከተማ ተፃፈ (ኃይሉ ከበደ(1963 ዓ.ም) ገጽ 3*





*ሃይማኖት ሰባኪ፣ የሚራቀቁ ደራሲ፣ የሚመራመሩ ታሪክ ጸሐፊ፣ ስለ ኀሊና ነጻነት ተከራካሪ፣ ከውጭ አገር ተበትነው የነበሩትን የኢትዮጵያ መጻሕፍት ሰብሳቢ ነበሩ:: በቤተ መንግሥት የተከበሩትን ያህል በወኅኒ ቤት ማቀዋል:: የተወደዱትን ያህል ብዙ ጠላቶችም ተነሥተውባቸዋል::*



**አለቃ ታዬ ገብረማርያም/1853 - 1916 ዓ.ም/**

ምንጭ:- ጮራ መጽሔት ቁ.40. 2003 ዓ.ም

ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መልስ ያላገኘ ዘመን ተሻጋሪ ጥያቄ እንጂ ሚሲዮናውያንን ተከትሎ የመጣ *"መጤ"* ጥያቄ አይደለም:: ይህ ትውልድ የተሐድሶ ጥያቄ በቃሉ ላይ ቆሞና ከቀደምት አባቶች ተቀብሎ እንጂ በራሱ ፈጥሮ እያስታጋባ አይደለም:: የወንጌል መልዕክተኞች ወደ ሀገራችን ሳይመጡና ወንጌላውያን የሆኑ አብያተ ክርስቲያናት በተለምዶ ፕሮቴስታንት የሚባሉ ሳይመሠረቱ የተሐድሶ ጥያቄ በአገራችን ነበር:: ከዛሬ መቶ ዓመት በፊት በቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ/የለውጥ ሀሳብን በገሃድ ካነሡት ፋና ወጊ የአገራችን ምሁራን መካከል አለቃ ታዬ አንዱ ነበሩ:: በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተምረው ያደጉና በእውነት ላይ ቆመው እውነትን በራስ በመወራረድ አንዳች ሳይፈሩ በገሃድ የገለጡ የእምነት ሐዋርያ እንደነበሩ ቅን ልቦና፣ ሚዛናዊ አዕምሮና የማርን ጣፋጭነት እያወቁ እሬት ነው ለማለት ሕሊናቸው ፈቃድ ለማይሰጣቸው ኢትዮጵያውያን ሁሉ የአደባባይ ምስጢር ነው:: በኢትዮጵያ ባለፉት ዘመናት በእውነት ላይ በመቆማቸው ያለ ፍትሕ የሥርዓቱ ሰለባ የሆኑ ኢትዮጵያውያንን ለመቁጠር የሚቻል አይመስለኝም:: አንዳንዶች ለዚህች አገር አንድነት፣ ዕድገትና ለውጥ ላበረከቱት መልካም ሥራ ትልቅ አድናቆት የተቸራቸው አሉ ሌሎች ደግሞ ተረስተዋል::

እንዲሁም ከሁሉ በላይ አንፀባራቂ ሥራ የሠሩትን ጥቂቶች ሲያሞግሷቸው በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ከሃዲ የሚቆጠሩና ሞተው እንኳ የሚወገዙ ታላላቅ ሰዎችም አልታጡም። ከእነዚያ መካከል አለቃ ታዬ አንዱ ናቸው። የብዙዎች ዓይን ገና ባልበራበት ዘመን "የአሥራ ዘጠነኛው ዘመን ኢትዮጵያዊ ምሁር" የሚል ቅጽል ስም ወጥቶላቸው ነበር። የዘመኑን የግብፅ ጳጳሳት የበላይነት፣ በቤተ መቅደስ የተንሰራፋውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንደ አባ እስጢፋኖስና ተካታዮቹ በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመቆም በግልጽ የሞገቱና ለእውነት ራሳቸውን የሰጡ ታላቅ ሰው ነበሩ፡-

*ኣለቃ ታዬ የተቃውሞ ትምህርት ያስተምራሉ በሚል በጳጳሱ ፊት ቀረቡ። ስለተከሰሱበት ነገር ራሳቸውን መከላከል ሲጀመሩ ጳጳሱ በቁጣ አቋርጠዋቸው አንተ አህያ ሃይማኖትህ ምንድነው? ሲሉ ዘለፏቸው። እርሳቸውም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ የተሾሙትን ግብጻዊ ጳጳስ በክርስቲያናዊ እምነታቸው ላይ እንዲቀልዱ ባለመፍቀድ፡- በርግጥ እኛን የማይረቡ አህዮች ያሰኘን እኮ በቤተ ክህነታችን ላይ እንደ እርስዎ ያሉትን ባዕዳን መሸከማችን ነው[91] ብለዋል።*

አለቃ ታዬ ከጀርመን መልስ የኢትዮጵያ የክብር ኮከብ ኒሻን ከዐፄ ምኒሊክ ተሸልመው በትውልድ ቀያቸው ጉልት ተቀብለው ሥራቸውን ቀጠሉ። ደጃዝማች መሸሻ ወርቄ በቅናት ተነሣስተው የአለቃ ታዬን ጉልት ግሚሱን በኃይል ከነጠቁ በኋላ ቀሪውን ደግሞ ለመጠቅለል አስበው በጊዜው የበጌምድር ገዢ ለነበሩት ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ እንዲህ ብለው ጻፉ፡- *"ኣለቃ ታዬ ሃይማኖቱ ንስጥሮስ ነው፤ ይህን ሃይማኖት ለሕዝብ ያስተምራል።"* ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ ቁጣና ብስጭት በተሞላበት መንፈስ እንዲህ ብለው ለአለቃ ታዬ ላኩ፡-

*የተላከ ከራስ ወ/ጊዮርጊስ ይድረስ ለአለቃ ታዬ እንዴት ሰንበተሃል? እኔ እግዚአብሔር ይመስገን ደህና ነኝ። ዝም ብለህ ተቀመጥ ስንልህ እንደዚህ ያለ ትምህርት ከየት ያመጣኸው ነው? በምን ተጣላኸኝ እንዳትል። በ1903 ዓ.ም ኅዳር 24 ቀን ተጻፈ።*

ደብዳቤው እንደ ደረሳቸው ሃይማኖታቸው ተዋሕዶ መሆኑንና የተፈጸመባቸው ግፍ ተገቢ እንዳይደለ ለንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ በመግለጽ የተወሰደባቸውን መሬት እንዲያስመልሱላቸው ጠየቁ፤ ንጉሡም ደጃዝማች መሸሻ ወርቄን አስጠርተው የወሰዱባቸውን ጉልት ለአለቃ ታዬ እንዲመልሱላቸው ፈረዱ። ሁኔታው ያልተዋጠላቸው ደጃዝማች መሸሻም፣ ታዬ *"ሃይማኖቱ ፀረ ማርያም"* ነውና አገር መግዛት አይገባውም በማለት ሌላ ክስ ከፈቱበት።[92] ንጉሥ ወ/ጊዮርጊስ ጉዳዩ ሃይማኖት ነክ በመሆኑ ታኅሣሥ 24 1903 ዓ.ም ክሱን ወደ አቡነ ማቲያስ መሩት። ጥር 28 1903 ዓ.ም በዋለው ጉባኤ አለቃ ፈለቀ ከሳሽ ሆነው በመቅረብ *"ኣለቃ ታዬ*

[91] *ጮራ መጽሔት ቁጥር 40 ታህሣሥ 2003 ዓ.ም ገጽ 13-14*
[92] *ደማቆቹ ገጽ 67*





*ለስዕልና ለመስቀል አይሰግድም፤ በሞቱ ቅዱሳን አማላጅነት አያምንም፤ ዝክርና ምዕዋት፣ የሞተ ሰውን ሊያጸድቅ እንደማይችል ይናገራል፤ የልማድ ጾም ዋጋ እንደሌለው ይሰብካል፤ ቀናትን አያከብርም"* ስሉ የክሱን ጭብጥ አብራሩ። ጉባኤው በክሱ በጭብጥ ላይ በብርቱ ከተወያየ በኋላ አለቃ ታዬን ለወደፊቱ ይህን ትምህርት እንዳያስተምሩ አስጠንቅቀው ቢያሰናብቱም በአለቃ ታዬ መለቀቅ የተበሳጩ ካህናት በወቅቱ ለዐፄ ምኒልክ ባለ ሙሉ ስልጣን እንደ ራሴ ለነበሩ ለራስ ተሰማ በማመልከት ያለ ሕግ ከታላቁ ወኅኒ ቤት እንዲገቡ አደረጉ። ለመሆኑ አለቃ ታዬ ለግዞት የዳረጋቸው *ለሥዕልና ለመስቀል እንድንሰግድ፣ የሞቱ ቅዱሳን እንደምያማልዱ፣ ዝክርና ምጽዋት የሞተን ሰው እንደሚያጸድቁና የልማድ ጾም ዋጋ እንዳለው* በየትኛው *መጽሐፍ* ቅዱስ ነው የተጻፈው? ከዚህ የሚረዳው አለቃ ታዬ ፍዳን ያዩት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ቆመው ነባሩን ልምድ ስለ ሞገቱ ነው።

እኚህ ታላቅ ምሁር በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቃሉ ብርሃን ጨለማን መግለጥ ሲጀምሩ *"ኣለቃ ታዬ የሃይማኖት ፀረ ማርያም ነውና አገር መግዛት አይገባውም፤ ፀረ ማርያም አይደለሁም ካለ ሥዕለ ማርያም ይምጣለትና ይስገድ"* ሲባል (ዘጸ.20፡1-6) በመጥቀስ ለሥዕል አልሰግድም ሲሉ ወደ ወህኒ ቢያወርዷቸውም አቋማቸውን እንዲህ ብለው በስንኞች ቋጥረዋል ፡-

## *"እኔ ለአምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድም!"*

*ይከራከሩኛል እየተጋዙ፣*
*በከንቱ ላይረቱኝ አምላክን ሳይዙ።*
*ወህኒ በመግባቴ በጣም ደስ ብሎኛል፣*
*አምላኬ በእኔ ስም ተመስግኖልኛል፣*
*ለወንጌሉ ስብከት ጊዜው ኢጋጥሞኛል።*
*መናፍቅ ነው ቢሉኝ እኔ ምን ዕዳዬ፣*
*ውዳሴ ከንቱ ነው ከሰው ምስጋናዬ*
*አንተ ሁነኝ እንጂ በነፍስ በሥጋዬ*
*ታምኜብሃለሁ አትጣለኝ ጌታዬ።*
*አንኳን በእግር ብረት ቢያገቡኝ በግንድ፣*
*ከቶ ምንም ቢሆን እውነትን አልክድ፣*
*መጨመር ነው እንጂ ከሳት ላይ ባሩድ፣*
*የተሰወረውም እንዲሆን ገሃድ፣*
*እኔ ለአምላክ እንጂ ለሥዕል አልሰግድ።*

*እየቀዘቀዘ ጠፋ:: ስለዚህ ጉዳይ ጃንሆይ አስበውበት እንዲህ ያለው ስድብ ሁሉ ባዋጅ እንዲከለከል ... ሰዎች እንዲከበሩ ቢያደርጉ ... በሌላ መንግሥት ስምና መልክ የተቀረፀ ገንዘብ ከመገበያየት በጃንሆይ መልክና ስም የተቀረፀበት ገንዘብ እንዲወጣ ቢያደርጉ ነፃ መንግሥትም ራሱን የቻለ የተሟላ ይሆናል...*

ኃይሉ ከበደም በመመረቂያ ጽሑፋቸው አለቃ ታዬ ጀርመን ሆነው ለንጉሥ ስለጻፉት ደብዳቤ እንደሚከተለው ገልጸዋል፦ *በየዕለቱ አዲስ ነገር አያለሁ፤ አዲስ ነገር እሰማለሁ:: ...ይህን አይቼ ለአገሬ መንግሥት ቅንዓት እንደእሳት በላኝ:: ምግኮ አደረጋለሁ? አዝኜ ወደ መቃብር እወርዳለሁ*[97] በማለት ከአውሮፓ ወደ አገር ቤት የሰደዱት ደብዳቤ አለቃ ታዬ ለአገራቸው ክብር፣ የኢኮኖሚ ብልጽግና የሥራ ባሕል ለውጥ የነበራቸውን ተቆርቋሪነት አመልካች ነው::

## የአለቃ ታዬ ተቀባይነት ማጣት

ለአገሩ ዕድገትና ብልጽግና ተቆርቋሪና በእግዚአብሔር ቃል ላይ በመቆም በዘመኑ የነበረውን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮና ልምምድ በገሃድ የሞገቱት አለቃ ታዬ በትልቅ መከራና መገፋት ውስጥ እንዳለፉ ታሪካቸው ያወሳል:: ታዋቂ የኢትዮጵያ ምሁር ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ ስለ አለቃ ታዬ ሲናገሩ፦

> *እስከ ዛሬ ድረስ እሩቅ አገር ተሰደው ወይም ወደ አበሾች ከመጡት ፈረንጆች ጥቂት ጥበብ ተምረው ያገራቸውን መንግሥት ሊጠቅሙ የሚፈልጉ ወንድሞቻችንን መናፍቃን፣ የሌላም መንግሥት ሰላዮች እየተባሉ ሲራቡ፣ ሲከሰሱም እናይ የለምን? እነዚያን መከረኞች ስም ሰንት ብለን እንቁጠረው? የሚከተሉት የሁለት ሰዎች ስም እንዲወሱ የግድ ነው:: እነርሱም ከንቲባ ገብሩና አለቃ ታዬ ናቸው:: ሦስት ዓመት ሙሉ አዲስ አበባ ላይ ስቀመጥ እንደእነዚህ ሁለት ሰዎች አድርጐ መንግሥቱን የሚወድ ሰው አላየሁም:: ይህ ደግነታቸው ግን እስከ ዛሬ ድረስ አልታወቀላቸውም ይመስለኛል:: እጅግ ያሳዝናል:: የእነርሱን ዕድል ያየ ሰው የኢትዮጵያ መንግሥት ለወዳጅ አይጠቅምም ብሎ ይቆርጣል::*[98]

## የአለቃ ታዬ ዜና ዕረፍት

*"ቢከፋ ቢደሰት ሁሉም በሞት ያልፋል*

*የመልካም ሰው ዝና ታሪኩ ይተርፋል::"*

[97] ኃይሉ ከበደ (1963 ዓ.ም)፣ የአለቃ ታዬ ገብረማርያም የሕይወት ታሪክ፣ አዲስ አበባ፣ አ.አ.ዩ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ (ያልታተመ)
[98] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 26





ተብሎ የተገጠመላቸው ለአለቃ ታዬ ነበር:: የታሪክ ምሁሩና ጸሐፊ አለቃ ታዬ በ1916 ዓ.ም ሲሞቱ በአዲስ አበባ ሥላሴ ቅበሩኝ ብለው ከመሞታቸው በፊት እንደተናገሩ ይነገራል:: መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ *"የሃያኛው ክፍለ ዘመን መባቻ"* በሚለው መጽሐፋቸው በአለቃ ታዬ ቀብራቸው ላይ ተገኝተው የታዘቡትን እንዲህ ዘግበዋል፦

> *ቤተሰቦቻቸውና ወዳጆቻቸው ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄደው ካህናቱን ፍትሐት ፍቱልን ቢሏቸው አንፈታም አሉአቸው:: ቀባሪዎችም መቃብር ለመቆፈር ቢጀምሩ ካህናቱ በደወል ተሰበሰቡና "ይህ ጸረ ማርያም፤ በቤተ ክርስቲያናችን አይቀበርም" ሲሉ አምባገሮ አንሥተው ከለከሉ:: ...በእምቢታቸው ስለ ጠነከሩ የአለቃ ታዬ ሬሣ ወደ ጉለሌ ተወስዶ በፕሮቴስታንቶች የመቃብር ሥፍራ ተቀበረ::... የዚህ ታሪክ ጸሐፊ የአለቃ ታዮን ሞት ሰምቶ ለማስቀበር ወደ ሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ሄዶ ነበርና አምባጓሮው ላይ ደርሶ የነገሩን ሁኔታ ተመልክቷል:: ካህናቱ ከፉኛ ተቆጥተው መቋሚያ ይዘው ለጥል ተሰልፈው ነበር*[99] ብለዋል::

ካህናቶቹ መቋሚያ ይዘው ለጥል የተሰለፉት ከማን ጋር ለመግጠም ይሆን? ከአፈር የተሠራው የሰው ሥጋ ሲሞት ወደ አፈር መመለሱ እንጂ በኦርቶዶክሶችና በፕሮተስታንቶች የቀብር ቦታ መቀበር በሟቹ ላይ አንዳች ለውጥ እንደሚያመጣ መጽሐፍ ቅዱስ ምንም ፍንጭ አይሰጥም:: የአንድ ሰው አስክሬን በልዩ አጀብ በክብር ወይም በውርደትም ቢቀበር፣ ሳይቀበር በስብሶ ወደ አፈርነት ቢለወጥ ወይም በእሳትም ቢቃጠል፤ በሕይወት እያለ በጌታ ያመኑ ለዘላለም ከጌታ ጋር ለመኖር ያላመኑ ደግሞ ለዘላለም ፍርድ አንድ ቀን ሁሉም እንደሚነሡ ቃሉ ይናገራል:: አለቃ ታዬ በሕይወት እያሉ ብቻ ሳይሆን በሞታቸውም ብዙ ወሬ ተነዝቶባቸው ነበር:: አንዱ ወሬ፣ ከእምነታቸው የተነሣ ከቄሳውስቱ ጋር አይስማሙም ነበር:: በዚህም የተነሣ መሬት አስክሬናቸውን እየተፋች አስቸገረች የሚል ነው:: በዚህ የተደነቀ አንድ ሰው "ትልቅ ሰው በመሆናቸው መሬት አልችላቸውም ብላ ነው" ሲል መለሰ ይባላል::

## ቃሉ ለሕያው ሰው እንጂ ለአስክሬን ሥርዓት የለውም

አንድ የሚስዮሎጂስት ፕሮፌሰር ሲያስተምረን ወደ ህንድ የወንጌል መልዕክተኛ ሆኖ ባገለገለበት ዘመን የአንድ አማኝ የቀብር ሥርዓት ትልቅ የወንጌል በር እንደከፈተለት የተረከልን ታሪክ ትዝ አለኝ፣ እንዲህም ብሎ ምስክርነቱን አካፈለን፦

> *እግዚአብሔር በወንጌል ያልተዳረሱትን የመድረስ ትልቅ ሸክምና ጥሪ ስለሰጠኝ ከአስፈላጊ ትምህርት በኋላ እ.ኤ.አ 1976 ከአሜሪካ ወደ ህንድ አቀናሁ:: ወንጌልን መስበክ በጀመርኩበት አካባቢ 99.9% የነበረው ሕዝብ የህንዱይዝም ሃይማኖት የሚከተሉና የተለያየ ጣኦት አምላኪዎች ነበሩ:: ከሁለት ዓመት*

[99] መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ(1896-1922 ዓ.ም) ፤ *የሃየኛው ክፍለ ዘመን መባቻ፤ የዘመን ታሪክ ትዝታዬ ካየሁትና ከሰማሁት (ሁለተኛ እትም)*፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 272-273

አላፍርም ስናገር ይህን ደጋግሜ፣
እውነት ሲመሰክር አይፈራም ወንድሜ::
ይሠሩህ ያግዙህ ይሰደዱህ የትም፣
አንተ ብትሰቃይ ታሪክህ አይሞትም::
ቢከፋ ቢደሰት ሁሉም በሞት ያልፋል፣
የመልካም ሰው ዝና ታሪኩ ይተርፋል::
ቅባትና ጸጋ ተሸሽጎ ቆየ፣
የተዋህዶማ መሠረቱ ታየ::
አንገተ ቢቆረጥ በሰይፍ በካራ፣
አልሰግድም ለሥዕል ለሰው እጅ ሥራ::
ይህንን ቢናገር በቆራጥነት
አቡንና እጨጌ ብዙ ካህናት፣
በዚህ ምክንያት ነው የፈረዱበት፣
ይዘው የከተቱት ከጨለማው ቤት፣
አትብሉ ሰላሰ የሙታን ንብረት::
ከወህኒ ቤት አስረው የዘጉበት ሳንቃ፣
ብሎ ተናገሮ ነው የወንጌል ቃል ይብቃ::
የወንጌልን ሥርዓት ተማሩ ቢላቸው፣
ትልቁም ትንሹም ሁሉም ደደብ ናቸው፣
አሉት ፀረ ማርያም መልስ ቢሳናቸው::
መጻሐፍም ሲሰበር በንባብ በትር፣
ምስጢር መድኃኒቱን ቀብቶ ለማሰር፣
ይህ ሐኪምነቱ ዕውቀቱ ነበር::
ዕውቀትና ምግባር ጉድኀድ ተከተተ፣
አራት ነው እንጂ መች አንድ ሰው ሞተ::
ወዝውዘው ነዝንዘው ጣሉት እንደ ገሆን፣
ያው ወደቀላቸው ይበሉት እንደሆን::
ከጨለማ መኻል በወጣ ብርሃን፣
አጥፉት አጥፉት አሉ እንዳይታየን::





መቅረዙ ተሰብሮ መብራቱ ቢጠፋ፣
ብርሃን የማይወዱ ፈገግን ሲሰፋ
መልሶ እንዲጨልም አደረጉ ተስፋ::[102]

## የአለቃ ታዬ አጽም ለውግዘት?

ኢትዮጵያ በየዘመናቱ አዲስ አሳብ የሚያመነጩና እንዲያስቀድሟት በእግዚአብሔር የተሰጧት ልጆቿን አሳዳ በመግደሏ ቀዳሚ ተብላ በሁሉም የሁሉ ጭራ እንደሆነች ዓለም የሚያውቀው እውነት ነው:: ለዚህ ነበር ባለቅኔውና ፀሐፊ ተውኔቱ አፈወርቅ አዳፍሬ፤ "ላገሬ መሞት" በተሸኘው ቲያትሩ ላይ እንዲህ ሲል ጎምዛዛ ምፀቱን ያስቀመጡት፡-

ኢትዮጵያ ሆይ ምኝ ነሽ ተላላ
የምተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ፤

ይህ ግጥም ደራሲውን ከሥልጣኑ አስወርዶ እስከ ሞት እንዳደረሰው ፍጹም ወ/ማርያም *"ያልተዘመረላቸው"* በሚል መጽሐፉ የአቶ በለጠ ገብሬ "የጉዞ ትዝታ"ን ዋቢ በማድረግ ጽፈዋል::[103] *"ከማይታወቅ መልአክ የሚታወቅ ሰይጣን ይሻላል"* የሚል የቆየ ብሂላችን ለተለመደው ነገር ያለንን ፍቅርና ለአዲስ ነገር ዝግ መሆናችንን ፍንጭ ይሰጠን ይሆን? ከዚህም የተነሣ በቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ ላይ ቃሉን ይዘው የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ በዚህች ምድር በግፍ እንደተሰቃዩና እንደተገደሉ የአባ እስጢፋኖስ፣ የደቂቀ እስጢፋኖስና የአለቃ ታዬ ታሪክ ሕያው ምስክሮች ናቸው:: ዛሬም ልባችን ብዙ አልተለወጠም:: በቅርቡም በአዲስ አበባ አገረ ስብከት በሚገኙ የሰንበት ትምህርት ቤቶች ስም በጥቅምት 2 ቀን 2004 ዓ.ም ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጽሕፈት ቤት ቀረበ የተባለው በታላላቅ ሰዎች የስም ዝርዝር  አለቃ ታዬ፣ ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴና ሌሎች የተሐድሶ ጥያቄ ያነሡ አባቶችን የጸጋ ቅባት *"የኑፋቄ ትምህርት ሠራተኞች"* በማለት በይፋ እንዲወገዙ ጥያቄ እንደቀረበ ጮራ መንፈሳዊ መጽሔት ይፋ አድርጓል::[104] የአለቃ ታዬ አስክሬን በሰላም እንዳያርፍ ካህናቶች መቋሚያ ይዘው ከተዋጉ ከ89 ዓመት በኋላ የዚያ ሀሳብ አቀንቃኞች አጽሙን ለውግዘት ማዘጋጀታቸው ከታሪክ ለመማር እንቢተኝነታችንንና የልባችንን ጥንካሬ ያመለክታል:: እግዚአብሔር ይቅር ይበለን:: የእኛ ያለመባረክ አንዱና ዋና ምክንያት ይቅርታን የማያውቅ የደነደነና ጠንካራ ልባችን ነው::

---

[102] ዮሐንስ አድማሱ *(2004 ዓ.ም)፣ ቀኝ ጌታ ዮፍታሔ ንጉሤ፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 41-42
[103] *ያልተዘመረላቸው 2005 ዓ.ም፣ ገጽ 156*
[104] *ጮራ መጽሔት፣ቁጥር 44፣ 2005 ዓ.ም ገጽ 13*

# አጽሙ ከመቃብር ወጥቶ የተቃጠለ የተሐድሶ ሰው!

በአውሮፓ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ የንጋት ኮከብ የተባለው ጆን ዊክሊፍ መጽሐፍ ቅዱስን ከላቲን የብዙሃኑ ቋንቋ ወደ ሆነው እንግሊዝኛ በመተርጎማቸው እርሱ ከሞተ ከአሥራ አራት ዓመት በኋላ የሮማ ጳጳስ አሩንዴል *"ውግዝ ከመአርዮስ"* በማለት በገሃድ አውግዞት ነበር፡፡ የሮማ ጳጳስ ማርቲን አምስተኛ ደግሞ ጆን ዊክልፍ ከሞተ ከ44 ዓመት በኋላ በ1428 ዓ.ም የጆን ዊክለፍ አጥንት ከተቀበረበት ወጥቶ እንዲቃጠልና አመዱ በወንዝ ላይ እንዲበተን አዞዋል፡፡ ቤተ ክርስቲያን ይህን አስነዋሪ ድርጊት እንድታከናውን ሥልጣን አልተሰጣትም፡፡

ቤተ ክርስቲያን የሰማያዊ ቃል ድሃ ስትሆን ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት በእምላክ ስም ሽፋን መፈጸሟ አይቀሬ ነው፤ ልጓም እንደበጠሰ ፈረስ በመሆን በውሸት ሜዳ ያለ ክልካይ ለጊዜውም ቢሆን ባለድል ትመስላለች፤ ሰውን በማዳን ምትክ በሰዎች ደም ጣቶቿን ነክራ የእግዚአብሔርን ፈቃድ እንዳገለገለች ማሰብ ብቻ ሳይሆን በድፍረት መናገሯ ሙት መሆኗን ያሳብቅባታል፡፡ መታወቅ ያለበት እውነት ቤተ ክርስቲያን ለኢሰብዓዊ ድርጊቷ አንድ ቀን በታላቁ ጌታ የፍርድ ወንበር ፊት ቆማ መልስ ትሰጥበታለች፡፡ ቤተ ክርስቲያን ከዘላለም የሞት ፍርድ ብታመልጥም የሥራ ፍርድ እየጠበቃት እንዳለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ነው፡፡ *"መልካም ቢሆን ወይም ክፉ እንዳደረገ እያንዳንዱ በሥጋው የተሠራውን በብድራት ይቀበል ዘንድ ሁላችን በክርስቶስ በፍርድ ወንበር ፊት ልንገለጥ ይገባናል"* (2ቆሮ.5:10)፡፡ በቤተ እምነት፣ በቡድንና በቤተሰብ ስም ሳይሆን እያንዳንዳችን የምድር አገልግሎትና ሥራችን በእሳት ገና እንደሚፈተን ቃሉ ይናገራል፡- *"...የእያንዳንዱ ሥራ ይገለጣል በእሳት ስለሚገለጥ ያ ቀን ያሳያልና የእያንዳንዱም ሥራ እንዴት መሆኑን እሳቱ ይፈትነዋል"*(2ቆሮ.3:13)፡፡

ቤተ ክርስቲያን ከተጠያቂነት በላይ አይደለችም፡፡ ከላይ እንደተመለከትነው በጆን ዊክልፍ ላይ ቤተ ክርስቲያን ያደረገችው አሉታዊና ኢሰብዓዊ ድርጊት ዋና ዓላማ የፕሮቴስታንትን ተሐድሶ ለማምከን ቢሆንም አልተሳካም፡፡ የእግዚአብሔር ቃል ሁሉንም አሸንፎአል፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያም ምን ያህል የተቀነባበረ ሤራ፣ የማሳደድ፣ የመግደልና የሙትን አጽም እስከ ማውገዝ የተሐድሶ ጥያቄ ይዘው በተነሡት ላይ ቢበዛም ኢየሱስ ክርስቶስ የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በዘመናችን በመንፈሱና በቃሉ ያድሳታል፡፡ መልዕክተኛውን እንጂ መልዕክቱንና የመልዕክቱን ባለቤት ምንም ማድረግ እንደማንችል እንወቅ፡፡ ማንም ሊቋቋምመው የማይችል የቤቱ ራስ የሆነው ኢየሱስ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶን በዘመናችን እውን ያደርጋል፡፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ቀጠሮ ላይ ደርሰናል፡፡





**መጽሐፍ ቅዱስ የት፣ በማን፣ እንዴት እና መቼ መቀበር እንዳለብን አንድም ቃል ያለመናገሩ የትም መቀበር በአንድ ሰው የዘላለም ዕጣ ፈንታው ላይ ምንም ለውጥ ስለማያመጣ ነው፡፡**

## አስተውሎት

ቤተ ክርስቲያን መታደስ እንዳለባት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ ከሞገቱት ከኢትዮጵያ ፋና ወጊ ምሁራን መካከል ነጋድራስ ገ/ሕይወት ባይከዳኝ፣ ዘመንፈስ ቅዱስ አብርሃ ዘብሔረ ዓድዋ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ ይገኙባቸዋል፡፡ አለቃ ታዬን ነጥለን ያየንበት ምክንያት ከቀደሙት ምሁራን እንደ ምሳሌ ለመውሰድ ነው፡፡ በተጨማሪ በእነርሱ የተጻፉ መጻሕፍትን ስናነብ የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አንገብጋቢ ጥያቄያቸው እንደነበር ማየት እንችላለን፡፡ ይህም የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአሁኖቹ ትውልድ ብቻ ሳይሆን የቀድሞዎቹ፣ ያልተማሩቱ ብቻም ሳይሆን የቀለም ፋና ወጊ የተባሉና ከቤተ ክርስቲያን የተገኙ የቀድሞና የአሁኑ ትውልድ ጥያቄ እንደሆነ ያሳየናል፡፡ እግዚአብሔር ያለፈውን የዘመናት የደም ዋጋ፣ የቅዱሳንን ዕንባ፣ ያልተቋረጠ ብርቱ ምልጃና መሥዋዕትነት ተቀብሎ በምህረቱና በጸጋው ራርቶልን የኢትዮጵያን ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ በማደስ ለዓለም በረከት በወንጌል በዘመናችን ያደርጋታል ብዬ አምናለሁ፡፡

በዘመናችን አባቶች ለተሐድሶ የከፈሉትን ዋጋና የእምነት ተጋድሎ ማንበብ ብቻ ሳይሆን የእነርሱን ዱካ ለመከተል መልካሙን የእምነት ገድል በመጋደል ላይ ያላችሁ፣ ትልቅ የስም መጥፋት የደረሰባችሁ የተዛተባችሁና እውነትን በመያዛችሁ የተወገዛችሁ የሐዋርያትን፣ የነቢያትንና የዚህች ምድር የቀደሙ አባቶችን ታላቅ ዕድል አግኝታችኋልና እንኳን ደስ አላችሁ፡፡ ጌታ ይመጣልና በርቱ፡፡ ቀጣዩ ምዕራፍ ቀደሚት አባቶች ሰማዕት የሆኑለት የተሐድሶ ጥያቄ በዚህም ትውልድ መቀጠሉን ያስቃኘናል፡፡

# ፳

# የዘመናችን የተሐድሶ እንቅስቃሴ

## "የፕሮቴስታንት ቅጥረኞች"

*የዚህ ዘመን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ እንቅስቃሴ መቀጣጠል የተጀመረው በ1950 ዓ.ም ገደማ እንደሆነ ይነገራል። በዚያን ዘመን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን መንፈሳዊ ሥርዓት ለማደስ ከተነሡት ሊቃውንት መካከል መምህር መሠረተ ስብሐት ከዋነኞቹ አንዱ ነበር።*[105] በሀገራችን አንዳንድ ታሪክን አዛብተው የተረዱና የሚያስረዱ ሰዎች *"የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ"* የሚል ስም በተነሣ ቁጥር ቶሎ ብለው ተሐድሶ ከጀርመናዊው ማርቲን ሉተርና የእንቅስቃሴው ውጤት ሆነው በዓለማችን ላይ ከተገለጡት ፕሮተስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ብቻ አያይዘው ለመተንተን ይጣደፋሉ። በኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በሰንበት ትምህርት ቤቶች *መምሪያ "የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ"* በሚል ርዕስ *"በማህበረ ቅዱሳን ዶክመንቴሽን ክፍል"* የተዘጋጀው *መጽሐፍ*፦

[105] *ከሣቴ ብርሃን፣ ቁጥር 3፣ 2004 ዓ.ም ገጽ 23*





ከማርቲን ሉተር በፊት በአገራችን በቀደመችው የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የተነሣውን ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በመዝለል *"ተሐድሶን በሀሳብ ፀንሶ በነቢብ ወልዶ በገቢር ያሳደገው መነኩሴ የነበረውና ቆቡን የጣለው ጀርመናዊው ማርቲን ሉተር ነው"*[106] በማለት ታሪክን ያላገናዘበ ውሸት በድፍረት ከነገረን በኋላ በአገራችን የተነሣው ዘመን ጠገብ የተሐድሶ ጥያቄ ትናንት ፕሮቴስታንትን ተከትሎ የመጣ አድርገው ሌላ ውሸት እንዲህ አቅርበዋል፦

> *ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን 'ቤተ ክርስቲያናችን ያረጀች ያፈጀች ስለ ሆነች ተሐድሶ ያስፈልጋታል፤ ተሐድሶውንም የምንፈጽመው እኛው ልጆቿ ነን በማለት የፕሮቴስታንቱ ቅጥረኞች በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ ተመሳስለው ገብተው የፕሮቴስታንቱን ዓላማ ለማሳካት በመሯሯጥ ላይ ይገኛሉ።*[107]

እንዲሁም ዲያቆን ሄኖክ ኃይሌም ከፕሮቴስታንት በፊት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተነሣውን የተሐድሶ ጥያቄ ዱካውን በማጥፋት አሁን ስላለው የተሐድሶ ጥያቄ ከእውነት የራቀ ተረት እንዲህ አስቀምጠዋል፦

> *የመጨረሻው ግብ ደግሞ ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያን በ"ተሐድሶ" ስም የፕሮቴስታንቲዝም ገባር ማድረግና ማጥፋት ነው*[108] ብለዋል።

በኢትዮጵያ ያሉ አብዛኛው የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን ለማደስ እንጂ ለማጥፋት በመጡት ሚሲዮናውያን አልተመሠረቱም። በአብዛኛው የፕሮቴስታንት (የወንጌል አማኞች) የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን የማጥፋት ዓላማ ሳይኖራቸው የተሐድሶ ጥያቄ በተነሣ ቁጥር በተለይ በአንዳንድ የኦርቶዶክስ ጸሐፊዎች ዘንድ ፕሮቴስታንት የተባሉ ሁሉ ስማቸው በአሉታዊ መነሣቱ የፕሮቴስታንት ፍርሃት (ፕሮቴስታንት-ፎቢያ) ይመስላል። በታሪክ፣ በዕድሜ፣ በሀብት፣ በሰው ብዛት፣ በዓለማችን ገናና ከሆኑት አብያተ ክርስቲያናት አንዷ የሆነች የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የመቶ ዓመት ሕፃን የሆኑ ፕሮቴስታንቶችን ትፈራለች ተብሎ ባይታሰብም አንዳንዶች ግን በኦርቶዶክስ ስም ያልበሰለና የወረደ አሳብ መወርወራቸው መልካም አይደለም። ሊዘነጋ የማይገባው ጉዳይ ግን የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ የፕሮቴስታንት ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ሳትወለድ ቢያንስ ከስድስት ምዕተ ዓመት የቀደመ መሆኑ ነው። እውነተኛ ተሐድሶ የቃሉ ጥያቄ እንጂ ሰዎች የመሠረቷቸው የቤተ እምነቶችና ዶግማ የበላይነት የሚሰበክበት እንዳልሆነ መታወቅ አለበት። እውነተኛ ተሐድሶ ከእግዚአብሔር፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ክብርና ለዓለም በረከት የሚሰጥ ስጦታ ነው።

[106] *የተሐድሶ መናፍቃን ዘመቻ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ላይ፣* 2003 ዓ.ም ገጽ 13
[107] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 13*
[108] ሐመር ተዋሕዶ *(ልዩ እትም)*፣ ነሐሴ 2002 ዓ.ም ገጽ 85

የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ የእግዚአብሔር ጉዳይ እንጂ የኦርቶዶክስ፣ የካቶሊክና የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት ጉዳይ ብቻ አይደለም:: ከእርስ በርሳችን ይልቅ ወደ ችግሮቻችን ዒላማችንን ብናነጣጥር ያዋጣናል:: ካልሆነ ግን ለራሳችንም፣ ለዓለምና ለእግዚአብሔርም ሳንሆን ዘመናችን በከንቱ ማለቁ ነው::

የፕሮቴስታንት ተሐደሶ እንቅስቃሴ በዓለም ከመገለጡና ሉተር ከመወለዱ በፊት በዐፄ *ያግብ ጽዮን (1278 – 1286)* እና በደቂቀ እስጢፋኖስ*(1406 - 1421) ዘመን* በኤትዮጵያ ተነሥቶ የነበረውን ተመሳሳይ የተሐድሶ ጥያቄ በኢትዮጵያ በወቅቱ ያልነበሩ የፕሮቴስታንት *"ቅጥረኞች"* ጥያቄ ነው እንበልን? በዚያ ዘመን በኢትዮጵያ ቀርቶ በዓለም ላይ ያልተወለደ ፕሮቴስታንቲዝም "ቅጥረኞችን" እንዴት ወለደ? እንዲሁም በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወልደው ያደጉ አለቃ ኪዳነ ወልደ ክፍሌ፣ አለቃ መሠረት ስብሐት ለአብ፣ አለቃ ታዬ፣ ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወልደ ሥላሴ፣ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ... ወዘተ ያሉ ቀደምት ደራሲያን በጽሑፎቻቸው የተሐድሶ አስተሳሰብ አራማጆች እንደነበሩ የእነርሱን ጽሑፎች ማንበብ በቂ ነው:: እነርሱንስ ምን እንበላቸው? እንዲሁም በቤተ ክርስቲያኒቱ ውስጥ ከነበሩ ስመጥር አስተማሪዎች እንደ የኔታ በየነ ዘውቴጣ እና አለቃ በየነ ዳምጤው እንዲሁም አባ ሀብተ ጊዮርጊስ ያሉ ለተማሪዎቻቸው ትክክለኛውንና የተሳሳተውን አስተምህሮ በመለየት በማስተማር የተሐድሶ ጥያቄ ለቀጣዩ ትውልድም ጥያቄው እንዲሆን የበኩላቸውን ሚና መጫወታቸው መዘንጋት የለበትም::

## "የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን"

የዛሬ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሻገረ የመጣ ውስጣዊ እንጂ እንደ ባሕር ዛፍ ከውጭ የእንዳልመጣ፣ ትናንት ከመጡ ፕሮቴስታንቶች የተኮረጀ ሳይሆን ትውልድ ከአባቶቹ እንደተቀበለ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በቤተ ክርስቲያኒቷ ተወልደውና አድገው ለአገልግሎት የበቁት ቅዱሳን ከአባቶቻቸው ተላልፎላቸው አንግበው ስለተነሡት የተሐድሶ ጥያቄ የሚሉትን ከራሳቸው እንስማ::

ዲያቆን ያሬድ ወልደ ማርያም ሲናገሩ:-

> *አሁንም እነዚህ ቤተ ክርስቲያናችንን በመውረር በንጹሕ ሐዋርያዊ መሠረቷ ላይ እንደ ኩይሳ የተከመሩባት የኑፋቄ ትምህርቶች መስተካከል እና መታረም አለባቸው እንላለን:: ይህንን ደግሞ የምንለው ከሉተር ቀድተነው ሳይሆን ከአባ እስጢፋኖስ ተምረነው ነው:: ...ስለዚህ አንዳንዶች እንደሚሉት የሃይማኖት ነፃነት ስለተገኘ ወይም ኢሕአዴግ ከመጣ ድንገት የተወለደ አለበለዚያም ከሉተር የተቀዳ ሳይሆን ከአባ እስጢፋኖስ የተወረሰ በልባችንም የተነሣና የኖረ (የደረጀ) ጥያቄ ነው:: እንደምትሉትም መጤና የነጮች ተጽዕኖ ያረፈበት አይደለም[109] ብለዋል::*

[109] *የማኅበረ ቅዱሳን የወቅቱ ዘመቻና የፈጠራ ሠነዱ፣* 2004 ዓ.ም ገጽ 15







አባ ተስፋ ማርያም ስለዚህ ሲናገሩ:-

> *በመጀመሪያ እኛ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ልጆች ነን፤ በቤተ ክርስቲያኒቱ የክህነት አገልግሎት ውስጥ ተሳታፊ የሆንን የቅኔ፣ የዜማ፣ የቅዳሴ የአቋቋምና የመጽሐፍት ፍቺ በመማር ያሳለፍን ቤተኞች ነን እንጂ ከሌላ ሥፍራ የመጣን አይደለንም:: በቤተ ክርስቲያኗ በቅስና፣ በዲቁና በመሪጌታነት በተለያየ የአገልግሎት ዘርፍ ያለን፣ በአርባ ቀንና በሰማኒያ ቀን የተጠመቅን ክርስቲያኖች እንጂ "ማህበረ ቅዱሳን" እንደሚያስወሩት የፕሮቴስታንቶች ቅጥረኞች አይደለንም፤[110]* በማለት በማህበረ ቅዱሳን የደረሰባቸውን ውንጀላ በገሃድ ተቃውመዋል::

በዘመናችን በኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን የተሐድሶ ጥያቄ አንግበው የተነሡ የኦርቶዶክስ አገልጋዮች እንጂ ፕሮቴስታንቶች እንዳይደሉ ምስክርነታቸውን በገሃድ በመናገር ላይ ይገኛሉ:: ዛሬም ትውልዱ ይዞት የተነሣውን የቆየውን የተሐድሶ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጥያቄ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ ከመመለስ አቅጣጫን ለማሳት የፕሮቴስታንት *"ቅጥረኞች"* ናቸው ማለት ብቻ በቂና ሚዛናዊ መልስ አይደለም:: መላውን አፍሪካ ሲያምስ የነበረው ፈላጭ ቆራጩ የሊቢያ መሪ ጋዳፊ ሕዝብ ፈንቅሎ ወደ አደባባይ ወጥቶ ሥልጣኑን እንዲለቅ ሲጮህ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ለጋዳፊ:- *"ሕዝቡ አንተን እየተቃወመ ስለሆነ ሥልጣን ለምን አትለቅም"* ሲለው ጋዳፊም:- *"ሕዝቡ እኔን እየደገፈ የእናንተን የምዕራባውያን ጣልቃ ገብነት እየተቃወመ ነው"* በማለት ለትክክለኛ ጥያቄ ያልተገባ መልስ በመስጠት ለመሸወድ ብሞክርም ከአሳዛኝ ሞት ራሱንና ቤተሰቡን ማስመለጥ አልቻለም:: ይህም የሕዝቡን ጥያቄ አቅጣጫ የማሳት አደገኛ አካሄድ በአፍሪካ ቤተ ክርስቲያንና ቤተ መንግሥት የተለመደ መሆኑን ያመለክታል:: በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዘመን ዘለቅ የሆነ የተሐድሶ ጥያቄ በተነሣ ቁጥር ፕሮቴስታንታዊ አድርጎ ዱካውን የማጥፊት አካሄድ ከእንግዲህ አይቻልም:: ማንም ሊክድ የማይችለው እውነት *"የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ያስፈልጋታል"* የሚል ድምፅ በግልና በተደራጀ መልኩ በምድራችን ከመቼውም ጊዜ ይልቅ በማስተጋባት ላይ እንዳለ የአደባባይ ምስጢር ነው:: በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በአገልግሎት ላይ እንዳሉ የሚናገሩ አገልጋዮች ቤተ ክርስቲያናቸው በምን ላይ ተሐድሶ ማድረግ እንዳለባት ለሕትመት በበቁት ቱባ መጻሕፍት በግልጽ ጥያቄያቸውን ከማቅረብ አልፈው በተለያየ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ተዋቅረው ለቤተ ክርስቲያናቸው ተሐድሶ የበኩላቸውን አዎንታዊ ሚና በመጫወት ላይ እንደሚገኙ የታወቀ ነው::

በኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዲቁናን፣ ቅስናንና መምህርነትን ተቀብለው በአገልግሎት እንደተሰማሩ በሚናገሩት አገልጋዮች በተሐድሶ ላይ ከተጻፉ ከብዙ መጻሕፍት መካከል *"ኦርቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው"፣ "በውኑ በማርያም ማመን ይገባልን?"፣ "ገድል ወይስ ገደል"፣ "ከመጋረጃው ጀርባ"፣ "መጽሐፍተ ኑፋቄ"፣ "አካልና ጥላ"፣ "ሎሌ"፣ "ክርስቶስ ታቦታችን"፣ "የተቀበረ መክሊት"፣ "የለውጥ ያለህ"፣ "የዘመናት እንቆቅልሽ ሲፈታ"፣ "መስተበቁዕ ዘሙታን"፣ "ማሣቀል"* ወ.ዘ.ተ የሚሉት ይገኙበታል::

[110] *ከሣቴ ብርሃን፣ ቁጥር 3.* 2004 ዓ.ም ገጽ 23

በተቃራኒው ደግሞ ተሐድሶ የሚለውን ቃል እንደ ጦር የሚፈሩ፣ ስለተሐድሶ የሚያነሣውን ሰው ሁሉ በማብጠልጠልና በአሉታዊ መልኩ አሳቡን አጣመው ማቅረብን እንደ ትልቅ አገልግሎት የቆጠሩ ቡድኖች በአገራችን ነበሩ፤ ለጊዜውም ቢሆን ይኖራሉ። አንድ ማወቅ የሚገባን እውነት ተሐድሶ የሰው ጉዳይ ሳይሆን የቤቱ ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ለቤቱ ያለው የዘመኑ አጀንዳ መሆኑን ነው። ስለዚህ የሮማው ማኅበተምና የወታደሮች ጥብቅ ጥበቃ የክርስቶስን መነሣትና የድንጋዩን መፈንቀል መግታት እንዳልቻሉ ሁሉ በ21ኛው ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን እየተቀጣጠለ ያለውን የተሐድሶ እሳት ማንም ሊያዳፍን አይችልም።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ካልታደሰች የኢትዮጵያ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የመሠረተ ልማት፣ የትምህርት፣ የአገር ገጽታ ሕዳሴ ሙሉዕ አይሆንም የሚል እምነት አለኝ። ለኢትዮጵያ ሕዳሴ ሕዝቡ ከመንግሥት ጋር በመያያዝ በትጋት በመሥራት ላይ እንዳሉ ሁሉ የቤተ ክርስቲያን ራስ የሆነው የናዝሬቱ ኢየሱስ አካሉ የሆነችውን የምድራችንን ቤተ ክርስቲያን በቃሉና በመንፈሱ ሊያድስ እየሠራ እንደሆነ መንፈሳዊ ዓይኑ ለተከፈተ ሰው ሁሉ ገሃድ የወጣ እውነት ነው። የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ አጀንዳ የግለሰቦች፣ የቡድኖችና የመንግሥት አጀንዳ ሳይሆን የክርስቶስ አጀንዳ ነው።

ቤተ ክርስቲያን የሰዎች የጠረጴዛ ዙሪያ ክርክር ወይም የፍርድ ቤት ውሳኔ ውጤት ካልሆነች ተሐድሶዋም በዚያ መንገድ አይሆንም። የክርስቶስ የዘላለም አጀንዳው ወንጌል ሲሆን በወንጌል ፊት የተደቀኑ የሰው ሥርዓትና ወጎች እንዲሁም እውነትን የጋረዱ ትውፊቶችን ለማስወገድ በእኛ ይጠቀማል እንጂ እኛን አያማክረንም። ለጌታ እጃችንን ብንሰጥ መሣሪያዎቹ ያደርገናል፤ መንገዱ ላይ ብንቆም ግን ጉዳታችን አስደንጋጭ ይሆናል። ከሁሉ የከፋው ጉዳት እኛን ለእኛው አሳልፎ ትቶን መሄድ ነው። በራሷ ሃይማኖታዊ ሥርዓትና ቅደም ተከተል ተጣብቃ ጌታን ቸል ስትለው ትቶዋት እንደ ሄደ እንደ ኢየሩሳሌም ቤተ መቅደስ ትቶን እዳይሄድ (ማቴ.24:1) መጠንቀቅ ነው። ከራሳችን በላይ ቃሉንና መንፈሱን እንስማ። በቤተ ክርስቲያን ለሚነሣው ፈርጀ ብዙ የተሐድሶ ጥያቄዎች መልሱ ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ እንጂ ምክንያተ ብዙ መሆን አይደለም። የራሳችንን ችግር በወጉ በማጤን፣ ከስሜታዊነት ነጽተን፣ ቃሉን መሠረት በማድረግ፣ ጸጋውን ተደግፈን የመፍትሔ እርምጃ በእምነት መውሰድ እንጂ ለራስ ችግር ሌላውን ተጠያቂ ማድረግ ችግሩን ቢያባብስብን እንጂ ከችግሩ የመውጫ መንገድ ሊሆነን አይችልም። *"የጠቢብ ዓይኖች ወደ ራሱ ነው"* የተባለው ለዚህ ነውና።

በዐፄ ያግብ ጽዮን ዘመን ከተነሣው የታሐድሶ ጥያቄ ከ718 ዓመት በኋላ፣ በደቂቀ እስጢፋኖስ ዘመን በአሰቃቂ ግድያ ከተጠናቀቀው የተሐድሶ ጥያቄ ከተነሣ ከ583 ዓመት በኋላ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ዛሬም የተሐድሶ ጥያቄ ቀዳሚ ጥያቄ እንደሆነ መጻሕፍት፣ መጽሔቶች፣ ጋዜጦችና የተለያዩ ድህረ ገጾች ያስተጋባሉ። መጋቢ ጥበቡ ሰሎሞን *"ኦሮቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው!"* በሚል መጽሐፋቸው፦





*ቤተ ክርስቲያኗ የአበው አስተምህሮ ልትይዝ ይገባል። በኋላ የመጣላትን ስሁት የተቀበለችውን ቤተ ክርስቲያናችን በንስሐ እንድትመለስ ወንጌል በአውደ ምሕረታችን በሥልጣን ገብቶ ሥፍራ ይያዝ ምዕመናን በቃለ እግዚአብሔር ይታጠቁ! ቤተ ክርስቲያናችን ትጠናከር የሚሉ ቅንአተ-ቤተ ክርስቲያን የበላቸው በርካታ የቤተ ክርስቲያን መነኮሳት፣ ቄሳውስት፣ ዲያቆናት ምዕመናን ሁሉ ተነሡ። ነገር ግን ከፋዎች ነግሠው ብዙዎችን አሳደዱ፣ ገደሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስን አቃጠሉ፣ የስም ማጥፋት ዘመቻውንም አጧጧፉ። ይሁን እንጂ ጥያቄው እየሰፋ እንቅስቃሴውም እየጎለበተ ከመንበረ ፓትሪያሪክ እስከ አዲስ አጥቢያ ድረስ ተዳርሷል።*[111] በማለት የተሐድሶ ጥያቄ የሁሉን ደጅ በማንኳኳት ላይ እንደሚገኝ ለማመልከት ጥረዋል።

ጥያቄው ምን እንደሆነ ከዚህችው የዕድሜ ባለጠጋና የሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እናት ከሆነችው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ተወልደው፣ አድገው፣ ተምረው ለአገልግሎት የበቁና ዛሬም የእርሷ ልጆች እንደሆኑ ከሚናገሩ መካከል "ከሣቴ ብርሃን ስብከት ወንጌል ዘኢትዮጵያ" አገልጋዮች በጽሑፎቻቸው በገሃድ ይናገራሉ። "ብሔራዊ ተሐድሶ" በሚል ርዕስ ባሳተሙት መጽሔት ባሉበት ቤተ ክርስቲያን ትልቁ የተሐድሶ ጥያቄያቸው ምን እንደሆነ ሲገልጹ፦

> *ተሐድሶአውያን የሚጠይቁት ዋና ጥያቄ ቤተ ክርስቲያናችን ክርስቶስን አጉልታና አብዝታ በመስበክ ሰው ሁሉ ድነትን ያግኝ የሚል እንጂ ከዚህ የተለየ ነገር የለም"*[112] ይላሉ።

እነርሱ እንዳሉት ጥያቄው ኢየሱስን መስበክ ከሆነ ክርክሩ ከየት መጣ? የቤተ ክርስቲያን መሥራችና ራስ የሆነው ኢየሱስ ክርስቶስ ሐዋርያትን ሲልክ *"ወደ ዓለም ሂዱ ወንጌልን ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ" (ማር.16:15)* ሲል ሐዋርያው ጳውሎስም *"እኛ ግን የተሰቀለውን ክርስቶስ እንሰብካለን" (1ቆሮ. 1:23)* በማለት የቤተ ክርስቲያን ቀዳሚ አጀንዳ የወንጌል ስብከት እንደሆነ አስታውቋል። ከወንጌል ስብከት የሚበልጥ ቤተ ክርስቲያንን በምድር የሚያኖራት አጀንዳ ምንም የለም። ታዲያ ቤተ ክርስቲያኒቷ ወንጌልን እየሰበከች ከሆነ የተሐድሶ ጥያቄ አንግበው እንደተነሡ የሚናገሩ ልጆቿም ጥያቄያቸው የወንጌል ይሰበክ ከሆነ ጥል፣ ውግዘትና ስም የማጥፋት ዘመቻውን ምን አመጣው? ዓለም እየጠበቀቻችሁ አለና ጠብ፣ ክርክርና ጥላችን አስወግዳችሁ በሰላም ወንጌል ሰላም በመመሥረት በክብርና በኃይል የመጨረሻውን መከር ለመሰብሰብ ይህ ዘመናችሁ ነውና እባካችሁን ንቁ! የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በዚህ ዘመን እግዚአብሔር በትልቅ ክብር በወንጌል ለወንጌል እንደሚያስነሣት አምናለሁ።

ዛሬ ተሐድሶን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወይም በካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በወንጌላውያን አማኞችም ዘንድ ዐቢይ ርዕስ ጉዳይ ያደረገው መንፈሳዊነትን ተላብሶ ዓለማዊነትና ሥጋዊነት በቤተ ክርስቲያን እየተዛመተና እውነተኛው የእግዚአብሔር ቃል በሰዎች ልምምድና ቤተ ክርስቲያናዊ ባሕል እየተቀየረ በመምጣቱ ነው። የዚህ መጽሐፍ ጸሐፊ

[111] ጥበቡ ሰሎሞን (መጋቢ)(*1999 ዓ.ም*)፣ *ኦሮቶዶክሳዊነት እንዲህ ነው!* ገጽ 172

[112] ብሔራዊ ተሐድሶ፣ 1ኛ ዓመት ቁጥር 1፡ ኅዳር 2004 ዓ.ም ገጽ 7

እንደ ቃሉ ያልሆኑ ብዙ ተሐድሶ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች በሁሉም አብያተ ክርስቲያናት እንዳሉ ያምናል፡፡ ይህን ዘመን ጠገብ ጥያቄ እንዳይመለስ ቤተ ክርስቲያን አሉታዊ እርምጃ በመውሰድ ታሪካዊ ስህተት እንዳትፈጽም፣ በባለራእይነት ዓይን አሻግራ ማየት እንድትችልና መጽሐፍ ቅዱሳዊ መልስ በመስጠት ወንጌልን ለዓለም በማድረስ ዋና ተልዕኮዋ ላይ እንድታተኩር የሁላችንም ጸሎት ይሁን፡፡

## የአብያተ ክርስቲያናት አንድነትና ልዩነት

*ዳንኤል ተሾመ "የቅርብ ዘመኑ (1979-1999) የተሐድሶ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን"* በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ባደረጉት ጥናት ላይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር አንድ ስለሚያደርጋት መሠረተ እምነት ሲገልጹ:-

> *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የክርስቶስን አዳኝነትም ሆነ መድኃኒትነት የምትቀበል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ በሆነው የአሐዱ አምላክ በሦስት አካል መገለጥ (ሥላሴ) አስተምህሮ የምታምን መሆንዋን እንዲሁም በብሉይና በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት (መጽሐፍ ቅዱስ) የእግዚአብሔር ቃል እንደሆነ የምታምን፣ ደግሞም ሦስቱን ዓለም አቀፍ የሆኑ የሃይማኖት መግለጫዎች (አመክንዮታት) (የሐዋርያት፣ የኒቂያና የአተናቴዎስ) የተቀበለች መሆኗ የመሠረት ችግር እንደሌለባት ያመለክታል[113] ብለዋል፡፡*

ዳጎስ ያሉ መጻሕፍት ደራሲ (ቀደሰ) ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ *"አንድ እረኛ አንድ መንጋ"* በሚል ርዕስ በጻፉት መጽሐፋቸው ስለ እነዚህ የሃይማኖት መግለጫ (አመክንዮታት) ሲናገሩ:-

> *እነዚህን አመክንዮታት የሚቀበል ሁሉ ክርስቲያን ነው፤ ስለሆነ የቀረው ችግር ሁሉ በክብ ጠረጴዛ ውይይት፣ መሪዎች ሰላም፣ ከፈለጉ ሊፈታ ይችላል፤[114]* ካሉ በኋላ *በዚሁ መጽሐፋቸው "ክርስቲያን የሚባሉ(ና) ያለመለያየት አብረው መኖር የሚገባቸው" የግሪክ ኦርቶዶክስ፣ የኦሪንታል ኦርቶዶክስ፣ የካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና ከሉተር ጀምሮ ያሉት ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ናቸው[115] ብለዋል፡፡*

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የራስዋ የሆኑ ብዙ ትውፊቶችና ሥርዓቶች ቢኖሯትም እ.ኤ.አ በ1948 በተቋቋመው *"የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር"*[116] አባል፤ እንዲሁም እ.ኤ.አ በ1963 የመላ

[113] *ዳንኤል ተሾመ፣2004 ዓ.ም ገጽ 50-51*

[114] *ዓለማየሁ ሞገስ ደረሶ (ቀደሰ) (1989 ዓ.ም)፣ ፣አንድ እረኛ አንድ መንጋ፣* ገጽ 106

[115] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 179-180*

[116] *የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የአንድነታቸው ዋና ዓላማ* It arose out of the ecumenical movement and has as its basis the following statement *he World Council of Churches is a fellowship of churches which confess the Lord Jesus Christ as God and Saviour according to the*





አፍሪካ አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ሲመሠረት የድርጅቱ መሥራች አባል መሆኗ በክርስቶስ ኢየሱስ ከሌሎች ጋር ያላትን አንድነት ለማመልከትና ወንጌልን ለዓለም አብሮ ለማድረስ እንደሆነ ለማንም ግልጽ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን የ2000 ዓመታት ታሪክ የተዘከረበት መጽሐፍ ስለ ዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር ዓላማ እንዲህ ይገልጸዋል:

> *ዓላማና ተግባሩም ምስጢረ ቁርባንን በአንድነት ለመፈጸም እስከሚቻል ድረስ አባል <u>አብያተ ክርስቲያናት ስለ እምነት አንድነት የሚያደርጉትን ጥረት ማበረታታትና የክርስትናው ዓለም አንድነቱን በተግባር እንዲያሳይ ማብቃት ነው</u>፡፡(መስመሩ በኔ)... የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የዚህ ድርጅት መሥራች አባል ስትሆን አሁንም በአባልነቷ እንደጸናች ትገኛለች፡፡[117] በዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር የታቀፉት አብዛኛው የኦርቶዶክስ አብያተ ክርስቲያናት፣ ከፕሮቴስታንቶች አንግሊካን፣ ሉተራን፣ መቶዲስት፣ መጥመቃውያን፣ ፕራስበቴሪያን፣ የፔንተኮስታል፣ አንዳንድ የቆዩ የካቶሊክ አብያተ ክርስቲያናት ወ.ዘ.ተ..ናቸው፡፡[118]*

ከሮማ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በቀር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማኅበር በ150 አገራት ከሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የተሰባሰቡ ሲሆን በአጠቃላይ ከ500 ሚሊዮን በላይ አባላትን ይዟል፡፡ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአህጉርና በዓለም አቀፍ ደረጃ ባሉት የአብያተ ክርስቲያናት ማኅበራት ከፕሮቴስታንቶች ጋር እጅ ለእጅ ተያይዛ መቆሟ ትልቅነቷንና ለአንድነት ያላትን ልብ ያሳያል፡፡ አንዳንድ የአገሬ የኦርቶዶክስ ጸሐፊዎች ቤተ ክርስቲያናቸው ከፕሮቴስታንት ጋር አንድ የሚያደርጋት ቀርቶ ፕሮቴስታንቶችን እንደ ቤተ ክርስቲያን ሳይሆን *"ፀረ ማርያም"* የሚል ዘመን ዘለቅ የውግዘት ስሌዳ ማሸከማቸው የተለመደ ነው፡፡ አንዳንድ ያላዋቂ ደፋር ጸሐፊዎች ደግሞ ፕሮቴስታንቶችን *"ሰይጣን"* እስከማለት ደርሰዋል፡፡ ትልቁ ችግራቸው መጽሐፍ ቅዱሳዊ የመረዳት ድሃ መሆናቸው ነው፡፡ እግዚአብሔር ዓይናቸውን ያብራ፡፡ በፕሮቴስታንትም ወገን አንዳንድ ጽንፈኞች የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ምንም እውነት እንደሌላትና የጠፋች እንደሆነች የሚናገሩና የሚጽፉ አይታጡም፡፡

ይህ ትልቅ ስህተት ብቻ ሳይሆን አንድ አምላክ እየጠራንና አንድ ወንጌል እንሰብካለን እያልን የጐሪጥ የምንተያይ ምስኪኖች አድርጎናል፡፡ ዋናው ኦርቶዶክሳዊነትና ፕሮቴስታንታዊነት ሳይሆን ለዓለም ኃጢአት በሞተልን ጌታ መገኘታችን ለዘላለም አንድ ያደርገናል፡፡ እግዚአብሔር የልጁ መንግሥት እንጂ የካቶሊክ፣ የፕሮቴስታንትና የኦርቶዶክስ መንግሥት የለውም፡፡ በምድር ወንጌልን በማሮጥ ሊጠቀምባቸው ግን ይችላል፡፡ እውነቱ ግን ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸው የአደባባይ ምስጢር መሆኑ ነው፡፡ በአንድነት ውስጥ ያለውን ልዩነታችንን አውቀን ብንቀባበል፣ መማማርና

*scriptures, and there fore seek to fulfil together their common calling to the glory of the one God, Father, Son and Holy Spirit.* ይበልጥ ለመረዳት ቀጣዩን ድረ ገጽ ይመልከቱ፡፡ *http://en.wikipedia.org/wiki/World_Council_of_Churches*

[117] *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከልደተ ክርስቶስ እስከ 2000 ዓ.ም፣ ገጽ 299*

[118] http://en.wikipedia.org/wiki/World_Council_of_Churches

መደማመጥ ቢኖር ለዓለም በወንጌል በረከት በሆንን ነበር:: እዚሁ ስንናቆር ለዓለም መድረስ ቀርቶ የጠራ ወንጌል ለሕዝባችን ሳናቀብል ቀዳሚ የሆንን እየመሰለን ኋለኞች ሆነናል:: በዓለም አቀፍ መድረክ የኦርቶዶክስና፣ የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት የመያያዣቸው ምስጢር የ"ቀኖና"[119] ልዩነት ቢኖራቸውም "የዶግማ"[120] (መሠረተ እምነት) አንድነት እንዳላቸው ስላመኑ ነው:: የአንድነታቸው መሠረት በዓለም አቀፍ ደረጃ በአብዛኛው አብያተ ክርስቲያናት ዕውቅና ባገኘው የሃይማኖት መግለጫዎች ላይ ስለቆሙ እንጂ በሁሉም አንድ ስለሆኑና የአንዱን አስተምህሮ ሌላው ሙሉ በሙሉ ስለሚቀበልና ስለተቀበሏ አይደለም::

በኢትዮጵያ የሚገኙ ፕሮቴስታንቶች እንኳ በቀኖና እጅግ መለያየታቸው ብቻ ሳይሆን ከዛሬ 30 ዓመት በፊት አንዱ የአንዱን ድኅነት ለመቀበል የሚቸገርና አንዱ የአንዱን እንከን ለመግለጥ ይተጉ እንደነበር የሚታወስ ነው:: አሁን እጅ ለእጅ የተያያዙት ከችግራቸው በላይ ያደገ አመለካከትና የወንጌል እውነት ምስጢር ከትናትናው ይልቅ ዛሬ መረዳት ስለበዛላቸው ልዩነታቸው እያለ አንድነታቸውን ለማጉላት የወንጌል እውነት አስገድዷቸው ነው:: በዚህ 21ኛ ክፍለ ዘመን በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን፣ በኢትዮጵያ ካቶሊካዊት ቤተ ክርስቲያንና በኢትዮጵያ በሚገኙ ፕሮቴስታንቶችም መካከል ያለው አሉታዊ ውጥረትና ትችት ረግቦ በክርስቶስ ኢየሱስ እውነት ተያይዘው ለዓለም በወንጌል መጥለቅለቅ ምክንያት ይሆናሉ:: ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የወንጌል መልዕክተኞችም የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያንን በመቀበል አብሮ ለመሥራት የፈቀዱበት ዋና ምክንያት ቤተ ክርስቲያኒቷ የመሠረተ እምነት ችግር የለባትም ብለው ስላመኑ ነበር:: የክርስትናን መሠረተ እምነት የሚንዱ የሉልዓቀፋዊነት አሉታዊ ጫና፣ የድህረ ዘመናዊነትና የእንጻራዊነት ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፍልስፍና ለመቋቋም አንድ መሠረተ እምነት ያላቸው አብያተ ክርስቲያናት ከልዩነታቸው ይልቅ አንድነታቸውን በማጉላት በሕልውናቸው ላይ የመጡ የዘመኑን ተግዳሮቶች አሸንፈው ወንጌልን ለቀጣይ ትውልድ የማቀበል አደጋ ተጋርጦባቸዋል:: እየመጡ ያሉት ፈርጀ ብዙ ተግዳሮቶች አንድነትን ውዴታ ብቻ ሳይሆን ግዴታ የማድረግ አቅም አላቸው::

ከላይ የተገለጡትን ሦስቱ ዓለም አቀፋዊ የሆነ የክርስትና ሃይማኖት መግለጫዎችን የሚቀበሉ አብያተ ክርስቲያናት በአንዳንድ የአስተምህሮ ልዩነታቸው ላይ መነጋገር መቻል አንድ ነገር ሆኖ አንዱ ለአንዱ "መናፍቅ" ማለት እንደማይችሉ ምሁራን ይናገራሉ:: አንዲት ቤተ ክርስቲያን የመሠረተ እምነት ችግር የላትም ማለት አስተምህሮዋ ስህተት አልባ ስለ መሆኑ

[119] *ቀኖና:- አምልኮተ እግዚአብሔርን ለማካሄድ ወንጌልን ለማሰራጨትና የመላለሱትን መንፈሳዊ ተግባራት ለማከናወን ሲባል የሚወጣ ሥርዓት ነው:: ቀኖና ሥርዓት በመሆኑም እንደጊዜው ሁኔታ ታይቶ መሻሻል የሚደረግበት ነው:: ዝኒ ከማሁ፣ 17*

[120] *መሠረተ እምነት (ዶግማ):- በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የቆመ፣ የሚጨመርበት የሚቀነስለት ወይም እንደ ሁኔታው ታይቶ የሚሻሻል የሌለበት ዘላለማዊ ነው:: ዲያቆን አግዛቸው ተፈራ፣ የተቀበረ መክሊት፣ አፍሪካ ማተሚያ ቤት፣ ገጽ 17*





ዋስትና ሊሆናት በፍጹም አይችልም:: አብዛኛው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነ የመናፍቅ ትምህርት ጥንትም ሆነ ዛሬ በአገራችንና በዓለም ላይ እንደ አሸን በመፍላት ላይ የሚገኘው የመሠረተ እምነት ችግር በሌላቸው አብያተ ክርስቲያን እንደሆነ አንዘንጋ:: ዋናው መሠረተ እምነት ቢሆንም መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው መሠረት እምነት በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስትምህሮ መመራት የግድ ነው:: የአንዲት ቤተ ክርስቲያን መልካም ጅማሬ መልካም ፍጻሜዋን አያመላክትም:: በፍቅር የታወቀችና ዝናዋን ሰምቶ ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ፍቅሯ የመሰከረላት የኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን *(ኤፌ.1:16)* ከ45 ዓመት በኋላ ኢየሱስ ፍቅርን ጥላ እንደወደቀች ሲመሰክርባት:-

> *"ዳሩ ግን የምነቅፍብህ ነገር አለኝ የቀደመውን ፍቅርህን ትተሃልና:: እንግዲህ ከወዴት እንደ ወደቅህ አስብ ንስሐም ግባ የቀደመውን ሥራህን አድርግ አለዚያ እመጣብሃለሁ ንስሐም ባትገባ መቅረዝህን ከሥፍራው እወስዳለሁ" (ራእ.2:5)::*

እንዲሁም ክርስቶስ በዓይናቸው ፊት እንደ ተሰቀለ ተሥሎ የነበረው የገላትያ ቅዱሳን 30 ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ክርስትናቸው አዚም *(የሚያፈዝ ወይም የሚያደነግዝ መተት አስማት)*[121] እንደሆነባቸው (ገላ.3:1) እና ሐዋርያው ጳውሎስ ወደ ቀደመው መንገድ ሊመልሳቸው *"ልጆቼ ሆይ ክርስቶስ በእናንተ እስኪሣል ድረስ ዳግመኛ ስለ እናንተ ምጥ ይዘኛል" (ገላ.4:19)* በማለት ይናገራል:: ቤተ ክርስቲያን እንደተቀበለችው ቃል ዕለት ዕለት መራመድና ፍሬ ማፍራት በመቻሏ፣ የቃሉን እውነት በማስተማር ደቀ መዝሙር በማድረግ አቅሟ፣ ወንጌል ያልሰማውን ዓለም በወንጌል ለመድረስ ባላት የሚሲዮናዊነት ራእይ፣ ስለ ክርስቶስ መከራን ለመቀበል ባላት ዝግጁነትና በክርስቶስ ኢየሱስ ወንጌል በመኖር ባላት ምሳሌነትና ፍሬ ትመዘናለች:: ከወንጌል ማህፀን የተወለዱ፣ ትናንት በዓለም አቀፍ ደረጃ ድንበር ዘለል የወንጌል ሚሲዮናውያንን በመላክ ለሚሊዮኖች የመዳን ምክንያት የነበሩ፣ ዛሬ በደርጅታዊ መዋቅራቸው ጥንካሬና በትናንትና ስም ያለ ቅጥ የሚደገፉና በመንፈሳዊ ሕይወታቸው ሙት ሆነው ክርስቶስ ሳይሆን በክርስቶስ ስም ክሂደት የሚሰበክባቸው አብያተ ክርስቲያናት እጅግ ብዙ ናቸው:: ወደ ቀድሞው ክብራቸው ለመመለስ ተሐድሶ ብቸኛ መንገድ ነው:: አገራችን ኢትዮጵያ አሁን ለቆመችበት መልካም የዕድገት መሠረት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የአንበሳ ድርሻ ብትወስድም ተሐድሶን እንቢ በማለቷ ለቀጣዩ ዕድገትና ብልጽግና ሳታውቅ እንቅፋት ሆናለች::

ዕድሜ ጠገብ ሆኖ ያልታደሰው ክርስትናችን እንደ አገር ላለንበት ኋላ መቅረት፣ ድህነት፣ ጥላቻና ጠባብነት ዋና ምክንያት ነው:: በቃሉና በመንፈሱ ላለመታደስ በኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምክንያቶች ዋሻ የተደበቀውና በአብዛኛው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ልምምድና ትውፊት የተተበተበው ክርስትናችን ከእግዚአብሔር እውነት ያራቀንና ለአገራዊ ዕድገትም ብርቱ ሞጋች እንደሆነብን በቀጣዩ ምዕራፍ እንመልከት::

[121] የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣ *(1993 ዓ.ም)፣ በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፣ ገጽ 333

# ፮

# ያልታደሰው "ክርስትናችን" የዕድገታችን ሞጋች

*"ለእነዚያ ደግሞ እንደ ተነገረ ለእኛ የምሥራች ተሰብኮልናል፤ ዳሩ ግን የሰሙት ቃል ከሰሚዎቹ ጋር በእምነት ስላልተዋሐደ አልጠቀማቸውም።" (ዕብ. 4:2)*

**እ.ኤ.አ 2007 በኢትዮጵያ ማዕከላዊ ስታትስቲክስ ባለሥልጣን ይፋ በተደረገው የሕዝብ ቆጠራ ውጤት የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሕዝብ፡-** *"73,750,932 ሲሆን ከዚህም፡ 62.8% ያህሉ ክርስቲያኖች፣ ከዚህም ኦርቶዶክሳዊያን 43.5% ወንጌላዊያን (ፕሮቴስታንቶች) ደግሞ 18.6% እንዲሁም ካቶሊካዊያን 0.7% የሚሆነውን ድርሻ ይይዛሉ"*[122] **በማለት ገልጾአል። ምንም እንኳን የፕሮቴስታንቶች ዕድገት ከ10 ዓመት በፊት 11% ከነበረው አሁን ትልቅ ዕድገት ላይ እንዳለ ቢያመለክትም የኢትዮጵያን ክርስትና የሕዝብ ብዛት ዕድገት ወንጌል ወደዚህች ሀገር ከገባበት ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንጂ በወንጌላውያን የ100 ዓመት ዕድሜ ፍጹም መለካት የለበትም የሚሉ ምሁራን ጥቂት አይደሉም። ከአፍሪካ፣ ከአውሮፓ፣ ከሩቅ ምሥራቅ አገሮች፣ ከአሜሪካና ከላቲን አሜሪካ ቀድማ ወንጌልን ከተቀበለች 2000 ዓመታት ባስቆጠረች ሀገር ዛሬም ወንጌል በእርሷ ውስጥ ላሉት ብዙ ብሔር ብሔረሰቦች ባዕድ መሆኑ ያስገርማል።**

[122] *2007 Ethiopian census, first draft, Ethiopian Central Statistical Agency*





አገራችን ከሁሉ ቀድማ ወንጌል ብትቀበልም ዘግይታም ቢሆን ያቆየችውን የወንጌል መልዕክት ለሌላው ዓለም ማቀበል ለምን አልቻለችም? ብዙ አገራት ክርስትና ለሕይወት ለውጥ፣ ብርቱ ሠራተኛ እንዲሆኑና ለአገራቸው ሁለንተናዊና ፈጣን ዕድገት ጉልህ ድርሻ እንዳበረከተ ሲመሰክሩ ለእኛ እንደ ዕድሜው ለምን አልጠቀመንም? ለሚለው ጥያቄ የሚከተሉትን ምክንያቶች ማስቀመጥ ይቻላል።

> *ታሪክ በትክክል የሚጻፈው ነፃነት በሰፈነበት አገር ብቻ ነው።*
> *የፈረንሳይ ፈላስፋ ቮሊቴር 1737*

## ክርስትናችን ራስ ተኮር መሆኑ

የኢትዮጵያ ወንጌላውያንን የመቶ ዓመት ዕድገት ከደቡብ ኮሪያ የመቶ ዓመት ቤተ ክርስቲያን ዕድገት ጋር ብናነጻጽረው ዕድገታችንን እንዴት እንገመግማለን? በተለይ ያለፉት 21 ዓመታት ኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተ ክርስቲያናት ምቹና አንጻባራቂ የዕድገት ዘመን ነበር። እኛ ኢትዮጵያውያን ራስ ተኮር ባንሆን፣ በመከፋፈል መባዛት ሥራ ላይ ባንጠመድና ውስጣዊና ውጫዊ ዕይታዎቻችን ሚዛናዊ ቢሆኑ ዓለምን በወንጌል ለመድረስ የጌታ መሣሪያዎች በሆንን ነበር። በእርስ በርስ መወነጃጀልና በፍርድ ቤት ሙግት የባከነ የሰው፣ የገንዘብና የጊዜ ኃይል ለወንጌል ስርጭት ቢውል ኖሮ ከዚህ እጥፍ ዕድገት ሊገኝ እንደሚችል ብዙዎች በቁጭት ይናገራሉ። አሁንም ሌላ ጊዜ ተሰጥቶናል። ቁጭታችንን በሚበልጥ ሥራ እንወጣ። የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የባህር ዘለል ሚሲዮናዊ ራእይን ያላሳደገች፣ ከ23 ሚሊዮን በላይ ሕዝቦቿ ገና ወንጌልን በጭራሽ ያልሰሙባት፣ 18.6% የወንጌል አማኞች ብቻ ያሉባት፣

ከ5 ያነሰ ነገረ - መለኮትን በዲግሪ የሚያስመርቁ ኮሌጆችና አንድ የነገረ መለኮት ድህረ ምረቃ ትምህርት ቤት ያለባት፣ በአጠቃላይ በዕድሜ ቀድማ በተግባር ከሁሉ ኋላ የቀረች ትመስላለች። በወንጌል የተለወጡ ደቡብ ኮሪያውያን ለመንፈሳዊ ለውጥ፣ አልፎም ለኢኮኖሚያቸው ምጥቀት፣ ለማኅበራዊ ሕይወት መቃናትና ሁለንተናዊ ለውጥ ክርስትና ትልቅ ሚና እንደተጫወተ ሲመሰክሩ የተለያዩ ጥያቄዎች በውስጤ ይፈጠራሉ፡- በኢትዮጵያ ለ2000 ዓመታት፣ በደቡብ ኮሪያ ላለፉት 100 ዓመታት የተሰበከው ወንጌል ልዩነት አለው ወይ? ልዩነት ከሌለው አንድ ዓይነት ባይሆንም ተቀራራቢ ውጤት እንኳ ለምን አላስገኘም?

በቀለ ሻንቆ *"የክርስቲያን ኃላፊነት ሁለንተናዊ ዕድገትን ለማፋጠን"* በሚለው መጽሐፋቸው የምድራችን ክርስትና የተፈለገውን ውጤት እንዳላመጣ ሲገልጹ፡-

*የቤተ ክርስቲያን ዕድገትና የአማኙ ቁጥር መጨመር በሕዝቡ ኑሮና ሕይወት እንዲሁም በአገር ልማት ላይ ይህ ነው የሚባል ተጽዕኖ እስካሁን ሊያሳድር አልቻለም"*[123] ብለዋል::

በአገራችን ሲሰበክ የቆየው *"ወንጌል"* በአብዛኛው *ቃሉን* *መሠረት* ያላደረገ፣ ከሥራ ጋር የተፋታ ባዶ የሃይማኖት ሥርዓት እንደነበር መረጃዎች ይጠቁማሉ:: በኢትዮጵያ ሰፊ ጥናት በማድረግ የሚታወቁት ሪቻርድ ፓንክረስ *"በኢትዮጵያ በአንድ ዓመት (በ365 ቀናት) የሚከበሩት የሃይማኖታዊ በዓላት ብዛት 1281 እንደሆኑ በጥናታቸው ይፋ አድርገዋል::*[124] በዓሎቹን በዓመት ውስጥ ባሉት ቀናት ስናካፍል በቀን ውስጥ *3.5* በዓላት በድርብነት ይዘከራሉ ማለት ነው:: በቀን ከሶስት በላይ በዓላትን የሚያከብር ሕዝብ የሚያስደንቀው አለማደጉ ሳይሆን ቢያድግ ኖሮ ነበር:: እስከ ዛሬ እኛ ኢትዮጵያውያን ለሥራ ያለን ተነሣሽነት የወረደ እንደሆነ የሚነገረው የችግሩ ሥረ መሠረት የሚጀመረው ከዚህ ይመስለኛል::

## ክርስትና በስብከት ወይስ በኃይል?

ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ቤተ መንግሥት የገባው በትልቅ ክብርና ሰላም ሲሆን ከቤተ መንግሥት ወደ ሕዝቡ የተሰራጨው በአብዛኛው በወንጌል ስብከት ሳይሆን በነገሥታት አዋጅና በኃይል እንደ ነበር ታሪክ ይናገራል:: በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የነበሩ ነገሥታት ሃይማኖትን የፖለቲካ መሣሪያ አድርገው ይጠቀሙበት እንደነበር የአገራችን የታሪክ ሊቅ ዶክተር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ:- *"ሁሉም ሃይማኖቶች የመንግሥት ኃይል አገልጋይ መሣሪያዎች ናቸው"*[125] እንዳሉት ክርስትናም የእግዚአብሔርን መንግሥት ከማስፋፋት ይልቅ የነገሥታትን ፍላጐት መያዣ መሣሪያ ሆኖ በሰፊው እንዳገለገለ ታሪክ ምስክር ነው:: በንጉሥ ኢዛና ዘመን ክርስትና ወደ ኢትዮጵያ ሲገባ ሕዝቡ በጣዖት አምልኮዎች የተያዘ በመሆኑ ከ100 ዓመታት በላይ ክርስትናን ትልቅ ተቃውሞና ጦርነት ገጥሞት እንደነበር መዛግብቶች ያወሳሉ:: ከዚህም የተነሣ ወንጌልን በመስበክ የሰውን ልብ በመለወጥ ሳይሆን *"ክርስትና"* በጦርነት እንደተስፋፋ ዶክተር አስፋው እንዳሻው የነበረውን ሁኔታ እንዲህ ይተርካሉ :-

> *በአዲሱ የክርስትና አማኞችና በጥንቱ የጣኦት አማኞች መካከል ከ100 ዓመት በላይ በኢትዮጵያ ከፍተኛ የእርስ በርስ ጦርነት በመካሄዱ ከፍተኛ ጥፋት ደረሰ... ንጉሠ ነገሥቱን ይዘው ያሸነፉት ክርስቲያኖች የጥንት የሥልጣኔ ቅርሶችን ሁሉ የአምልኮ ጣዖት ነው በማለት የሚፈርሰውን አፈረሱት፤ የሚቀጠቀጠውን እየቀጠቀጡ፣ የሚቃጠለውን እያቃጠሉ ደምስሰው አጠፉት*[126]

[123] በቀለ ሻንቆ *(2000 ዓ.ም)፤የክርስቲያን ኃላፊነት ሁለንተናዊ ዕድገትን ማፋጠን፤*ኤኔክ አሳታሚ፤ ገጽ 155
[124] Richard Pankhurst and others (editors). *(April 1990)' Proceeding of the first National Conference of Ethiopia Studies,* ,p.165
[125] *የኢትዮጵያ ታሪካዊ መሠረቶችና መሣሪያዎች ገጽ 45*

[126] *ኢትዮጵያ የህዝቦች ስብጥርና የአገዛዞች አወቃቀር አጭር ታሪክ፣ (2004 ዓ.ም) ገጽ 34*





ይህ ጥናት እንደሚያመለክተው ከሆነ በጊዜው የኢትዮጵያ ክርስትና ጽድቅንና እውነትን፣ የክርስቶስን ሞትና ትንሣኤ በመስበክ ሳይሆን በኃይል እንደሆነ ምስክር ነው:: የአንድ ነገር ዕድገት መሠረት ወሳኝ እንደሆነ አንዘነጋ:: ይህም የተበላሸና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና መሠረት እንደሆነ ልብ እንበል:: ወንጌልና ኃይል አብረው አይሄዱም:: ኢየሱስና ሐዋርያት ወንጌልን ብቻ በመስበክ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል የሰዎችን ልብ እግዚአብሔር ለውጦ ክርስቲያን እንደሆኑ እንጂ በክርስትና ስም የሰዎችን ሃይማኖት እንዳስለወጡ መጽሐፍ ቅዱስ አይናገርም:: ዶክተር ሀብተማርያም አሰፋ ክርስትና በኢትዮጵያ የተስፋፋው በኃይል እንደሆነ ከላይ ያለውን አሳብ ሲያጠናክር:-

> *የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድ ጊዜ አሜን ብሎ ክርስትናን አልተቀበለም:: ከኢዛና ዘመነ መንግሥት እስከ ዐፄ ካሌብ ዘመነ መንግሥት ድረስ እርስ በርስ 150 ዓመታት ያህል ሲዋጋ ነበር እንጂ*[127] *ብለዋል::*

ከኢዛና በኋላ እስከ ምኒልክና ሌሎች ነገሥታቶችም እንደ ቀዳሚዎቻቸው *"ክርስትናን"* ለማስፋፋት የጣሩት በአብዛኛው ወንጌልን በመስበክ ሳይሆን በኃይልና እንደ ፖለቲካ መሣሪያ በመጠቀም እንደነበር: ላተውሬት ሲገልጹ:-

> *የአበሻው ቤተ ክርስቲያን ከነበረችባቸው ሁኔታዎች ጋሩና የተነሣ ለየት ያለ አጥቢያዊ ገጽታ ባሕሪይ አላት፣ ምኒልክና ሌሎችም ነገሥታት ከግዛታቸው መስፋፋት ጎን ለጎን በቅኝ የያዙአቸውን ሕዝቦች ይህን ይፋዊ (ኦፊሲሊያዊ) እምነት እንዲቀበሉ የግድ ብለዋቸው ክርስትናውን የግብር ይውጣ ከመቀበላቸው በስተቀር ቤተ ክርስቲያኒቱ የወንጌል ማዳረስ ተግባሪዋን ትታለች*[128] ብለዋል::

ወንጌል በእግዚአብሔር ኃይል እንጂ በሰዎች ሰይፍ ተደግፎ እንደሚሰራጭ መጽሐፍ ቅዱስ በአንድም ቦታ አይናገርም:: ዊሊያም ሼክስፒር እ.ኤ.አ ከ1603-1607 ባሉት ዓመታት እንደጻፈው በሚታመነው *"ማክቤዝ"* የተውኔት ድርሰቱ ማክዱፍ የተባለው ገጸ ባሕሪይ *"እኔ ቃል የለኝም፤ ድምጼ በሰይፌ ነው"*[129] እንዳለው በወንጌል አገልግሎት ቃል ጥሎ በሰይፍ መናገር አደገኛ ብቻ ሳይሆን ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው:: በኢትዮጵያ ክርስትና ሕይወት መሆኑ ቀርቶ ገገርው መደብ ሕዝቡን በአንድነት ለማሰር የሚጠቀምበት ገመድና የአገርን ሉዐላዊነት ለማስጠበቅ የሚጠቀሙበት የፖለቲካ በትር በመሆን አገልግሏል:: የኢትዮጵያ መንግሥት ሌላውን ቋንቋና ሃይማኖት አጥፍቶ በኢትዮጵያ ውስጥ ካሉት ቋንቋዎች አማርኛን ከሃይማኖቶች ደግሞ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንን ብቻ በማስጠበቅ በአገሪቷ አንድነት የማስጠበቅ ሙከራ አድርጎ እንደነበር ፕሮፌሰር ባሕሩ ዘውዴ ሌላ ጸሐፊን በመጥቀስ እንዳሰፈሩ በመጽሐፋቸው

[127] ሀብተ ማርያም አሰፋ(ዶ/ር) (1986 ዓ.ም)፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ ጥያቄዎችና ባሕሎች*፣ አዲስ አበባ፣ ገጽ 266-267
[128] *ላተውሬት 1971 ቅጽ 6 ገጽ 31*
[129] "I have no words; my voice is in my sword." *Muir, Kenneth,* (1884.) *Macbeth' The Arden Shakespeare,* Second Series, 11th ed.,

# የኦርቶዶክስ ክርስትና በሲዳማ

የኦርቶዶክስ ክርስትና በሲዳማ መቼና እንዴት እንደተሠራጨ *"የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል" መጽሐፍ ፀሐይ የተባለን ጸሐፊን ዋቢ በማድረግ፡- የኦርቶዶክስ ክርስትና ወደ ሲዳማ የደረሰው ወራሪውን የሚኒልክ ሠራዊት ተከትሎ እንደነበርና በሲዳማ ምድር በመጀመሪያ የተሠራው ቤተ ክርስቲያን የሺሻ ማርያም ሆኖ ዘመኑም በ1884 እንደነበር ይናገራል።*[135] ካለ በኋላ የኦርቶዶክስ ክርስትና እንዴት እንደተሰራጨ ደግሞ ሲናገር፡-

*የሃይማኖቱ አመጣጥም ከነፍጠኛውና ከመልከኛው ሥርዓት ጋር ስለነበርና ሥርዓቱም የሕዝቡን መሬት ወስዶ ጭሰኛና ገባር ባደረገበት ሂደት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን አጋር ስለነበረች በሕብረተሰቡ ዘንድ የነበራት ተቀባይነት እምብዛም ነበር። በሌላ መልኩ የኦርቶዶክስ እምነት ሳይሰበክ ሕዝቡ በግድ በአዋጅ እንዲጠመቅ ስላደረገ በወቅቱ ቤተ ክርስቲያኒዋ በነበራት የፖለቲካ ወገንተኝነት ሕዝቡ በተደጋጋሚ አልቀበልም ማለቱ ይነገራል።*[136]

*"የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባሕል" መጽሐፍ የአንድን አዛውንት* ምሬት እንዲህ አቅርቧል፡-

*ሕዝቡ ልብሶቻቸውን ገፍፈው ወንድና ሴቱን ራቁታቸውን አጥምቀዋቸዋል። ክርስትና ያስነሡዋቸው ለወንድማዊ እኩልነት ሳይሆን በክርስትና ስም ሕዝቡን ተከፋፍለው ለማሳረስና አገልጋዮች ለማድረግ ነበር። ይህን የተገነዘበው የሲዳማ ሕዝብ ከጣሊያን በፊት የነበረውን የገባሪነት ሥርዓት በክርስትና ስም ሊጭኑብን ነው በማለት ሸሽቶዋቸዋል። ሚሽኖች ግን መጥተው ወንጌልን ሲሰብኩ ሕዝቡም ተቀብሎዋቸው ወደ እነሱ ተመልሷል። የኦርቶዶክስ እምነት መሪዎች ግን የሲዳማ ሕዝብ የሚሽን እምነት በመከተሉ 'እኛ ክርስትና አስነስተናችሁ ሕዝቡን አከፋፍለው የሚያጠፉትን የሚሽኖች እምነት ለምን ትቀበላላችሁ? ሲሉ እኔ በወቅቱ የሰጧቸው ምላሽ፣ እናንተ ለእኛ ክርስትና ስታስተምሩ ወደ ቤተ ክርስቲያን አስጠግታችሁ የክርስትናውን ምስጢር መቼ አስተማራችሁን? ክርስትና ማንሣት የሃይማኖት ምስጢር ማስተማር ሆኖ እያለ እናንተ ግን እያንዳንዳችሁ አቅማችሁ የፈቀደውን ያህል 200 ወይም 300 ሰው ተከፋፍላችሁ። ልጆች መጡ እያላችሁ ወደ ጓሮዎችሁ አስማርታችሁ የቀረውን በክርስትና ሽፋን ስለጫናችሁብን ሸሽተናል የሚል ነበር። ከጣሊያን ወረራ በኋላ ሕዝቡ ክርስትና እንዲነሣ በአዋጅ ስለተነገረ አንድም ሰው ሳይቀር በአዋጅ ታዘው ሕዝቡ ወንዝ ወርደው ተጠምቀዋል።*[137] *የጣሊያን ወረራ እንዳበቃም የኢትዮጵያ መንግሥት ከስደት ወደ መንበረ ዙፋኑ ከተመለሰ በኋላ ኢትዮጵያውያን በአንድ ሃይማኖት መተዳደር አለባቸው ብሎ ፓትሪያርኩ መመሪያ በማውጣት ፀጉራቸውን በመላጨት ክርስትና እንዲነሡ በማስገደዱ ከአላታና ከሐዌላ የተወከሉ ለአበቱታ ወደ ንጉሡ እንደሄዱ በመጽሐፉ ተዘክሯል።*[138]

---

[135] የሲዳማ ብሔር ታሪክና ባህል፣ 2003 ዓ.ም ገጽ 233
[136] ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 233
[137] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 233*
[138] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 234*





በወቅቱ ስለነበረ ሁኔታ ሕዝቡ ስሜቱን በሥነ ግጥም እንዲህ ገልጾ ነበር፡-

## ሲዳምኛ

*Nugusaho Hayile Sillaase,*

*Hayile Sillaase qaalinni manna Kiritiiinna kayise.*

*Anera dunno gambayichi eino Hawasa daade:*

*Cimeeyye umma meendeenna bade labbanno mataate:*

*Meyaa labbaaha qodho tirreena lawanno Qulbate qaaqe.*

## ትርጉም በአማርኛ

*ኃይለ ስላሴ ንጉሥ ናቸው*

*ሁሉ ሰው ተጠምቆ በትእዛዛቸው፤*

*በጥምቀቱ ሰበብ ውሃ እየፈሰሰ፤*

*እስከ ሐዋሳ ደረሰ።*

*ያዛውንቶቹ ራስ ሲመለጥባቸው*

*የማሰሮ አንገት ገል አስመሰላቸው፤*

*ሴቱም ወንዱም ባዶ እራቁቱን ሆነ*

*አዲስ የበቀለም እንጉዳይ መሰለ።*[139]

መጽሐፍ ቅዱስ ይህን ድርጊት አያውቀውም። ኢየሱስ ወደ እኔ ኑ ብሎ ሰዎች በፈቃዳቸው ወደ እርሱ እንዲመጡ እንጂ በኃይልና በአዋጅ እንዲቀበሉት አላደረገም፤ ቅዱሳንም ክርስትናን በኃይልና የሰዎችን ፈቃድ በመጨፍለቅ እንዲያስፋፉ አላዘዛቸውም። ክርስትና በወንጌል ስብከትና በሰዎች በጎ ፈቃድ ላይ ተመሥርቶ የተሰራጨና የግለሰብን፣ የአገርንና የዓለም ታሪክ በአዎንታዊ መልኩ የለወጠ መለኮታዊ እውነት ነው። ከላይ በካፋና በሲዳማ ክርስትናን በኃይልና በአዋጅ የማስፋፋት ሙከራ ምንጩ የእግዚአብሔርን ቃል በቅጡ ካለመረዳት የመጣ እንጂ ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ጋር ምንም ዓይነት የአስተምህሮና ታሪካዊ ቁርኝት እንደሌለው መታወቅ አለበት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ጥንት፣ ዛሬና ለወደፊቱም የሰዎችን ነፃ ፈቃድ የሚያከብር የሕይወት፣ የለውጥ፣ የዕድገት መንገድና ብቸኛ የአዳም ዘር ሁሉ የመዳኛ መንገድ ነው።

---

[139] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 234*

ይነሣሉ:: የአገራችን ክርስትና እንደሚገባው ለራሳችን አልጠቀመንም ለአገርም ጠቃሚዎች አላደረገንም:: ለብዙዎች ክርስትና ከአባትና ከእናት የሚወረስ ሃይማኖት እንጂ የእግዚአብሔርን ቃል በግል በመረዳት፣ ለቃሉም በመታዘዝና የክርስቶስን እውነተኛ ወንጌል ለሌሎች በመመስከር፣ ለአገር ዕድገት፣ ለኢኮኖሚ ምጥቀትና ለዲሞክራሲ ማበብ የሚገባውን ሚና እንዲጫወቱ አላደረጋቸውም:: ከዚህም የተነሣ ቀድመን "ክርስትና" ተቀብለን በብዙ የኋለኞች ኋለኛ ሆነናል::

## ሐዋርያት ወንጌልን ያስፋፉት በጡንቻ ይሆን?

ኢየሱስን የሰቀሉ፣ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ የነበሩና በዚህ ጉዳይ ከማንም ጋር የማይደራደሩ አይሁዶች የጴጥሮስን ስብከት በበዓለ ሃምሳ ዕለት *"በሰሙ ጊዜ ጴጥሮስንና ሌሎችን ሐዋርያት ወንድሞች ሆይ ምን እናድርግ?"* (የሐዋ.2፡ 28) ሲሉአቸው ንስሐ እንዲገቡ በመርዳት በአንድ ስብከት 3000 በላይ አክራሪ አይሁዶችን በወንጌል የማረኩት በሰይፍ ሳይሆን በወንጌል ስብከት ነበር:: በሰማርያ ከተማ ሲሞን የተባለ ጠንቋይ አገርን እያስደመመ፣ የሕዝብን አዕምሮ በመግዛት ሀብታቸውን እየበዘበዘ እንደ ከተማ አምላክ ተፈርቶ ይኖር ነበር:: ፊልጶስ ወንጌልን በዚያ ከተማ ያሰራጨው በወንጌል ስብከት እንጂ የጠንቋዩን ቤት በማፍረስ አልነበረም::

> *ፊልጶስም ወደ ሰማርያ ከተማ ወርዶ ክርስቶስን ሰበከላቸው:: ሕዝቡም የፊልጶስን ቃል በሰሙ ጊዜ የተናገረውን በአንድ ድምጽ አደመጡ:: እርኩሳን መናፍስት በታላቅ ድምፅ እየጮኹ ከብዙ ሰዎች ይወጡ ነበርና ብዙም ሽባዎችና አንካሶች ተፈወሱ በዚያችም ከተማ ታላቅ ደስታ ሆነ:: ...ሲሞንም ደግሞ ራሱ አምኖ ተጠምቆም ከፊልጶስ ጋር ይተባበር ነበር (የሐዋ. 8፡ 4-8፡ 13)* ይላል:: መጽሐፍ ቅዱሳዊና አዲስ ኪዳናዊ የወንጌል ስርጭት ምሳሌ በአጭሩ ይህን ይመስላል:: ሐዋርያው ጳውሎስም ወንጌል የመለኮት ኃይል እንደሆነ ሲገልጽ፡- *"በወንጌል አላፍርምና አስቀድሞ ለአይሁድ ደግሞም ለግሪክ ሰው ለሚያምኑ ሁሉ የእግዚአብሔር ኃይል ለማዳን ነውና" (ሮሜ.1፡16)* ብለዋል::

ወንጌል የመለኮት ኃይል ሆኖ የሰውን የአፍ ምስክርነት እንጂ ጡንቻ አይፈልግም:: ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ የተሠራጨው የክርስትና ሃይማኖት ስም የተሰጠው ሥርዓት እንጂ የተቀበሉትን ሰዎች ሕይወት ለውጦ የለውጥ መሣሪያ የማድረግ ኃይል ያለው የወንጌል ቃል አልነበረም:: ክርስትና ዓለማትን የገዛው ጌታና ንጉሥ የሆነ የናዝሬቱ ኢየሱስ በገሃድ የሚሰበክበት መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት እንጂ ገገርዎች ተገገርዎችን የሚጫኑበት የፖለቲካ መሣሪያ አልነበረም:: ገገርዎች ራሳቸው ክርስትና በትክክል ቢገባቸው ኖሮ ለክርስቶስ ተገዝተው ክርስትናን እንደ መሣሪያ በመጠቀም ዜጐችን ለመግዛት ባልተነሡ ነበር:: የኢትዮጵያ ክርስትና ከመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ጋር የተፋታበት አንዱ ነጥብ ይህ ነው::





# ዐፄዎችና ክርስትና

### *ምሳሌ፡-ዐፄ ዮሐንስ*

ተክለ ጻድቅ መኩሪያ "*ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት*" በሚለው መጽሐፋቸው፡- ***ዐፄዎች በክርስትና ስም ሰዎችን ሲያሳድዱ፣ ሲያሠሩና ሲገድሉ እግዚአብሔርን ያገለገሉ ነው እንጂ ግፍ የሠሩ መስሎ አልታያቸውም ነበር***[143] *(መስመሩ በኔ)* ብለዋል:: ድርጊቱ ጸሐፊው እንዳሉት ከሆነ ቤተ ክርስቲያን ወንጌል ከጡንቻና ከሰይፍ ጋር በፍጹም ተያያዥነት እንደሌለው የእግዚአብሔርን ቃል እንዳላስተማረችና ዐፄዎች ክርስቲያን ተባሉ እንጂ የክርስትና መሠረት የሆነ የክርስቶስ የወንጌል ቃል ዕውቀት እንደሌላቸው ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊታቸው ያሳብቅባቸዋል:: በአገራችን በክርስትና ስም የተፈጸሙ ግድያና ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ደርጊቶችን ሁሉ እንደ ጽድቅ ሥራ መቁጠር ዋናው ምክንያት ክርስትናችን ሥጋዊ ልምድ እንጂ የቃሉ መሠረት እንዳልነበረው አንዱ ማስረጃ ነው:: የኢትዮጵያ ነገሥታት "ክርስቲያን" እንደነበሩ የታወቀ ነው:: የክርስትና ስም ቢኖራቸውም አብዛኛው ድርጊታቸው ክርስቲያን እንደነበሩ አያመለክትም:: ክርስቲያን የክርስቶስ ብርሃን በሕይወቱ የበራና የእግዚአብሔር ቃል በውስጡ ስለሚኖር በንግግሩ፣ በአስተሳሰቡ፣ በእርምጃውና በሥራው ክርስቶስን የሚያሳይ ሰው ነው::

በኢትዮጵያ ታሪክ ገናናና መንፈሳዊ እንደነበሩ ከሚነገርላቸው ነገሥታት መካከል አንዱ ዐፄ ዮሐንስ ናቸው:: በሕይወታቸው በሙሉ ለአገራቸው አንድነት በብርቱ የደከሙና ወገናቸውን ከጥቃት ለመታደግ ሲሉ ሕይወታቸውን የሠው ታላቅ መሪ ስለሆኑ አንጸባራቂ ታሪካቸው በዘመን ሁሉ ይወሳል:: አሁን እየኖርንባት ላለችው ኢትዮጵያ የነፍስ ዋጋን ከከፈሉ የአገራችን ብርቅዬና ታላቅ መሪዎች አንዱ በመሆናቸው እንኮራባቸዋለን:: ዐፄ ዮሐንስ ለሃይማኖታቸው ቀናኢ እንደነበሩ፤ ከዚህም የተነሣ በኢትዮጵያ ታሪክ *"ዮሐንስ መነኩሴውና ወታደሩ"*[144] እየተባሉ እንደሚጠሩ ተጽፎዋል:: ለኚህ ታላቅ ሰው አድናቆት ይገባቸዋል:: በክርስትና ስም ያደረጉት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ድርጊቶች ግን ከተነገረላቸው የመንፈሳዊነት ምስክርነት ጋር በብዙ ይጋጫል:: ዐፄ ዮሐንስም እንደ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ በክርስትና ስም ኃይልን እንደተጠቀሙ መረጃዎች ይጠቁማሉ:: ዶክተር ላጵሶ ጌ.ድሌቦ "*የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ*" በሚለው መጽሐፋቸው፡-

> *በአሥራ ዘጠነኛው ምዕተ ዓመት በዘመናዊ ጦር መሣሪያ በታጠቁ የኢትዮጵያ ነገሥታት በተለይም በዐፄ ዮሐንስ ዘመነ መንግሥት በአንድ በኩል የመንግሥቱን የክርስትና ሃይማኖት በኃይል የፖሊሲ ተግባር ለማስፋፋት ያደረጉት... እስከ ዛሬ ድረስ በመካሄድ ላይ ላሉት ውስብስብ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ፣ የሃይማኖት፣ የብሔረሰብ፣ የቋንቋ፣ የባህል ችግሮች ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደአደረጉ ግልጽ ነው*[145] ብለዋል::

---

[143] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ(1982 ዓ.ም)፣ *ዐፄ ዮሐንስ እና የኢትዮጵያ አንድነት*፣ ኩራዝ አሳታሚድርጅት፣ 76

[144] ሐረ አትክንስ፣ *የኢትዮጵያ ታሪክ*፣ ገጽ 26

[145] ላጵሶ ጌ.ድሌቦ (ዶ/ር) (1985 ዓ.ም) *የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ* ገጽ 150

የጎበጠው የክርስትና አስተምህሮ የሚቃናው በመጽሐፍ ቅዱሳዊ አስተምህሮ እንጂ በኃይል እርምጃና በማክረር አይደለም:: ሰይፍ ሰይፍን እንጂ የጸጋን ወንጌል አይወልድም:: ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ አለብን::

የእግዚአብሔር ቃል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ለዘመናት ከተያዘችበት ቀለበት የመውጫ ብቸኛ መንገድ ነው:: በአገራችን በኃይልም ቢሆን ክርስትናን ማቆየታችንና ኢትዮጵያን የ*"ክርስቲያን ደሴት"* ማለታችን በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጠራል:: አሳዛኝ ጎኑ ግን ከቃሉ ውጭ በኃይል፣ በግድያና ሌሎችን እያሳደድን ባስጠበቅነው ኢ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ "ክርስት"ና የእግዚአብሔር ቃልና አብሮነት መታጣቱ ነው:: ብዙ ክትባቶች በሽታ መሆን ከማይችለው ሕዋስ ተቀሚመው ለሰዎች ሲሰጡ ያ በሽታ ሰውነታቸውን ለማጥቃት ሲመጣ ቀድሞውኑ በክትባት መልክ ሰውነት ውስጥ የነበረው የበሽታው ሕዋስ በሽታን ይከላከላል:: እንዲሁም የወንጌልን እውነት ያልተረዳ፣ የክርስቶስን ቤዛነት አምኖ ኃጢአቱን ተናዝዞ የልጅነትን ሥልጣን ያልተቀበለ፣ ከዓለም ከፋትና እርኩሰት ያልተለየና ደቀመዝሙር ያልሆነ ከክርስቲያን ቤተሰብ በመወለዱ /"ክርስቲያን" በመባሉ/፣ በ40/በ80 ቀኑ በመጠመቁና የክርስቲያን ስም ስለተሰጠው ክርስቲያን የሆነ መስሎት መጽሐፍ ቅዱሳዊና ሕይወት ለዋጭ ክርስትና ሲነገረው በፍጹም የማይታገስ "አማኝ" ብዙ ነው:: በሌላውም ሃይማኖት ቢሆን እጅግ ብርቱ ተከራካሪና ኃይልን ስለ ሃይማኖታቸው ከመጠቀም የማይመለሱ ሰዎች ስለ ሃይማኖታቸው በቂና የጠለቀ ዕውቀትና ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች ናቸው::

የክርስትና መታወቂያችን ፍሬያችን እንጂ ዕድሜያችን አይደለም:: ጌታችን ይህን ሲናገር *"ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ ...መልካም ዛፍ ክፉ ማፍራት ወይም ክፉ ዛፍ መልካም ፍሬ ማፍራት አይቻለውም:: መልካም ፍሬ የማያደርግ ዛፍ ሁሉ ይቈረጣል ወደ እሳትም ይጣላል:: ስለዚህም ከፍሬያቸው ታውቋቸዋላችሁ"* (ማቴ.7:16-19):: የዕድሜያችንና የቁጥር ብዛታችን ብቻቸውን እግዚአብሔር ከእኛ ጋር የመሆን ማረጋገጫ ሊሆኑን በፍጹም አይችሉም:: አይሁዶች ለአራት ሺ ዓመታት የመሲህ የኪዳን ቃል ይዘው መቆየታቸው ከኪዳኑ ጋር እንዳይተላለፉ አላደረጋቸውም:: የእግዚአብሔርን ቃል በግልጽ እየተቃወሙ ረዥም ዕድሜ ያስቆጠሩና በአስደማሚ ፍጥነት በማደግ ላይ ያሉ ሃይማኖቶች በዓለማችን ብዙ ናቸውና:: ለምሳሌ:- በዋርዊክ ዩኒቨርሲቲ መምህር ፕሮፌሰር ሮበርት ጃክሰን ሲናገሩ:- ማን እንደመሠረተው የማይታወቅ ህንዱይዝም ሃይማኖት ዕድሜው 5,000 ዓመታት ሲሆን ከ700 ሚሊዮን በላይ ተከታዮች አሉት:: የጃፓኖች ቀዳሚ ሃይማኖት የሆነው ሽንቶይዝም የተጀመረው ከክርስቶስ ልደት በፊት ሲሆን በብዙ ሚሊዮን የሚገመቱ ጃፓናውያን በዚህ ሃይማኖት ይኖራሉ::

ከላይ የተጠቀሱ እነዚህ ዕድሜ ጠገብና በአጠቃላይ ከአንድ ቢሊዮን በላይ ተከታዮች ያሏቸው ሃይማኖቶች ዕድሜያቸውና የሰው ቁጥር ብዛት ብቻውን





በእግዚአብሔር ፊት ተቀባይነትንና ትክክለኛነትን አያጎናጽፋቸውም:: መጽሐፍ ቅዱስ ስለ መዳን ሲናገር:-*"መዳንም በሌላ በማንም የለም፤ እንድንበት ዘንድ የሚገባን ለሰዎች የተሰጠ ስም ከሰማይ በታች ሌላ የለምና"(የሐዋ.4:12):: "ልጁ ያለው ሕይወት አለው፤ የእግዚአብሔር ልጅ የሌለው ሕይወት የለውም"(1ዮሐ.5:12)::* በማለት በግልጽ አስቀምጦታል:: የሰው ልጅ ትምክህት በእግዚአብሔር ቃል በተገለጸው በክርስቶስ ኢየሱስ በወንጌል እውነት ላይ መመሥረትና በተዘጋጀለት የምህረት መንገድ በጸጋ መዳን ነው:: ከዚህ ውጪ ሞት ነው::

በአጠቃላይ የክርስቶስ ቤዛነት የማይሰበክበት፣ ጸጋው በእምነት እንዳዳነን በግልጽ የማይታወጅበት፣ ሰዎች ድነታቸውን በሥራ ለማግኘት ደፋ ቀና እንዲሉ በሚደረግበት፣ ከቃሉ ይልቅ በቆየው አገራዊ ሃይማኖታዊ ሥርዓት ያለቅጥ የሚሞገስበት *"የአገራችን ክርስትና"* የትም አላደረሰንም፤ የትም አያደርሰንምም:: እግዚአብሔርን በቃሉ መንገድ እንጂ ከቃሉ ባፈነገጡ ልምዶቻችን አናገኘውም:: ወደ ቃሉ መመለስ አለብን:: ተሐድሶ! ተሐድሶ! ተሐድሶ! ያስፈልገናል:: እሥራኤላውያን በኃጢአታቸው ከእግዚአብሔር እጅግ ርቀው፣ የእግዚአብሔር ቃል ብርቅ ሆኖና ራእይ ጠፍቶ ቤተ መቅደስ ነውር የሚፈጸምባት ዋሻ ሆና ነበር:: በዚያ ዘመን እስራኤላውያን ከፍልስጥኤማውያን ጋር ለመዋጋት በወጡ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል በውስጣቸው ሳይኖርና ከእርሱ ጋር ያላቸው ግኑኙነት ፈርሶ የኪዳኑን ታቦት ይዘው ቢዘምቱም ከሽንፈትና ከሞት አልታደጋቸውም::

*"ፍልስጥኤማውያንም የእግዚአብሔርን ታቦት ወሰደው ወደ ዳጎን ቤት አስገቡት በዳጎንም አጠገብ አኖሩት"(1ሳሙ.5:2)::*

ልባችን ለእግዚአብሔር ካልተሸነፈ ለእርሱ በምናደርገው ሥርዓት ብዛት እርሱ ዘንበል አይልልንም፤ በጠላቶቻችንም ላይ ድል አይሰጠንም:: ረሃብ፣ እርዛት፣ ጦርነት፣ ድህነት፣ ኋላ ቀርነት፣ በሽታ፣ ጥላቻና ያለመቀባበል፣ የታሪካችን አካል ሆነው በምድራችን የገነኑት ከዚህ የተነሣ ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል የበላይነትን ባልያዘበት የንስሐ ልብና የተሐድሶ ፍላጎት በሌለው የረዥም ዘመን ክርስትናችን ብቻ እየተኩራራን መጓዝ ከቀጠልን ዕድሜን ከመቁጠር ያለፈ ክርስትናችን እንደ ሌሎቹ አይጠቅመንም፤ ጠቃሚዎችም አያደርገንም:: ከድግግሞሽ፣ ከሰዋዊ ወግ ዘበኝነትና ከባዶ ሃይማኖተኝነት ያለፈ እግዚአብሔር ወዳዘጋጀልን በረከት ቤተ ክርስቲያንንና አገርንም ለመምራት እንደ ሌላ አገር ክርስቲያኖች ዐቢይ ሚና መጫወት አንችልም:: መፍትሔው መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተሐድሶ ነው:: ያለፈውን የምናነሳው የመጣንበትን መንገድ ዞር ብለን ለማየት፣ ያለንበትን ለማወቅ፣ መጭውን በተሻለ ራእይ ለመተለም፣ ከስህተታችን ለመማር፣ የባሰ ታሪካዊ ስህተት እንዳንፈጽም፣ ስለ ራሳችንና ስለአባቶቻችን በደል በእግዚአብሔር ፊት በተሰበረ ልብና መንፈስ ለይቅርታ ለመውደቅ፣ ኢትዮጵያ ተባርካ ኢትዮጵያውያን ለዓለም በረከት በወንጌል ምክንያት እንድንሆን ነው::

# የቤተ ክርስቲያን ዝምታ ለምን?

በወቅቱ ቤተ ክርስቲያን የሥርዓቱ ደጋፊ ሳትሆን ራስዋ የሥርዓቱ መሪዎችን የምትቀባ፣ ምክር የምትሰጥና ድምፅዋ በቤተ መቅደስና በቤተ መንግሥት እኩል የሚሰማላት ሆና ሳለች በወንጌል ስም ዘግናኝ ድርጊቶችን ዐዌዎች ሲፈጸሙ ለምን ዝም አለች? ቤተ ክርስቲያን በጊዜው ከዐዌዎቹ ጋር ጣትና ቀለበት ብትሆንም ሰይፍና ወንጌል አብሮ እንደማይሄዱ ያስተማረች አይመስልም:: ይህ በኢየሱስ፣ በሐዋርያትና፣ በጥንት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የማይታወቅና በቃሉም የተወገዘ ድርጊት ቢሆንም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በዝምታ ለምን እንዳለፈች አይታወቅም:: ቤተ ክርስቲያን በጊዜው ለመቃወም ቢያስፈራትም በኋላ በወንጌል ስም የተደረጉ ኢሰብዓዊ ድርጊቶችን ለምን አላወገዘችም? ዛሬም እንኳ ያን ድርጊት ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ እንደነበር ሲነገር አይሰማም፣ ሲጻፍም አይታይም:: ይህን ጥያቄ ማንሣትና መጻፍ በራሱ በዚህ ዘመን ባይሆን ኖሮ እንደሚያስወግር የታወቀ ነው:: እንዲያውም ያን ዘግናኝ ድርጊት በክርስትና ስም የፈጸሙ ሰዎች አሉታዊ ድርጊታቸው በአንዳንዶች ዘንድ እንደ ልዩ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ገድል ተደርጐ መወሰዱ ያሳዝናል::

በክርስትና ስም ዛሬ ገሃድ የወጣ በሰይፍ የመዝመት አዋጅ ባይኖርም በአንዳንዶች አንደበት አልፎ አልፎ የሚሰማው አደገኛና የኃይል መፈክር መሠረቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካልሆነ ካለፈው ታሪካችን ስላለመሆኑ መካድ ይቻል ይሆን? የመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና ዓለምን ያንበረከከው በነገሥታትና "በክርስቲያኖች" ሰይፍ ሳይሆን በመንፈስ ቅዱስ ኃይል በተሰበከው ሰማያዊ ወንጌል ነው:: ቤተ ክርስቲያን ለወንጌል ትሞታለች እንጂ ስለ ወንጌል አትገድልም:: ቤተ ክርስቲያን የመንፈስ ሰይፍ የሆነ የእግዚአብሔር ቃል እንጂ የሥጋ ሰይፍ አልነበራትም፤ ዛሬም የላትም፤ ወደ ፊትም አይኖራትም:: የወንጌል ስብከት ከሌለ እውነተኛ ክርስትናም ሆነ ቤተ ክርስቲያን በዓለም ልትኖር በፍጹም አትችልም:: ሰው ልቡ በወንጌል ካልተለወጠ በሃይማኖት ስም ሌላውን ከመግደል እንደማይመለስ ታሪክ አሳይቶናል:: ለውጥ ደግሞ ከድርጊት ሳይሆን ከአመለካከት እንደሚጀምር መዘንጋት የለበትም:: ስለ ጠንካራ የእምነት አቋሚቸውና የኮሚኒዝም የክሂደት መንፈስ በገሃድ በመግጠማቸው በደርግ የተገደሉ የኢትዮጵያ ወንጌላዊት መካነ ኢየሱስ ቤተ ክርስቲያን ዋና ጸሐፊ የነበሩ ቄስ ጉዲና ቱምሳ ሲናገሩ፣

> *እኛ ክርስቲያኖች የማመን መብታችንና እምነት እንዲስፋፋ ያለን ምኞት እንዲከበር ከፈለግን፣ የማያምኑ ሰዎችና ሊያምኑ የማይችሉ ሰዎችንም መብት ማክበር አለብን::[158] ብለዋል::*

የመንፈስ ሰይፍ የሆነውን ቃሉን ጥሎ የሥጋን ሰይፍ ለማንሣት የሚቋምጥ *"ክርስትና"* መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም:: በዚህ ዓይነት አመለካከት ዛሬም የሚሰቃዩ ካሉ ይህ የተሸናፊነት፣ የፍርሃትና ወንጌልን በፍጹም ያለማወቅ ምልክት ነው:: እነዚህ ሰዎች ወደ መስቀሉ ፍቅር፣ ለሰዎች ልጆች ድነት ወደ

[158] ጉዲና ቱምሳ፣ *ምስክርነት ደቀመዝሙርነት*፣ ገጽ 31



ፀጋአብ በቀለ

ተሰጠው የክርስቶስ ጸጋ፣ በንስሐ በር በመዝለቅ በወንጌል ዓለምን ለመለወጥ እንደ ገና በቃሉና በመንፈሱ መወለድ አለባቸው:: ለዚህም ለኢትዮጵያ ክርስትና ተሐድሶ ያስፈልገናል:: ኢትዮጵያ የሰላም ወንጌል እንጂ የሥጋ ሰይፍ ይበቃታል:: መገዳደላችን ከእግዚአብሔር ጋር ከመጣላት፣ በቀልን በውስጣችን አርግዘን እያቃሰትን ከመኖር፣ ኋላ ከመቅረት፣ ምድሪቷ ከእርግማን በታች እንድትወድቅ ከማድረግ፣ በፈረንጅ በጥቁሩ አገር ለእንጀራ ልመና ከመሰደድ በቀር ለምንም አልረባንም:: ወንጌል ለዚህ ሁሉ ብቸኛ ፈውስ ነው:: ቃሉም እንዲህ ይላል:-

> *"መጥቶም ርቃችሁ ለነበራችሁ ለእናንተ ሰላምን የምሥራች ብሎ ሰበከ፤ በእርሱ ሥራ ሁላችን በአንድ መንፈስ ወደ አብ መግባት አለንና" (ኤፌ.2:17):: "በሩቅም በቅርብም ላለው ሰላም ሰላም ይሁን እፈውሰውማለሁ ይላል እግዚአብሔር:: ክፉዎች ግን እንደሚንቀሳቀስ ባሕር ናቸው ጸጥ ይል ዘንድ አይችልምና ...ለክፉዎች ሰላም የላቸውም ይላል አምላኬ" (ኢሳ.57:21)::*

# ከክርስቶስ ምን እንማራለን?

ክርስትናን ከክርስቶስ እንማር:: የክርስቶስ ቃል ያልገነነበት ክርስትና ከዘላለም ሞትና ኩነኔ የማይታደግ ባዶ ሃይማኖት ነው:: ክርስቶስ የክርስትና መንገድ ነው:: ከእርሱ ምን እንማራለን? መጽሐፍ ምን ይላል?

> *"እርሱ ኃጢአት አላደረገም ተንኰልም በአፉ አልተገኘበትም: ሲሰድቡት መልሶ አልተሳደበም መከራንም ሲቀበል አልዛተም ነገር ግን በጽድቅ ለሚፈርደው ራሱን አሳልፎ ሰጠ:"* (1ጴጥ.1:22-23)::

ሐዋርያው ጳውሎስ በስደትና በትልቅ ፈተና ተከበው ለነበሩ ለሮም ክርስቲያኖች እነርሱን ለሚያሳድዱና ለሚጠሉ አጻፋቸው ምን መሆን እንደሚገባ እንዲህ ብሎ መክሮ ነበር:-

> *"የሚያሳድዱአችሁን መርቁ፣ መርቁ እንጂ አትርገሙ:: ...ልባሞች የሆናችሁ አይምሰላችሁ:: ለማንም ስለ ክፉ ፈንታ ክፉን አትመልሱ በሰው ሁሉ ፊት መልካም የሆነውን አስቡ:: ...ተወዳጆች ሆይ ራሳችሁ አትበቀሉ ...ጠላትህ ግን ቢራብ አብላው ቢጠማ አጠጣው ይህን በማድረግህ በራሱ ላይ የእሳት ፍም ትከምራለህና:: ክፉውን በመልካም አሸንፍ እንጂ በክፉ አትሸነፍ"* (ሮሜ.12:12-21)::

ሌሎችን መውደዳችንና የወንጌል ተከታዮች መሆናችንን የሚገለጸው ግን የዳንበትን ወንጌል ለማይወዱንና ለሚቃወሙን ሰዎች በፍቅር ለማድረስ ስንጨክን ብቻ ነው:: ክርስቶስ ጠላቱ ወደ ሆነው ሰው ልጅ የመጣው በሰይፍ ሳይሆን በወንጌል ነው:: ወግ አጥባቂና የሃይማኖት አክራሪ ለሆኑ አይሁዶች ወንጌልን ሰበከላቸው እንጂ ሰይፍ አልመዘዘባቸውም:: ኢየሱስ ሰዎችን ያዳነው ለሰዎች ራሱን አሳልፎ በመስጠት እንጂ ለሃይማኖቱ በሰይፍ በመዋጋት አልነበረም:: የክርስቶስ መንገድ የመስቀል መንገድ እንጂ የሰይፍ መንገድ አይደለም:: መስቀል ተሸክመን እርሱን እንድንከተል እንጂ በእርሱ ስም ሌላውን ሰው መስቀል እንድናሸክም አልተጠራንም::

ኢየሱስ የሰጠን ሃይማኖትን ሳይሆን ሕይወቱን ነው:: እርሱ ራሱ ሲናገር:- *"እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"* (ዮሐ.10:10) በማለት ሃይማኖት ሳይሆን ሕይወቱን እንደሰጠን ተናግሯል:: በኢትዮጵያ "ክርስትናን" በኃይል ለማስፋፋትና ሰዎችንም በግድ በማጥመቅ እንዲቆርቡ በማድረጋችን ብዙዎች ክርስቲያን መባልን እንጂ በእውነት ክርስቲያን ለመሆን ደንታ ቢስ እንዲሆኑ ምክንያት ሆነናል:: ክርስቶስ የማይታወቅበት ክርስትና በአገራችን እንዲንሰራፋ ምክንያት ሆነናል:: ብዙዎች ክርስቲያን ስለመሆናቸው እንጂ ስለ ጽድቅና ስለ ቅድስና ኑሮ፣ ያልዳነውን ዓለም በወንጌል ስለመድረሲ፤ የማያምኑትን ሰዎች ስለመውደድ፣ ስለመዳናችንና ስላዳነን ጌታ ስለመመስከር፣ ለዓለም እውነተኛ ብርሃንና ጨው ስለመሆን መናገር አልለመዱም:: የክርስትና ሃይማኖት እንዳለን እንጂ የክርስቶስ ተከታዮች እንደሆንን አንደበታችንም ሆነ ሕይወታችን አይናገርም::

በክርስትና ሃይማኖት ስም መቁጠር የማይቻል በዓላትን እያከበርን ስለኖርን ለሥራ ባለን አጅግ የወረደ አመለካከት አገራችንን የድሆች ዋሻ አድርገናታል:: ዛሬ ያን የተዛባ የሥራ ባሕላችንን ለመለወጥ መንግሥት፣ ቤተ ክርስቲያንንና ዜጎችን ብዙ ዋጋ እየከፈልን ነው:: ከሁሉ በጣም አሳዛኙ በኢትዮጵያ ክርስትና ለድርሳናት፣ ለገድላት፣ ለሰማዕታት፣ ለቅዱሳን አበው ትልቅ ቦታ መስጠቱ ባይከፋም ለኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ያ ቦታ መነፈጉ ነው:: ክርስቶስ ለአገራችን ክርስትና ባዕድ ይመስላል:: በአጠቃላይ የኢየሱስ ወንጌል በኢትዮጵያ በትክክልና እንደሚገባ በእውነት አልተሰበከም:: ለዚህም በሁለት ሺ ዓመት ያፈራነውን ፍሬ ብቻ ማየቱ ከበቂ በላይ ነው:: ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም በአዲስ ታይምስ መጽሔት:-

*የኢትዮጵያ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አሁንም እውነቱን አላወጣችም፤ አንድም ለሹመት ያካበከበ ጳጳስ የክርስቶስን ጸሐየ ጽድቅነት አምኖና ተቀብሎ እውነቱን ለመናገር የደፈረ አልተሰማም::*[159]

በማለት የክርስቶስ እውነት በዚህች ምድር እንደሚገባው እንዳልተሰበከ ለመግለጽ ጥረዋል:: ለወንጌል ያልተሰጠና ወንጌልን ለሌሎች ያልሰጠ ሰው ወንጌልን በትክክል አልተቀበለም:: የወንጌል እውነት ሲገባን በወንጌል ከመኖር እኩል ወንጌልን ለሌሎች በማድረስ ሂደት ሞት እንኳን ቢመጣ ራሳችንን በደስታ ስለሌሎች መዳን አሳልፈን እንሰጣለን እንጂ ማንንም ለመግደል አናደባም:: ቃሉም:- *"እርሱ ስለ እኛ ነፍሱን አሳልፎ ሰጥቶአልና በዚህ ፍቅር አውቀናል፤ እኛም ስለ ወንድሞቻችን ነፍሳችንን አሳልፈን እንድንሰጥ ይገባናል"* (1ዮሐ.3:16) ይላል::

---

[159] አዲስ ታይምስ፤ *ቅፅ1፣ ቁ8 ህዳር 2005 ዓ.ም ገጽ 30*





## ከሰይፍ የተወለደ ሰይፍ

*ዐፄ ዮሐንስ በግድና በኃይል... እምቢተኛ የሆነው አፍንጫው እየተፎነነ ምላሱ እየተቆረጠ የጭካኔ ቅጣት ተቀበለ:: የፈራው ክርስትና ተነሣ:: የቀረው አገሩን ጥሎ የዐፄ ዮሐንስ ሥልጣን ወደ ማይደርስበት የጠረፍ ግዛቶችና የጎረቤት አገሮች ተሰደደ::*[160] *በስደት ሄደው ከሃይማኖት ወገኖቻቸው ጋር ተደባልቀው በዐፄ ዮሐንስ ላይ ሲያሴሩ የቆዩትና በመጨረሻም በ1881 ዓ.ም በመተማ ጦርነት ሊበቀሏቸው የቻሉት::*[161]

የመንግሥት አሐዳዊነት ለመንግሥቱ ጥንካሬ መደላደል የመሆኑን ያህል ያለ አግባብና በግድ በሕዝብ ኅሊናዊ ነጻነት ላይ ሲጫን ግን ለሕዝብና ለአገር መበታተን ዋነኛ መነሾም መሆኑን እንደገና ለማጤን እንገደዳለን::[162] ዶክተር ላጵሶ በግምት ከ1270-1577 በሰሎሞናዊ መንግሥትና በእስላሙ የዋለስማ ሱልጣኖች መካከል የመሬት፣ የንግድ፣ የሃይማኖት፣ የሥልጣንና የጉሳ ጦርነቶች ለረጅም ጊዜ እንደተካሄዱ፤ ሰሎሞናውያን ወታደራዊ የኃይል ሚዛን በማግኘት እስላሞችን በጭቆና ሥርዓት ሲገዙ ቆይተው በመጨረሻም ምዕራፍ በ16ኛው ምዕተ ዓመት እስላሞች በኢማም አህመድ ግራኝ መሪነት ባካሄዱት የበቀል ጦርነት በክርስቲያን መንግሥትና ኅብረተሰብ ላይ በሕይወትና በንብረት ከፍተኛ ጥፋት እንዳደረሱ[163] ጽፈዋል:: ከዚህም የተነሣ የአንድ አገር ሕዝቦች በሃይማኖትና በፖለቲካ ተከፋፍለው ባደረጉት የእርስ በርስ ጦርነት በሺዎች የሚገመቱ ዜጎች ተሰውተዋል፤ የአገር ሀብት ወድሞአል፤ ምትክ የሌላቸው ቅርሶች ዶጋ አመድ ሆነዋል፤ አብያተ ክርስቲያናትና ገዳማት ተቃጥለዋል፤ እንዲሁም እጅግ ብዙ ካህናት ተገድለዋል:: ይልማ ደሬሳ በኢትዮጵያ ሽምብራ ኩሬ *(የዛሬ ሞጆ አካባቢ)* በሚባል ቦታ በክርስቲያኖችና በሙስሊሞች መካከል የተካሄደውን የእርስ በርስ ጦርነት ዘግናኝ እልቂት እንዲህ አስፈረዋል::

*በዚያች ቀን ሽምብራ ኩሬ ላይ የሞቱት የኢትዮጵያ ሰዎች ከክርስቲያኑ ሠራዊት 12000፣ ከእስላሞች 6000 የሚበልጡ ወታደሮችና መኮንኖች ሲል ታሪክ መዝግቧል:: ...ሽምብራ ኩሬ የኢትዮጵያ ታሪክ መንገድ የተለወጠችበት ቀንና ቦታ ነች::*[164] ብለዋል::

አስደናጋጩ ነገር ዛሬም የሃይማኖት እኩልነትን የሚገልጽ ሕግ ልጓም ባያበጅላቸው ኖሮ ሰይፍ ለማንሣት የማይመለሱትን መቁጠር ይቻል ይሆን? ከላይ እንደተመለከትነው በኢትዮጵያ የሃይማኖትን አህዳዊነት በማስፈን ለሕዝብ አንድነት የማይበጅ ርካሽና ስውር የፖለቲካ ርዕዮተዓለም ለማስፋፋት ታቅደው የተካሄዱ ግጭቶችና ጦርነቶች የንጹሃንን ደም በከንቱ ከማፍሰስ፣ የአገርን ሀብት ከማውደም፣ በድህነትና በተስፋ መቁረጥ ሸለቆ ከመውደቅ፣ የአገርን ታሪክ ከማበላሸት፣ አብሮ የመኖርን መንፈስ

---

[160] ወንድዬ አሊ፤ ገጽ 63
[161] ተክለ ጻድቅ መኩሪያ፣ (1982 ዓ.ም) ገጽ 200
[162] ወንድዬ አሊ፣ ገጽ 63
[163] ላጵሶ ጌ.ድሌቦ (ዶ/ር) (1999 ዓ.ም) ፣ *የኢትዮጵያ የመከራ ሥርዓትና የኤርትራ ጥያቄ፣* ገጽ 143
[164] *ይልማ ደሬሳ (1999 ዓ.ም) ፣ የኢትዮጵያ ታሪክ በአሥራ ስድስተኛው ክፍለ ዘመን፣ ሁለተኛ እትም፣* አዲስ አበባ ገጽ 66

ከማደፍረስ፣ የፈረሰችና የወደመች አገር ለቀጣዩ ትውልድ ከማውረስ፣ የቂምና የበቀል መንፈስ ከማስፋፋትና ምድርቷን ከእርግማን በታች ከማድረግ ያለፈ ሌላ ትርፍ አላመጣም:: ይህን ርካሽና ኋላ ቀሪ አጀንዳ ይዘው ዛሬም የሚነሡ ካሉ እነርሱም ከታሪክ የማይማሩና ይህች በብዙ የተጐዳችን አገር ለማፈራረስ የቆረጡ የጥፋት መልዕክተኞች መሆን አለባቸው:: ይህ ህቡዕ አጀንዳ ድሮም አልተሳከም አሁንም አይሳካም:: ከዚህም በኋላ አይሳካም:: ኢትዮጵያ እስላም፣ ክርስቲያኑ እንዲሁም ሃይማኖት የለሽና ባሕላዊ ሃይማኖት ተከታይ ሕዝቦች በአንድነት የሚኖሩባት አገር ነበረች፤ አሁንም ናት:: ክርስትና ለሰዎች ልጆች የሞተው ጌታ የሚሰበክበት ሕይወት እንጂ በክርስትና ስም ሰዎች የሚገዳደሉብት ሥጋዊ ግንባር በፍጹም አይደለም:: የሰውን ነፍስ የፈጠረ እግዚአብሔር ሰውን መግደል አቅቶት ሰው በሃይማኖት ስም ሌላውን ሰው እንዲገድል አይልክም:: ለወንጌል እውነት ከገደሉን እንድንሞት እንጂ ሰዎች ወንጌልን ስላልተቀበሉ ወይም ለጽድቅ ቀናዒ በመሆን ሌሎችን እንድንገድል መጽሐፍ ቅዱስ አያስተምረንም:: እንዲያውም *"ነፍሰ ገዳይም የሆነ ሁሉ የዘላለም ሕይወት በእርሱ እንዳይኖር ታውቃላችሁ" (1ዮሐ 4: 15)* ያለው ቃሉ ነው::

ኢየሱስም ሲናገር:- *"ሌባው ሊሰርቅና ሊያርድ ሊያጠፋም እንጂ ስለ ሌላ አይመጣም እኔ ሕይወት እንዲሆንላቸው እንዲበዛላቸውም መጣሁ"(ዮሐ.10:10)*: በማለት የራሱንና የሰይጣንን ተልዕኮ በግልጽ አስረድቶአል::

የእኛ ድርሻ ወንጌልን መስበክ ሲሆን የተሰበከውን ቃል በመጠቀም የሰውን ልብ የሚለውጠው እግዚአብሔር ብቻ ነው:: ትልቁ ችግር ሰው የቃሉም ሰባኪና የሰው ልብ ለዋጭ ለመሆን ከተነሣ ነው:: ሰው ያሰበው አልሳካለት ሲል ከተስፋ መቁረጥ የተነሣ፣ በሥጋዊና አጋንንታዊ ሀሳብ ተጽዕኖ ሥር ወድቆ በሰይፍ ክቡር የሆነውን የሰው ነፍስ በእግዚአብሔር ስም ለማጥፋት ይነሣል:: በሰይፍ የሚያምን ሃይማኖት በታሪክ ሌላ እንጂ በፍጹም ክርስትና አይደለም::

## ነጻነትን የተራበ ነጻ ሕዝብ

ዮሐንስ ስለ ኢየሱስ ሲናገር:- *"የእርሱ ወደ ሆነው መጣ የገዛ ወገኖቹም አልተቀበሉትም" (ዮሐ.1:14)*:: እርሱ ፈጣሪ፣ መልዕክትና መልዕክተኛም ሆኖ የገዛ ሕዝቡ እንቢ ሲሉት እንደ እኛ ዐዔዎች በሰይፍ ሳይሆን በቃሉ ብቻ የማጥፋት አቅም እያለው ያለመጠቀሙ በሰው ውስጥ የፈጠረውን ነፃ ፈቃድ ማክበሩን ያመለክታል:: እግዚአብሔር ለሰው የሰጠውን አሳቡን የመግለጥ ነፃነት ራሱም ለመጣስ አይፈልግም፤ ሰውም የሌላወን ሰው ነፃነት እንዲጥስ አይፈቅድም:: የምድራችን የጥንት ሆነ የዛሬ ዐቢይ ችግራችን የራሳችን አሳብ እንጂ የሌላውን አሳብ ማስተናገድ አለመቻላችን ነው:: የራሱ የአሳብ ነፃነት እንዲከበርለት የሚፈልግ ሰው የሌላ ሰውን ነፃ አሳብ መገደብ የለበትም:: በእኛ ላይ እንዲደረግ የማንፈልገውን ነገር በሌሎች ላይ መፈጸም የለብንም::





ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ዘመኑን ቀንብቦ የያዘውን የሃይማኖት መንፈስ እንደ ሚከተለው ሕያው አድርጎ አስቀርቶታል:-

> *አንድ ልብ ብሩህ ያበሻ ሰው መሬት ትዞራለች ብሎ ቢያስተምር አሁን በቅርቡ በሐረርጌ በዳኛ ተይዞ አልነበረምን፤ አሁን በ1900 ዓመታት ከክርስቶስ ልደት በኋላ አልፈው ሀያኛውን መቶ ዓመታት ስንጀምር አንድ ሰው የተዋሕዶን ሃይማኖት ቢነቅፍ ካዲስ አበባ ገበያ ላይ በደንጊያ አልተቀጠቀጠምን?*[165]
> በማለት ለልምዳችን ያለንን ቀራጥነት፣ እርምጃ፣ ለለውጥና ለአዲስ ሐሳብ ያለን አሉታዊ አቋም ምን እንደሚመስል በተግባር ያስረዳል::

በየትኛውም መልክ አዲስ አሳብ በኢትዮጵያ እንደ ጦር ይፈራል:: አሳብን በአሳብ ከማሸነፍ ይልቅ የተለየ አሳብ የሚያነሡ ሰዎችን ማሳደድ፣ የገቡበት ጉድጓድ ገብቶ ካልገደልን ማለት፣ ለመግደል ባይቻል ደግሞ አሳቡን ትቶ ግለሰቡን ማጣጣልና በየመድረኩ ስሙን ማንኳሰስ እንደ ትልቅ ጀብዱ ይቆጠራል:: ይህ የኋላ ቀሪነታችንና የድህነታችን ዐቢይ ምክንያትና ምልክት ነው:: በአገራችን ጓደኛህ አንድን አሳብ ከተቃወመ አንተም የግድ መቃወም እንዳለብህ ያስባል:: እርሱ የሚቃወመውን አንድን አሳብ ከደገፍክ እንደ ቀንደኛ ጠላቱ አድርጎ አንተን ለመቁጠር ጊዜ አይፈጅበትም:: አስተማሪውን የሚበልጥ ተማሪ በአስተማሪው ይገፋል:: በኢትዮጵያ አዲስ አሳብ፣ አማራጭ መንገድና ልዩ አቀራረብ በየትኛውም መልኩ ተቀባይነት የለውም:: ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ እንጂ ጠቃሚ እንኳን ቢሆን አዲስ ነገር እንደ ብርቱ ጠላት ይታያል::

አንብበን ከምንረዳው እውነት ይልቅ ላልነበረ የአፈ ታሪክ ትልቅ ቦታ እንሰጣለን:: በቋንቋችን አንብበን ከተረዳነው እውነት ይልቅ በማንሰማው ቋንቋ ለተነገረን ውሸት ጥብቅና እንቆማለን:: ሰውን እስከ አንገት እንጂ እስከ ቁመታችን ማሳደግ አልለመድንም:: በመረጃ የተደገፈና በእጅ ካለው እውነት ይልቅ በንግርት እየተላለፈ የመጣ ውሸት በብዙዎች ዘንድ ነቁጥ አልባ እውነት ተደርጋ ትታመናለች:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ ድርሳናትና ገድላት በብዙ ይታመናሉ፤ ይጠቀሳሉ:: እውነትም ይሁን ውሸት እየተሻገረ የመጣ የቆየ አሳብ እንጂ የተሻሉና የጊዜው ብዙ አማራጭ ሐሳቦች ፍጹም አይፈለጉም:: መስለህ እንድትኖር እንጂ ራስህን ፈልገህ እንድታገኝ አይፈለግም:: በኢትዮጵያ በየትኛውም መልኩ የተለየ ሐሳብ እንዳታመነጭ በሕግ የተከለከለ ይመስላል:: ውጤቱም ያለንበት ባዶነትና ኋላ ቀርነት እንደሆነ ፕሮፌሰር መስፍን ወ/ማርያም ሲናገሩ:-

> *የኢትዮጵያ ሊቃውንት "ሲወርድ ሲዋረድ" በሚል በማያስብና በማያሳስብ የቁልቁለት አስተሳሰብ ለብዙ ምእተ ዓመታት ተጓዙ፤ ውጤቱ ዛሬ ያለንበት ደረጃ ነው::*[166]

[165] *ነጋድራስ ገብረ ሕይወት ባይከዳኝ ሥራዎቹ (2004 ዓ.ም)፣* አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ፕሬስ፣ ገጽ 14
[166] *ዝኒ ከማሁ፣ ገጽ 13*

የመስቀል ጦረኞች በአንደበት እግዚአብሔርን እያመሰገኑና የምስጋና መዝመሩ እየዘመሩ በእጃቸው ሰውን እያሰቃዩ የፈጁ የባዶ ሃይማኖት እስረኞች እንጂ የወንጌል አማኞች አልነበሩም:: የኢየሱስ ወንጌል ይህን በፍጹም አያስተምርም:: ይህ በእግዚአብሔር ቃል ፍጹም የተወገዘ ድርጊት ነው:: የልብና የአመለካከት ለውጥ በአማኞች ላይ የማያመጣ ክርስትና ከኢ-አማኒነት አይለይም:: የመስቀል ጦርነት "ክርስቲያን" ጦረኞች ከ*1095-1270* ዓ.ም ከልጅ እስከ አዋቂ የሆኑ የአውሮፓ ምዕመናን በኢየሩሳሌም ላይ ያወጁት የጥፋት ጦርነት ነበር:: የመስቀል ጦርነት ተዋጊዎች የእስልምናን ወረራ ለመቀልበስና ኢየሩሳሌምን ለመቆጣጠር ከ200 ዓመታት በላይ *8* የመስቀል ጦርነቶች አካሂደዋል:: እ.ኤ.አ ጁላይ*1099* የመስቀል ጦረኞች የኢየሩሳሌምን ከተማ ሰብረው ሲገቡ ጌታችንን የገደሉ በማለት አይሁዶችን ጨፍጭፈዋል፣ ዘርፈዋል፣ ከተማዋንና ታሪካዊ ቦታዎችን ወደ አመድነት ቀይረዋል::[173] የመስቀል ጦረኞኛ በጥቅል ክርስቲያኖች የተባሉ እንጂ የአዲስ ኪዳን እውነት የገባቸውና የክርስቶስ ደቀ መዝሙር የሆኑ ልቤ ክርስቲያኖች አልነበሩም:: የመስቀሉ *ሥራ* ያልገባቸው የመስቀሉ ወታደሮች፤ ጌታን በሕይወታቸው የማያውቁ ነገር ግን በጌታ ስም የሚዋደቁ፤ ባዶ ሃይማኖት እንጂ ሕይወታቸውንና አመለካከታቸውን የለወጠውን እውነት በልባቸው ያላሳደሩ አማኞች የተባሉ ኢ-አማኒያን ነበሩ::

ለዚህም ዋቢ ካስፈለገ የጦርነቱን አንዱን ዓላማ ማየት ከበቂ በላይ ነው:: የመስቀል ጦርነት ብርቱ ሰባኪና ጦሬኞቹን በፀሎት ባርከው የሸኙት የካቶሊክ ፖፕ ኡርባን ዳግማዊ ነበሩ:: ሕዝቡን ለመስቀል ጦርነት ሲያነሣሱ:- *ለመስቀል ጦርነት ለሚሄዱ ሁሉ የኃጢአት ሥርየትንና የዘላለም ሕይወትን ለመስቀል ጦረኞች ብቻ ሳይሆን ለቤተሰቦቻቸውና ለወላጆቻቸው ጭምር ተስፋ ሰጥተው ነበር::* ለኃጢአት ሥርየት ስለ ሰው ልጆች በፈሰሰው የኢየሱስ ደም መታጠብ ወይስ የሌላውን ሰው ደም በማፍሰስ? ሰው በወንጌል ልቡ ካልተለወጠ በስተቀር ቤተ ክርስቲያን በመሄዱ፣ በመቁረቡ፣ በጾም ፀሎት ብርቱ በመሆኑ፣ ስለ ክርስቶስ ቀንቶ ሌላው ላይ ዘምቶ በመግደሉና ክርስቲያን የሚባል ስም በመሸከሙ አይድንም:: የወንጌል ሰባኪው ጳጳስ የሰላም ወንጌል ጠፍቶበት ሰይፍ በማንሣት ጦርነትን እንደ ጽድቅ ቆጥሮ ከሰበከ የጽድቅ ቃል በውስጡ ያላደረውና ልበ ክርስቲያን ያልሆነው ሕዝብ ምን ይሆን? ክርስቲያን ክርስቶስን የሕይወቱ ቤዛ አድርጎ የተቀበለ፣ በእግዚአብሔር ቃል የሚመራ፣ የዕድሜ ዘመን ደቀ መዝሙር ሆኖ ክርስቶስን የሚከተል፣ በመልካም *ሥራ*ው በዙሪያው ላሉት ሰዎች የክርስቶስን መልካም መዓዛ የሚገልጥ፣ ለራሱ ፈቃድ ሞቶ ለሞተለት ጌታ የሚኖር እንጂ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረውን የሰውን ልጅ ለመግደል የሚያደባ አውሬ መሆን በፍጹም የለበትም:: ድነት የሚገኘው በመታገል ሳይሆን በጌታ በማመን ነው::

[173] Riley-Smith, Jonathan.*( 1990). The Atlas of the Crusades New York: Facts on File,* *"High ideals were besmirched by cruelty and greed ... the Holy War was nothing more than a long act of intolerance in the name of God"*. http://en.wikipedia.org/wiki/Crusades





ድነት በእምነት እንጂ ሰውን በመግደል አይገኝም:: በመጽሐፍ ቅዱስ አንድ የሮም ወታደር ከዛሬ 2000 ዓመታት በፊት ሐዋርያ ጳውሎስን:-

> *"እድን ዘንድ ምን ማድረግ ይገባኛል?"* በማለት ያቀረበው ጥያቄ ዛሬም የብዙሃን ጥያቄ ነው:: ሐዋርያ ጳውሎስ ግልጽና አጭር በሆነ መልስ:- *"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላችሁ"(ሐዋ.16:31) ብሎታል::* ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያንም በጻፈው መልዕክቱ ድነት የ*ሥራ* ሳይሆን በእምነት ከእግዚአብሔር የምንቀበለው ስጦታ እንደሆነ ገልጾዋል:- *"ጸጋው በእምነት አድኖአችኋልና ይህም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው እንጂ ከእናንተ አይደለም፤ ማንም እንዳይመካ ከሥራ አይደለም"(ኤፌ.2:8)::*

የክርስትና ዋና *መሠረት*ና አስተማሪ ኢየሱስ:- *"ሰይፍ የሚያነሡ ሁሉ በሰይፍ ይጠፋሉና ሰይፍህን ወደ ስፍራው መልስ" (ማቴ 26: 52)* በማለት የጴጥሮስን *ሥጋዊ* እርምጃ ኮንኖታል:: በመጽሐፍ ቅዱስ የተገለጠው አምላክ የሚዋጋልን ብርቱ እንጂ በሰው ሰይፍ ተዋግተንለት ዙፋኑን እንደ ምድራዊ *መንግሥት* የምናስጠብቅለት ደካማ አይደለም:: ማንም ሳያስገድደው ፍጹም የጠፋንና ጠላቶች የነበረነውን ሞቶልን በጸጋው ካዳነን በኋላ እኛም በተራችን የፍቅር መልዕክተኞች እንዲንሆን ወደ ዓለም ልኮናል:: በእውነት ከእርሱ ጋር ከታረቅን ከሐዋርያው ጳውሎስ ጋር *"እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልዕክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለክርስቶስ እንለምናለን" (2ቆሮ.5:21)* ለማለት እንችላለን:: ይህ ማለት አንዋጋም ማለት ግን አይደለም:: የዳነው በጦርነት ለጦርነት ነው:: ጥያቄው ምን ዓይነት ጦርነት? የሚል ይሆናል:: በእውነት የዳነ፣ የክርስቶስ ደቀመዝሙር የሆነና ቃሉ በውስጡ ያደረ ሰው መንፈሳዊ ጦረኛ ነው:: የምንዋጋው ግን ከሰው ጋር ሳይሆን ከአጋንንት ኃይላት፣ በዓለም ካለው ክፉ አሠራር፣ በውስጣችን ካለው ጥላቻ፣ ቂም፣ በቀል፣ ከንቱ ውዳሴ፣ ትዕቢት፣ ካለመታዘዝ መንፈስና ከውሸት ጋር ነው::

> *"በሰው ልማድ ምንም እንኳ የምንመላለስ ብንሆን እንደ ሰው ልማድ አንዋጋም፤ የጦር ዕቃችን ሥጋዊ አይደለምና ምሽግን ለመስበር ግን በእግዚአብሔር ፊት ብርቱ ነው፤ የሰውንም አሳብ በእግዚአብሔርም እውቀት ላይ የሚነሣውን ከፍ ያለውን ነገር ሁሉ እናፈርሳለን"* (2ቆሮ.10:3-5)::

በአገራችንም ቢሆን በክርስትና ስም የተካሄዱ ስም የማጥፋት፣ የስደት፣ የእስራትና ግድያ ድርጊቶች በእግዚአብሔር ቃል የተወገዙና ተቀባይነት የሌላቸው ብቻ ሳይሆን በክርስትና ስም ክፋት ፈጻሚዎቹ ልበ ክርስቲያን ያለመሆናቸው ከመስቀል ጦረኞች ጋር አንድ ያደርጋቸዋል:: የክርስትና ጉልበት የእግዚአብሔር ቃልና መንፈስ ብቻ ነው:: ኢየሱስ በጡንቻ መጥቶ ካልተዋጋ በጡንቻ እንድንዋጋለት በፍጹም አይልከንም::

# ሐዋርያት ስለ ክርስትና ገደሉ ወይስ ተገደሉ?

የክርስትና መሠረት ክርስቶስ ነው። ክርስቶስ የተገለጠው በቃሉ ነው። የእግዚአብሔር ቃል የሆነው ደግሞ በሁለት ኪዳናት የተከፈለ በውስጡ 66 መጻሕፍት የያዘ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በዚህ መጽሐፍ የክርስትና ዋና መሥራች ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰዎችን ለማዳን ሞተ። እርሱም በቀጥታ ወደ ዓለም የላካቸው አሥራ ሁለቱን ሐዋርያት ሲሆኑ እንደ ጌታቸው ላመኑበት የወንጌል እውነትና ለወንጌል አገልግሎት ለማዕት ሆነዋል:-

*1. ጴጥሮስ - ራሱን ወደ ታች ተዘቅዝቆ በሮም ተሰቀለ በ64 ዓ.ም አካባቢ*

*2. የያዕቆብ ልጅ ይሁዳ - በድንጋይ ከወገሩት በኋላ አንገቱ ተቀላ*

*3. ማቴዎስ - በመጥረቢያ ተቆረጠ በ60 ዓ.ም አካባቢ*

*4. የዘብዴዎስ ልጅ ዮሐንስ - በሰላም ሞተ*

*5. የእልፍዩስ ልጅ ያዕቆብ - በ90 ዓመቱ በድንጋይ ተወገሮ ሞተ*

*6. ፊልጶስ - በስቅላት ተገደለ በ54 ዓ.ም አካባቢ*

*7. ቀነናዊው ስምዖን - በስቅላት ተገደለ*

*8. ታዴዎስ - በቀስት ተገደለ*

*9. ቶማስ - በጦር ተወግቶ በህንድ ተገደለ በ72 ዓ.ም አካባቢ*

*10. ቤርተሎሜዎስ - በሕይወት እያለ ቆዳውን ገፈው አንገቱን ቀርጠዋል።*

*11. የዜብድዮስ ልጅ ያዕቆብ - በሰይፍ አንገቱ ተቀላ በ44 ዓ.ም አካባቢ*

*12. የአስቆርቶ ይሁዳን የተካ ማቲያስ - በድንጋይ ከተወገረ በኋላ አንገቱ ተቀላ*

ሐዋርያት ለጌታ ብለው ወንጌልን ለሌሎች እየሰበኩ እንደሞቱ እንጂ ለወንጌልና ለቤተ ክርስቲያን ብለው አንዳች ሰው እንዳስገደሉም ሆነ እንደገደሉ ቀርቶ ሰውን እንደሰደቡ እንኳ ቃሉም ሆነ ታሪክ አይናገርም።

ቦብ ጊሊያም *"ታላቁን ተልዕኮ ለመፈፀም ቤተ ክርስቲያን ተካዮች ማስልጠኛ መመሪያ"* በሚል ርዕስ ባዘጋጁት መጽሐፍ *"Jesus Freaks"* ከሚል መጽሐፍ ያገኙትን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ የአንድ ቤተሰብ አስደናቂ ተጋድሎ ያነበቡትን ይጠቅመናልና እንመልከት:-

*ታሪኩ የተፈፀመው እ.ኤ.አ 1970ዎቹ በካምቦዲያ ነው። በ"ግድያ ሜዳዎች" ዘመን የሆነ። የሀይም ቤተሰቦች ሌሊቱን በሙሉ አንድ ላይ ታስረው እርስ በርሳቸው እየተያዩ መሬት ላይ ተኝተው እንዲያድሩ ተደረገ። ክርስቲያኖች ስለሆኑና የታላቁ አብዮት ጠላቶች ተብለው በኮሚኒስቶች ስለተቆጠሩ በዚያው ዕለት ማለዳ ለመግደል ምልክት ተደረገባቸው። በማለዳም የሀይም ቤተሰቦች እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን መቃብር እንዲቆፍሩ ተደረገ። ገዳዮቻቸውም ለእነርሱ ቸርነትን በማድረግ ተንበርክከው በጋራ ፀልየው ለሞታቸው እንዲዘጋጁ ዕድል ሰጧቸው። የሀይም ቤተሰብ ወላጆና ልጆች እጅ ለእጅ ተያይዘው ለራሳቸው በቆፈሩት ጉድጓድ አጠገብ ተንበረከኩ። ከፀሎት በኋላ ሀይም እነርሱን ለመግደል የተዘጋጁ ፖሊሶች፣ ኮሚኒስቶቹንና ተመልካቾችን ንስሐ በመግባት ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኛቸው አድርገው እንዲቀበሉ በትልቅ ድፍረት ወንጌልን ሰበከላቸው፤ በዚህ ጊዜ ሞት ያስፈራው ከሀይም ታናናሽ ልጆች መካከል አንዱ ከተንበረከከበት ተነሥቶ በቅርብ ወዳለው ጫካ ሮጦ ገባ። ሀይም ልጁን ለክርስቶስ በክብር ወደ መሞት ዕድል ለመጥራት እንዲፈቅዱለት እጅግ ተረጋግቶ ወታደሮቹን አጥብቆ ተማፀናቸው። ተንበርክኮም ልጁ ተመልሶ ለክርስቶስ ኢየሱስ ከእርሱ ጋር ተመልሶ እንዲሞት ይለምን ነበር። ድምፁንም ከፍ አድርጎ "ልጄ አስብ" ብሎ ጮኸ! "ጥቂት ተጨማሪ የሕይወት ቀናትን በዚህ ጫካ ውስጥ ኮብላይ ከምትሆን ከቤተሰብህ ጋር ለጌታ ብለህ ሞተህ ወዲያውኑ ለዘላለም በመንግሥተ ሰማይ በነጻነት ከመኖር ጋር ይወዳደራልን?" ሲል ልጁም እያለቀሰ ለክርስቶስ ከቤተሰቡ ጋር ለመሞት ተመለሰ። ሀይምም በታላቅ ደስታ ለገዳዮቹ "አሁን ለመሄድ ዝግጁ ነን" አለ። ነገር ግን ይህን ለማመን የሚያስቸግር ትዕንት ያዩ ከነበሩ ወታደሮችመካከል አንዳቸውም ሊገድላቸው አልቻለም። በቦታው ያልነበረ ወታደር መጣና የሀይምን ቤተሰብ በአንድነት ገደላቸው። ሰማዕትም ሆኑ።*

በድልና በታላቅ ደስታ ወደ ቀጣዩ ሕይወት በክብር በአንድነት ተሻገሩ። ይህም በሐዋርያት ዘመን ብቻ ሳይሆን ለክርስቶስ ራሳቸውን የሰጡ ቤተሰቦች ከልጅ እስከ አዋቂ ላዳናቸው ጌታ በፍቅር ሲሞቱ በዘመናችን ማየት የእውነተኛ ክርስትና መንገድ ዛሬም እንዳልደበዘዘ ያመለክተናል። ሐዋርያት የቤተ ክርስቲያን አባቶችና በየዘመናቱ የኖሩ እውነተኛ ክርስቲያኖች ለወንጌል ሲሞቱ እንጂ ለወንጌል ሰውን ሲገድሉ ቃሉና ታሪክም አይናገርም። ታዲያ የኢትዮጵያው በተለይ የጥንትና የመካከለኛ ዘመን *"ክርስትና"* ሀገር በቀል ካልሆነ በስተቀር ሰውን በግድ ክርስቲያን ማድረግ፣ እንቢ ያለውን መግደልና ማሳደድ፣ ወደ ቃሉ እንመለስ ብለው ሀሳባቸውን የገለጹትን አፍንጫቸውን መፎነን፣ ምላሳቸውን መቁረጥና በድንጋይ መውገር ከየት አመጣው? የዚህ ክርስትና መሠረቱ መጠናት የለበትም ወይ? አሁን ካልሆነ መቼ ይጠናል? እኛ ካላጠናን ማን ያጠናዋል? ይህ ክርስትና ተብሎ ተመሳሳይ ስያሜ የተሰጠው ሌላ ሃይማኖት ይሆን? ያልተጠየቀና ለአንዳንዶች የሞኝ ጥያቄ ሊመስል እንደሚችል እያወኩ ጥያቄዬን ልድገም የኃይል አጠቃቀምና በግድ ሰውን ክርስቲያን የማስባል አካሄድን ተደግፎ የተሰራጨው የኢትዮጵያ ክርስትና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው? ካልሆነ ንስሐ መግባት አለብን።

## በአዋጅ "ቤተ ክርስቲያንን" ማሠራት

እንደ ጸሐፊ ትዕዛዝ ገብረ ሥላሴ ዘገባ በ1900 ዓ.ም በአዲስ አበባ የሚኒልክ ቤተ ክርስቲያን ግንባታ አዋጅ:-

*የሃይማኖት መሠረቱ የቤተ ክርስቲያን ምልክቱ ቤተ ክርስቲያን መሥራት ነው። ለጉልበትህና ለገንዘብህ ሳስተህ ቤተ ክርስቲያን አልሠራም ብለህ የወሰለትህ ሰው በሰማይ ይፈረድብሃል። በምድርም ሹመትህን ገንዘብህን ታጣለህ። የሚል ቃል በየሀገሩ አዋጅ ተነገረ*

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራስዋን በማየት በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ብትመለስ፣ በወንጌል ለዓለም የበረከት ምክንያት ትሆናለች፤ ዕድሜዋን የሚመስል ዓለም አቀፋዊ የጽድቅ ፍሬዎች ባለቤት ትሆናለች፤ ሰው ሰው ሳይሆን ኢየሱስ፣ ኢየሱስን ትሸታለች፤ ኢትዮጵያ በእውነት ትባረካለች፤ የዚህች ምድር ሕዳሴ ሁለንተናዊ ይሆናል:: የልብ ጥንካሬና ትዕቢት ካለ የባሰ ጥፋት፣ ስብራትና ውርደት መምጣቱ አይቀሬ ነው:: ወደ እግዚአብሔር እንመለስ::

## ዛሬን በቅጡ ለማወቅ ትናንትን የመረዳት ግዴታ

ድንጋይ፣ አሎሎም ሆነ ጦር አርቀን ወደ ፊት ለመወርወር ወደ ኋላ መንደርደር አማራጭ እንደሌለው ሁሉ መጭውን አርቀን ለማየት ወደ ኋላ ሄደን ታሪክን መቃኘት የግድ ይላል:: በሁለተኛው የዓለም ጦርነት እንግሊዝን በድል የመሩ ጠቅላይ ሚኒስተር ዊንስተን ቸርችልም ስለዚህ ሲናገሩ:- *"The farther back we look, the farther ahead we are able to see."* በግርድፉ ሲተረጎም *"ያለፈውን ወደኋላ ዞር ብለን ለማየት በቻልን መጠን የወደፊቱንም አርቀን ለመመልከት እንችላለን::"* ወደ ፊት አርቀን ለማየት ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና ዕውቅና መስጠትና ያለፈ ታሪካችንን መቃኘት የግድ ነው:: መለኮታዊ ራእይን አንግበን አዲስ የታሪክ ምዕራፍ እንድንከፍት እግዚአብሔር ከእኛ ይፈልጋል::

እግዚአብሔር በዘመናችን ምን እንደሠራን የሚጠይቀን በሀገራችን ታሪክና በቤተ እምነታችን ስም ላይ ተንተርሶ ሳይሆን በሰጠን ቃሉ፣ ጸጋና ራእይ ላይ ተመሥርቶ ነው:: የአባቶቻችን ድል እኛ የሚበልጥ ታሪክ እንድንሠራ ካላነሣሳን፣ ከአሉታዊ ታሪካቸው ካልተማርን ታሪኩ ለእነርሱ እንጂ ለእኛ ዋጋ የለውም:: ትልቁ ጥያቄ አባቶቻችን ዛሬ እኛ የምንመካባቸውንና የምንደገፍባቸውን ታላላቅ ሥራዎች ከሠሩ እኛ ለልጆቻችንና ለቀጣዩ ትውልድ ምን የላቀ ሥራ ሠርተን እንለፍ? ነው:: በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ያለቅጥ የሚኮራና የዛሬዪቷን ኢትዮጵያ ውርደትና ውድቀት ለመለወጥ ራእይ አልባ የሆነ ሰው፤ የኢትዮጵያውያንን ቁጥር ከመጨመር ውጭ ለኢትዮጵያ አንዳች አይፈይድላትም:: የአድዋን ድል ብቻ እያነሣ ዘራፍ የሚል፣ የዛሬን ብርቱ ጠላት ድህነትና ድንቁርናን ለመግጠም ምክንያት የሚደረድር እርሱ ለራሱም አይጠቅምም:: በሁለት ሺ ዓመታት ፍሬ አልባ የክርስትና ስም ያለቅጥ የሚመካና በጥፋት ላይ ያለውን ዓለም በወንጌል ለመድረስ ደንታ የሌለውና የሃይማኖቱ ገድል ሰባኪ እርሱ የክርስቶስ የመስቀል ምንነት አልገባውም:: ስለ አክሱም ሐውልቶች ገናናነት ለመተረክ ጊዜ የማይበቃው ዛሬ ብዙ የፈረሰውን የአገርን ቅጥር ለመገንባት ልብ የከዳው እርሱ ወሬን ሥራው ያደረገ ሰው ነው::





በዘመን ጠገብ ሃይማኖታዊ ትውፊት ከልክ ያለፈ የሚኩራራና የጊዜውን መለኮታዊ አጀንዳና መገለጥ ለመስማት ጆሮ የሌለው እርሱ ሃይማኖተኛ እንጂ የክርስቶስ እውነት የበራለት ክርስቲያን አይደለም:: ትናንት በተገነባው የታሪክ ጥላ ሥር ሆኖ ዛሬ ሕይወቱ የፈረሰበትና ግራ የተጋባ እርሱ ራሱ የአገር ዕዳና ሸክም ነው:: አንድ ጸሐፊ "ቅኝ የተገዛው ማነው?" በሚል ርዕስ ኢትዮጵያውያን ያለንበትን አሳዛኝ ሁኔታ ሲገልጹ *"ዛሬ እየኖርን አይደለም:: ያለፈ ታሪክ እያወራን ጉንጫችንን ስናለፋ ዛሬ ጥሎን ሄዷል"*[175] ብለዋል::

## የኢትዮጵያና የኤርትራ ጦርነት የልብ ጥንካሬ ያመጣብን ይሆን?

እ.ኤ.አ በ1997 የአፍሪካ አገራትና ከዓለም ዙርያ የተሰበሰቡ የፀሎት ሰዎች የሆኑ ተወካዮች የተካፈሉበት የመላ አፍሪካ የፀሎት ኮንፍራንስ በአዲስ አበባ በሚገኘው *"በአፍሪካ አንድነት ድርጅት"* የስብሰባ ማዕከል ተካሂዶ ነበር:: በጉባኤው ላይ ልዩ የእግዚአብሔር መገኘት ነበር፤ ለአፍሪካ አገሮች ሁሉ በየተራው የምልጃ ፀሎት ተደርጓል:: ከዚህ ፕሮግራም አዘጋጆች መካከል አንዱ የሆኑ ሬቨረንድ ጆን ማልንድ የሚባሉ ዩጋንዳዊ የእግዚአብሔር ሰው ስለ ኢትዮጵያና ኤርትራ በንስሐ ጥሪ ዕድል ያለመጠቀማቸው *"Tranforming Our World"* በሚለው መጽሐፋቸው እንዲህ ዘግበዋል:-

> *ለኢትዮጵያና ለኤርትራ የምልጃ ፀሎት የሚደረግበት ጊዜ ደረሰ:: ከሁለቱም አገሮች የመጡ ተወካዮች ወደ መድረክ ተጋበዙ:: በምድራቸው በእርስ በርስ ጦርነት ስለተጨፈጨፉ፣ ምድራቸውን በሰው ደም የሸፈነ እርግማን ስላለ ከልብ እርስ በርስ ይቅር በመባባል በንስሐ በእግዚአብሔር ፊት እንዲወድቁ ጥሪ ተላለፈላቸው:: ጉባኤው ስለ ሁለቱ አገራት በእንባ የምልጃው ፀሎት ልዩ መቃተት ውስጥ ገባ:: የእግዚአብሔር ሀልዎት በመካከላችን ስለነበረ የኢትዮጵያና የኤርትራ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች በብርቱ እንባ ውስጥ ሆነው ይቅር እየተባባሉ ሳሉ ነበረውን ሁኔታ የሚጋፋ መንፈስ ሲመጣብኝ፤ በዚህ ሁኔታ መካከል አንገቴን አቀርቅሬ ሳለሁ እግዚአብሔር እንዲህ አለኝ:-*
>
> *"እነዚህ (የኤርትራና የኢትዮጵያ ተወካዮች ሆነው በመድረኩ እያለቀሱ የምፀልዩ) በእኔ ላይ እያላገጡ ነው:: እያደረጉት ያለው ነገር ሁሉ ከልባቸው አይደለም:: ሁሉም ለሰዎች ታይታ ነው፤ በምድራቸው ላይ በከንቱ የፈሰሰው ደም ወደ እኔ እየጮኸ ስላለ ልቤ እጅግ አዝኗል:: ጠላት ሌላ የጅምላ ጭፍጨፋ በምድራቸው ሊያካሀድ የፈሰሰውን ደም እየተጠቀመ ነው:: አገልጋዮች እያላገጡ ነው፤ አለኝ:: ውስጤ ተሰበረ፤ እጅግም አዘኜ ሳለሁ፤ ከኢየሩሳሌም የፀሎት አገልጋዮች አንዱ የሆነው ጓደኛዬ ቶሚ ሀሰሲ ወደ እኔ መጥቶ "ከእግዚአብሔር የሆነ ቃል እንዳለህ እርግጠኛ ነኝ" ስለኝ "ግራ ገብቶኝ እባክህን ለብቻዬ ተወኝ" አልኩት:: በመጨረሻም ከተቀበልኩት መልዕክት ጥቂት ነገር ነገርኩት:: እርሱም:- የተቀበልከውን መልዕክት መናገር አለብህ ብሎ ገፋፋኝ:: እኔም*

[175] *አዲስ ጉዳይ ሚያዝያ 27 ቀን 2004 ዓ.ም ገጽ 8*

ለጊዜው እንኳን አገልግሎት ሲያቆሙ ያለመታየታቸው በሕዝቡ ዘንድ ትልቅ ግራ መጋባትን ፈጥሯል:: ይህን ሀሳብ በየትኛውም ቦታ በአሉታዊ መልኩ የሚናገር እርሱ መንፈሳዊ ኋላቀር፣ ያልዘመነ፣ ያልተቀባ፣ ገና ብዙ ነገር እንደሚቀረው ስለሚቆጠርና ለእግዚአብሔር ቃል ሳይሆን ለሰዎች ቲፎዞ በሆኑ "አገልጋዮች" እንዳይብጠለጠል ስለሚፈራ የሞት ዝምታ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሰፍኗል::

ለእግዚአብሔር ክብርና ወንጌልን ለማስፋት ሳይሆን የንዋይ ፍቅርና በዓለም ያጡትን መሪ የመሆን ረሃባቸውን ለማስታገስ ቤተ ክርስቲያን "ተካዮች" ሳይሆን "ከፋቾች" እንደ አሸን ፈልተዋል:: አዳዲስ ቤተ ክርስቲያናትን በብዛትና በጥራት በመተከል በጣም አምናለሁ:: በቂም ባይሆን ጌታ በረዳኝ መጠን ወንጌልን ባልሰሙት ሕዝቦች መካከል ሚሲዮናውያንን በመላክ አዳዲስ ቤተ ክርስቲያን በመትከል ላይ እንገኛለን:: ኮንፍራንሶቻችን፣ የጅማ ጉባኤዎቻችንና የማነቃቂያ ስብሰባዎቻችን ላይ ሁሉም ሰው እንዲገኝ በነፃነቱ ተጠቅመን በፖስተር፣ በቴሌቪዥንና በሬዲዮ ወንጌል ይሰበካል፣ እውር ይበራል፣ ድንቅና ተአምር ይሆናል በማለት አብዝተን ብንጣራም ብዙዎች ገደብ የለሽ ጭፈራና ገንዘብ የማሰባሰብ አደገኛ አካሄድ ስለሰለቻቸው መምጣት አቁመዋል:: ነገሩ ያልገባቸው ጥቂት ምስኪኖች ሲመጡ ወንጌል መስበክና ፀሎት ሁሉ ረስተን ክሳቸውን ለማራቆት ግብግብ እንፈጥራለን:: በአገራችን በየኮንፍራሱ "ነቢይ" እንደሆኑ በፖስተር ተገልጾ አንዴም የእግዚአብሔርን ቃል ሳይናገሩ ከስሜት ኮርኳሪ ስብከት በኋላ ተነሥተው ገንዘብ፣ ወርቅ፣ ሞባይልና በእጅና በከስ ያለውን ሰዎች እንዲሰጡ የሚያስገድዱ እየበረከቱ ነው:: በዚህ የተዋጣላቸው አንዳንዶች ካሰባሰቡት ገንዘብ 40% እንደሚጠይቁ ይነገራል:: ይህ በሉተር ዘመን ወንጌል ረግጠው የኃጢአት ስርየትንና መንግሥተ ሰማያትን በቲኬት ሽያጭ እንደለወጡት በዘመናችንም ወንጌልን በገንዘብ የለወጡ "ገበያና ሆድ መር" አገልጋይ ተብዬዎች ቁጥራቸው ቀላል አይደለም:: ይህን ኢወንጌል፣ ቤተ ክርስቲያንንና አገርን ወደ አደጋ የሚመራ አካሄድ የእግዚአብሔር ቃል ያላት ቤተ ክርስቲያን በገሃድ ልታወግዝ ይገባል:: አሳዛኙ ስለዚህ ነገር በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የፍርሃትና ግራ የመጋባት ዝምታ መስፈኑ ነው::

አብዛኛው ጉባኤዎቻችን አፌ ጮሌዎች፣ በወንጌል ስም *"ሌላ ወንጌል"* የሚያራምዱ አገልጋይ ተብየዎችና የድርጊቱ ተባባሪ አንዳንድ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች እግዚአብሔርን ብሎ የመጣውን ሕዝብ የምመዘብሩበት ሜዳ ሆኗል:: በዚህ መርዝ የተለከፉ አገልጋዮች ብዙ ክርስቲያኖች ወደ ሚኖሩበት ከተማና አካባቢ እንጂ ተቃውሞ ወዳለበት አካባቢ በስህተት እንኳን ጉራ አይሉም:: "ወንጌልን" የሚያሰራጩት ወንጌልን ከሺ ጊዜ በላይ በሰሙት አማኞች መካከል ነው:: ከዚህም የተነሣ የከሰረ ነጋዴ፣ ለመማር ያልታደለ አዕምሮ፣ ሞፈር የሰቀለ ገበሬ፣ ለቤተ ክርስቲያን የማይታዘዝ ሁሉ የዋህ ሕዝብ ለመበዝበዝ እንዲያመቸው ሐዋርያ፣ ነቢይ፣ ፓስተር፣ ወንጌላዊ፣ የእግዚአብሔር ሰው፣ ወዘተ...የሚሉ የአገልግሎት ቢሮ አመልካች





ስሞችን በራሳቸው ላይ በመለጠፍ ትልቅ ብዝበዛ ከማካሄድም አልፈው ለወንጌል እንቅፋት የሚሆን ዘር በምድራችን ከከተማ እስከ ገጠር በስፋት እየተዘራ ነው::

እ.ኤ.አ በ2013 ናይሮቢ ኬንያ ለአገልግሎት ሄጀ ኬ.ት.ኤን በሚባል ቴሌቪዥን አንዳንድ *"አገልጋዮች" "የተቀደሰ ውሃ"ና "ልዩ ዘይት"* ብለው ሕዝቡን በገሃድ እየዘረፉ እንዳሉ፤ መንፈሳዊ የቴሌቪዥን፣ የራዲዮ ፕሮግራሞችና ኮንፍራንሶች ሁሉም ወንጌልን መስበክ ሳይሆን ገንዘብ ተኮር መሆኑ ያሳሰባቸው ጋዜጠኞች ልዩ ፕሮግራም አዘጋጅተው ታዋቂ አገልጋዮችን በመጋበዝ ቃለ መጠይቅ ያደርጉ ነበር:: ስለዚህ ጉዳይ አስተያየት እንዲሰጡ ከተጋበዙት መካከል "ሪድምድ ጎስፔል ቸርቺ" የተባለ ከ4 ሚሊዮን በላይ የሚገመት አባላት ያለው የፐንቴኮስታል ቤተ እምነት መሥራችና ከአሥር ሺ በላይ አባላት ያለው ቤተ ክርስቲያን መሪ የነበሩ ዶ/ር ጳጳስ አርተር ግቶንጋ አንዱ ነበር:: ጋዜጠኛው *"የዚህን ዘመን ገንዘብ ተኮር ወንጌል እንዴት ታየዋለህ?"* ሰዎች *"የተቀባ ውሃ" "ተአምረኛ ዘይት"* እያሉ በዚህ ምስኪን ሕዝብ ላይ በ5,000 በ10,000 በ100,000... ሺልንግ እየሸጡ ሲሆን በመገናኛ ብዙሃን በቀን በሌሊት ይህን ብቻ ይሰብካሉ፤ ይህን እንዴት ያዩታል? ብለው ሲጠይቁ:: መልሳቸው:- ይህ የእግዚአብሔርን ስጦታ እንደ ስምዖን ለመሸጥና ለመግዛት እንደ መከጅል ነው፤(የሐዋ.8:9-13):: ይህ ኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ራስ ተኮር አደገኛ እንቅስቃሴ ነው፤ ካሉ በኋላ የተጠቀሙበት ሌላ ምሳሌ ያስገርማል:: እንዲህ አሉ:-

> *ላለፉት 25 ዓመታት በኮንጐ በሚሊዮን የሚገመት ነፍሳት የቀጠፈና በብዙ ሚሊዮን የሚገመቱ ዜጐችን ስደተኛ ያደረገ የእርስ በርስ ጦርነት በዚያ ምድር እየተካሄደ ሰላለ በዚያች አገር ዩኒቨርሲት መማር፣ አርሶ መብላት፣ ነግዶ ማትረፍ፣ ሠርቶ መለወጥ የማይታሰብ ሲሆን ለአብዛኛው ኮንጐሊሲት ቀላልና አማራጭ የሥራ ዕድል ተደረጎ የተወሰደው ዘፈን ነው:: እንደዚሁም በዛሬይቷ ኬንያ መማር፣ መነገድ፣ መሥራት፣ ያልቻለ "የአገልጋይነት" (ነቢይ፣ ሐዋርያ፣ ፓስተር፣ ወንጌላዊ) ጭንበል በመልበስ በአቋራጭ ለመበልጸግ፣ በተራቀቀ መንገድ በእግዚአብሔር ስም ገንዘብን ከሰው እጅ የሚነጥቁ የበግ ለምድ የለበሱ ነጣቂዎች በምድሯ ላይ ተለቀዋል:: ካሉ በኋላ መፍትሔው ቤተ ክርስቲያን ወደ ቃሉ ተመልሳ ሕዝቧንና አገልጋዮቿን ወደ ቃሉ ካልመለሰች ትውልድና አገር የሚያጠፋ ዘር ማጨዳችን አይቀርም፤ ያሉትን ሁሴ አልረሳም:: በአገራችንም እየተካሄደ ያለው ተመሳሳይ ነው::*

ከሁሉም ይልቅ የሚያሳዝነው በአገራችን የችግሩን ፍጥነትና አደገኝነት እያየች የቤተ ክርስቲያን ዝምታ ነው:: ቤተ ክርስቲያን በዝምታዋ ከቀጠለች እግዚአብሔር ለዝምታዋ ሁሉ ተገቢ ዋጋ የሚያስከፍላት ሌላ አካል ማስነሳቱ አይቀሬ ነው:: ወደ እግዚአብሔር ተመልሰን መንገዳችንን ካላስተካከልን እርሱ ራሱ ምድሯን በክፋታችን እንዳናጠፋ ሌላ ከልካይ በመንገዳችን ላይ ሊያቆም ወስኗል:: ከልካይ ሳይወጣ ዛሬ በቃሉ ተይዘን ብንቆም ምንኛ መልካም በሆን ነበር::

ለዚህ ሁሉ መፍትሔው ተሐድሶ ነው። ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ። ካልተመለስን የዘራነው መራራ ዘር በብዛት አፍርቶ የባሰ ነገር ማጨዳችን አይቀሬ ነው። እግዚአብሔር ሆይ! በምሕረትህ አስበን።

## በንስሐ ያልተወገደ የትናንቱ የበደል ስንክፍ

የኢትዮጵያ ረሃብ፣ ስደት፣ ጦርነት፣ በሽታና ያለመባረክ ሌላው ምክንያት በክርስትና ስም በዚህ ምድር የተደረጉ ኢሰብአዊ ድርጊቶችን በንስሐ ወደ እግዚአብሔር ፊት ያለማቅረባችን እንደሆነ አውቀን በምድራችን አገራዊ የንስሐ ጥሪ ልናውጅና ንስሐ ልንገባ ይገባል። ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ፣ ተከታዮቹና ደጋፊዎቹ የተሐድሶ አሳብ አንግበው የተነሡትን እስጢፋኖሳውያን በኢሰብዓዊ ሁኔታ በዘመኑ ከነበረችው ቤተ ክርስቲያን ጋር በማበር እንደፈጁአቸው በሰፊው ተመልክተናል። ከዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ቀጥሎ የነገሡት ዐፄ በእደ ማርያም (1460-1470) ዐፄ እስክንድር (1470-1487) እስጢፋኖሳውያንን በማሳደድ እንደ ቀጠሉ ታሪክ ይናገራል። የአሕመድ ግራኝ ታላቅ ግድያ፣ በኃይል አገርን የማስለም ጦርነት፣ አብያተ ክርስቲያናትን የማፍረስና ካህናት በጅምላ መግደል የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በእስጢፋኖሳውያን በኩል ከእግዚአብሔር የተላከላትን የንስሐ ጥሪ የመቃወሟ ብቻ ሳይሆን በመልዕክተኞቹ ላይ ያደረገችው ዘግናኝ ጭፍጨፋና የመለኮታዊ ምሕረት ዐዋጅ የመጋፋት ውጤት እንደሆነ አንዳንዶች ይናገራሉ።[183] ከዚያም በኋላ የፖርቱጋል ወታደሮችን ተከትለው የመጡት ኢየሱሳውያን መነኰሳት የካቶሊክን ሃይማኖት በመስበካቸው በካቶሊኮችና በኦርቶዶክሶች መካከል በተካሄደው ጦርነት ከኦርቶዶክሳውያንና ከካቶሊካውያን 9,000 እስከ 12,000 ሰዎች እንደሞቱ ይገመታል።[184] በሁለቱም ወገን የተገደሉት ኢትዮጵያውያን እንደ ነበሩ መዘንጋት የለበትም። ከዚያም በኋላ የቅብዓቶችና የተዋሕዶዎች (1657-1847ዓ.ም) በማለት ጎራ ፈጥረው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጦርነት ገጥመው ብዙዎች ተገድለዋል።

ነገሥታቱ በማያውቁት ጣልቃ እየገቡ በሚያከራክሩበት ጊዜ የወገኑለትን ወገን ረቺ ሌላውን ተረቺ በማድረጋቸውና በተረቺው ላይ ጦር በማዝመታቸው ለረዥም ጊዜ የእርስ በርስ መገዳደል ሰፍኖ ነበር። እንዲሁም የካሮች ጭፍጨፋ (1947-1909 ዓ.ም) በክርስትና ስም በዚህ ምድር ተካሄዷል። የተዋሕዶችን ትምህርት ያልተቀበለ ክፍ ብሎ አንገቱን ዝቅ ብሎ ባቱን ይቈረጣል! በሚለው አዋጅ ቅባቶችና የጥንቱ ተዋሕዶዎች እጅና እግራቸውን ምላሳቸውን ጭምር ተቈርጠዋል። ይህ አዋጁ እስከ ምኒሊክ ሞት የጸና ነበር ይባላል። የጉንዳጉንዶ (የአባ እስጢፋኖስ ገዳም) መምህር የነበሩ አንድ አባት በማለዳ ጸሎት ጊዜ ለጉባኤው አባላት እንዲህ አሉ ይባላል፡-

*በአገራችን እስጢፋኖስና ደቀ መዛሙርቱ በግፍ ደማቸው ፈሷል፤ ሕይወታቸው ተሠውቷል፤ ለአብ ለወልድ እና ለመንፈስ ቅዱስ ካልሆነ ለሌላ አንሰግድም በማለታቸው ለሙሲሊሞች መጠለያ የሆነች አገር በእነርሱ ላይ ግፍ ፈጽማለች። በዚህ ጉዳይ ቤተ ክርስቲያናችን ንስሐ ካልገባች እስካሁን የተፈራረቁባት መቅሠፍት ይቀጥላል እንጂ አይቋረጥም።*[185] *ብለዋል ይባላል።*

[183] ጥኑተ ብርሃን፣ መጋቢት 2002 ዓ.ም ገጽ 9

[184] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10







ዛሬም እግዚአብሔር ለአገራችን ኢትዮጵያ እውነተኛ ንስሐና በፊቱ የመዋረድና የመመለስ ጥሪ ያቀርባል። ካልተመለስን እየሄድንበት ያለው መንገድ መጨረሻው አሁን ካለው የባሰ ስብራት ይሆናል። እየሞላ ያለ መራራ ጽዋ በታትኖን ሳያጠፋን፣ የክርስቶስን መስቀል የጋረዱብንና እጅግ ብርቱ እንደሆኑ የሚነግሩን የሃይማኖት ሥርዓቶቻችን፣ ያለ ቅጥ የሚንኮራበት ታሪካችን፣ ልምዶቻችንና የአገልግሎት ሩጫዎቻችን ተመልሰው የማሰናከያ አለት ሳይሆኑብን ወደ እግዚአብሔር እንመለስ።

### መፍትሔ

## ልባዊና እውነተኛ አገራዊ ንስሐ መግባት ይገባናል

*"ኑ ወደ እግዚአብሔር እንመለስ" (ሆሴ.6:1)።*

እግዚአብሔር እንደ ሙሴ "እባክህ እንደ ምሕረትህ ብዛት የዚህን ሕዝብ ኃጢአት ይቅር በል" (ዘኁ.14:19) ብለው ስለ ኢትዮጵያ በፊቱ የሚወድቁትን፤ እንደ ነህምያም *"እኔና የአባቴ ቤት በድለናል። እኛም በአንተ ላይ እጅግ ክፉ ሠርተናል" (ነህ 1:6)* በማለት ስለ ሕዝብና ስለ አገር ምሕረትን የሚጠይቁና ለግንባታ የሚነሡትን እውነተኛ የቤተ ክርስቲያን መሪዎች ይፈልጋል። *"ቅምጥሊቱ ግን በሕይወት ሳለች የሞተች ናት"* (1ጢሞ.5:6) *ቃሉ* እንደሚለው ጽድቃችንን እያወራን፣ ልዩ መሆናችንን እየሰበክንና ከሁሉ ኋላ ቀርተን ከሁሉ የቀደምን አድርገን እንደትናንቱ ማወጅ አይገባንም። ትዕቢት ሁልጊዜ ከሰይጣን ነው። *ቃሉ "ልቡ የታበየ በእግዚአብሔር ዘንድ ርኩስ ነው፤ እጅ በእጅም ሳይቀጣ አይቀርም"* (ምሳ.16:5) ይላልና።

ከኢመጽሐፍ ቅዱሳዊ ትውፊቶቻችንና ክርስትና ቀመስ አገር በቀል አስተምህሮዎቻችንን ወደ እግዚአብሔር ቃል መመለስ አለብን። የኢትዮጵያ አብያተ ክርስቲያናት ኦርቶዶክስ፣ ካቶሊክና ፕሮተስታንቶች የሚል ልዩነት ሳይኖር ሁላችንም ወደ እውነተኛ ቃሉ እንመለስ፤ ተመልሰን ራሳችንን በመመዘን ለተሐድሶና ለለውጥ ብንነሣ ለዓለም የበረከት ምክንያቶች እንሆናለን። አብያተ ክርስቲያናቱ ይህን ወሳኝ ጊዜ ካልተጠቀሙ ለራሳቸው፣ ለአገራቸውና ለዓለምም በወንጌል የለውጥና የዕድገት ሚና ሊጫወቱ ቀርቶ ሕሊውናቸው ራሱ በአደጋ ላይ ነው። ሁሌ ቆሞ የማይጠብቀን የበረከትና የተሐድሶ ዕድል በደጃችን ቆሞ ይጠራናል። በወቅቱ በዚያ የፀሎት

[185] ዝኒ ከማሁ ገጽ 10

ታሪክን የሚያወሩ ሳይሆኑ ታሪክን ለመሥራት መለኮታዊ ራእይን የሰነቁ ልጆች ለኢትዮጵያ ዛሬ ያስፈልጓታል:: ራእይ ማጣትን በራእይ ኃይል የሚበቀሉና የግራ መጋባትን ጽልመት ከምድሪቷ የሚገፉ ኃያላን ይነሣሉ:: ዛሬ ይህን መጽሐፍ የምታነብ ወገኔ ከእነዚያ ባለ ራእዮች አንዱ አንተ እንደሆንክ ታውቃለህ? የእግዚአብሔር ቅናት ይህን  በአንተ እውን ያደርጋል:: በተሐድሶ፣ ለተሐድሶ እንነሣ! በ21ኛው ክፍለ ዘመን የቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ጀምሯል:: ይህ የተሐድሶ አዋጅ ነው:: ወደ እግዚአብሔር ቃል እንመለስ:: ንስሐ እንግባ:: ተባርከን ለበረከት እንሆናለንና:: እግዚአብሔር ኢትዮጵያን ይባርክ::

በአገራችን የሃይማኖታቸውን የበላይነት የሚሰብኩና እውነትን የተቀሙ አንዳንድ ሰዎች *“ፕሮቴስታንት”* ማለት “ሰይጣን” ማለት ነው በማለት ያለማወቃቸውን እንደ ዕውቀት ሲገልጡ ተስተውለዋል:: ነገሩ እነርሱ እንዳሉት ይሆን? ሌሎች ደግሞ ራሳቸውን እንደ አገር በቀል ቤተ እምነት በመቁጠር *የፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናትን “መጤ”፣ “የምዕራባውያን ቅጥረኞች”*፣ ስለአገራቸው ግድ የማይላቸውና *“ባንዳዎች”* አድርገው ከመቁጠር አልፈው የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ በዓለም ላይ የአሉታዊ ተጽዕኖ ብቻ እንዳመጣ ኢሚዛናዊ ምስክርነታቸውን በተለያየ መልኩ ስላናፈሱ ተደጋግሞ የተነገረው ውሸት በአንዳንዶች ዘንድ እንደ እውነት ሳይቆጠር አልቀረም::

በእውነት ፕሮቴስታንቶች ለአገር ግድ የማይላቸው፣ ባንዳዎች ናቸው እንዴ? የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለም አዎንታዊና አንፀባራቂ ለውጦችን ያመጣ አይደለም ወይ? በዓለማችን ለወንጌል ሚሲዮናዊነት እንቅስቃሴ፣ ለሥራ ፈጣሪነት፣ ለዲሞክራሲ፣ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ፣ ለዩኒቨርሲቲዎችና የምርምር መስፋፋት፣ ለሰው ልጆች የኗኗር ለውጥ፣ ለቤተ ክርስቲያንና መንግሥት መለያየት አንዱ ምክንያት የፕሮቴስታንት እንቅስቀሴ በዓለማችን መከሰት አይደለም ወይ?  ለሚሉ ወሳኝ ጥያቄዎች መልሶችን በሚከተለው ምዕራፎች እናገኛለን:: እንዲሁም የፕሮቴስታንት አጀማመር፣ የፕሮቴስታንት ምሶሶያት፣ የፕሮቴስታንት እንቅስቃሴ  ዓለም አቀፍ አዎንታዊ ተጽዕኖዎችና እግዚአብሔር ለስሙ ክብር ባለፉት 500 ዓመታት በፕሮቴስታንት አብያተ ክርስቲያናት በኩል የሠራቸውን አበይት ድንቅ ሥራዎቹን በወፍ በረር በሚከተሉ ምዕራፎች በመቃኘት ለዘመናችን ትምህርት እንቀስማለን::

ዋናውና ትልቁ ትኩረቴ በፕሮቴስታንቶች በተጠቀመው ጌታና ፕሮቴስታንቶች የሰበኩት የጠራው የዘላለም ወንጌል ላይ እንጂ በሆን ጊዜ ተነሥቶ በሆን ጊዜ በሚጠፋው እንቅስቃሴ ላይ እንዳልሆነ አንባቢያን እንድረዱኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ:: እኔ ክርስቶስን እንድሰብክ እንጂ ለፕሮቴስታንት ጥብቅና አልተጠራሁም:: ለዓለም ጥያቄ መልስ ኢየሱስ እንጂ ፕሮቴስታንትዝም አይደለምና::





# ክፍል ሁለት

## ዓለምን የለወጠው የፕሮቴስታንት ተሐድሶ